ከመጀመሩ በፊት ጥቅምት 10 ቀን 1949 ዓ.ም አባሎቹ ሲመረጡ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ « የጣልያን ኮሚቴ » ብለው እንደሰየሙት ሁሉ፣ በእውነትም የጣልያን ኮሚቴ መሆኑን በአሠራሩ ደህና አድርጐ አረጋገጠ።

የንዑስ ኮሚቴው ረቂቅ ውሳኔ መጀመሪያ በዋናው ኮሚሲዮን ቀጥሎ በጠቅላላው ጉባኤ መታየት ስለአለበት፤ እስከ መጨረሻው ተሟግቶ ለማስለወጥ ተስፋ አንቆርጥም ብለው የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ትግላቸውን ቀጠሉ።

# የዋናው ኮሚሲዮን ችሎት

መላው የተባበሩት መንግሥታት አባሎች የሚካፈሉበት የዋናው ኮሚሲዮን ጉባኤ፣ በንዑስ ኮሚቴ «17» ተዘጋጅቶ የቀረበለትን ረቂቅ ውሳኔ በሚመረምርበት ጊዜ፣ ለትክክለኛ ፍርድ የቆሙ አንዳንድ አገሮች በሚሰጡት አስተያየት፤ የጣልያንና የግሩፖቹ ሤራ ሊፈርስ ይችላል በማለት የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ተስፋ አድርገው ነበር።

ጉባኤው ሥራውን ሲጀምር፣ የዩጐዝላቪያና የኒውዚላንድ፣ የላይቤሪያና የፊሊፒን መልዕክተኞች በንዑስ ኮሚቴ 17 የተዘጋጀው መፍትሔ ኢትዮጵያን ለማሳዘን የተሰነዘረ በመሆኑ፣ ዋናው ኮሚሲዮን ለውሳኔ እንዳይቸኩል አስጠነቀቁ። እንደዚሁም የታላቋ ብሪታንያ እና የአሜሪካ እንደራሴዎች በሰጡት መግለጫ፣ ንዑስ ኮሚቴ 17 እንደጠየቀው ለሁለተኛ ጊዜ መርማሪ ኮሚሲዮን ወደ ኤርትራ መላክ፣ ጊዜ ለመፍጀት ካልሆነ በስተቀር፣ ከዚህ ቀደም በአራቱ ኃያላን መንግሥታት ቡድኖች የተደረገውን ጥናት ሊለውጠው አይችልም በማለት ጉባኤውን ለማሳመን ሞከሩ። በተለይም የኒውዚላንድ መልዕክተኞች መሪ፣ ሰር ካርል በረንድሰን (SIR CARL BERENDSEN) በገለጸው አስተያየት፣ « .... በዘር፣ በባሕልና በታሪኩ ያለውን አንድነት አምኖበት፤ አብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ጋር እንቀላቀል ብሎ ሲጠይቅ፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እንቅፋት መሆን አይገባውም ... » የሚል አስተያየት ሰጥቶ ነበር። ነገር ግን በብዛትም ሆነ በአፈኛነት የኮሚሲዮኑን ገበታ እንቀው የያዙት የጣልያን ወገኖች፣ የንዑስ ኮሚቴ 17 የሥራ ውጤት እጅግ የሚደነቅና የሚመሰገን ከመሆኑም በላይ፣ ከዚህ ከቀረበው ሌላ የተሻለ መፍትሔ አይገኝም እያሉ፣ በጩኸት አዳራሹን ስለአፈኑት፣ በጣም ጥቂቶቹ የኢትዮጵያ ደጋፊዎች አስተያየት አልተደመጠም።

የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ ባደረጉት ንግግር፣ « የንዑስ ኮሚቴ 17 » አባሎች ሆነው የተመረጡት የጣልያን ወገኖች፣ የሮማ መንግሥት የሰጣቸውን መምሪያ ነጥብ በነጥብ ተከትለው ያዘጋጁትን ሕገ ወጥ የሆነ ረቂቅ ውሳኔ፣ እነሱ ራሳቸው አድናቂዎች፤ እነሱ ራሳቸው አመስጋኞች ሆነው፣ የሚያደርጓቸውን የማወናበጃ ዲስኩሮች፣ ኮሚሲዮኑ እንዲገነዘበው በሰፊው ጥረው ነበር። እንደተባለውም የጣልያን አፈ ጉባኤዎች በአርጀንቲናና በፓኪስታን ተቀዳሚነት « ...... ለኤርትራ ጉዳይ ተገቢው መፍትሔ ነፃነትን መስጠት ነበር። ነገር ግን አንዳንድ አገሮች የተባበሩት መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን ልኮ፣ የሕዝቡን ትክክለኛ ፍላጐት አጣርቶ ያቅርብልን ብለው ስለአመለከቱ፤ ሁላችንም በዚህ ሀሳብ

ተስማምተን ይህንን ውሳኔ አቅርበናል ...... » በማለት በየዲስኩራቸው መራቀቃቸውን ቀጠሉ::

የሶቪየት መንግሥትም፣ በተለይ ቼኮዝሎቫኪያንና ፖላንድን አስከትሎ በንዑስ ኮሚቴ 17 ተዘጋጅቶ የቀረበው መፍትሔ የተቀነባበረው፣ የኮሎኒያሊስቶቹን ጥቅም ለመዳበር በሚያስችል መንገድ መሆኑን በመተንተን፣ በስፊው ማውገዙ አልቀረም ነበር:: ይሁን እንጂ የሶቪየት መንግሥት መልዕክተኛ ባደረገው ንግግር፣ ምንም እንኳን ጣልያን በሞግዚትነት ወደ ሱማሌም ሆነ ወደ ኤርትራ መመለስ የለበትም ብሎ፣ አጥብቆ የሚቃወም ቢሆንም፣ በተለይ በኤርትራ ጉዳይ ስለ ኢትዮጵያ ጥያቄ የሰጠው የመጨረሻው አስተያየት፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን መንግሥት እጅግ ቅር የሚያሰኝ ሆነ:: ኤርትራና ሱማሌ፣ መስኮብ አባል በሆነበት በተባበሩት መንግሥታት የሞግዚት አስተዳደር፣ ለአምስት ዓመታት ቆይተው ነፃነታቸውን ቢቀበሉ ይሻላል በማለት፣ የሶቪየት መንግሥት ያለማቋረጥ ሲደክም እንደሰነበተ ይታወሳል:: የሶቪየት መልዕክተኛ ያቀረበውን ሬዞሉሽን ለማስረዳት ባደረጋቸው ዲስኩሮች ሁሉ፣ እስከዛሬ ድረስ የኢትዮጵያን ጥያቄ በቀጥታ የሚቃወም ንግግር ሲሰነዝር አልተሰማም ነበር:: አሁን ግን በኅዳር 7 ቀን 1949 ዓ.ም፣ በዋናው ኮሚሲዮን ላይ በሰጠው ሰፊ መግለጫ ውስጥ፣ በኤርትራ ጉዳይ የኢትዮጵያ ጥያቄ ተገቢ አይደለም በማለት፣ ፊት ለፊት ተቃውሞውን በመግለጹ፣ ለአቶ አክሊሉ ሀብተወልድና ለመልዕክተኞቻቸው ያልጠበቁት አዲስ ነገር ሆነባቸው:: የማርሻል ስታሊን ልዑክ፣ በሰጠው መግለጫ፣
« ..... የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደጋግሞ ሲናገር እንደሰማነው፣ ለኤርትራ ነፃነቷ ከኢትዮጵያ ጋር መዋሀዷ ነው ይላል:: ..... የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መልዕክተኛ በዚህ ሀሳቡ የሚጸና ከሆነ፣ በመጀመሪያ ለኤርትራ ሕዝብ ነፃነቱ ከተሰጠው በኋላ፣ ከኢትዮጵያ ጋር ለመቀላቀል፣ ወይም ራሱን ችሎ ለብቻው ለመኖር መወሰን ያለበት፣ ራሱ ሕዝቡ ነው እንጂ፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አለመሆኑን እንዲገነዘብ ያስፈልጋል:: ....... የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዛሬውኑ መወሰን የሚገባው፣ ለኢትዮጵያ በአሰብ በኩል የባሕር በር እንዲሰጣት ማድረግ ብቻ ነው:: ለዚህ የሶቪየት ሶሻሊስት ሬፑብሊክ መንግሥት ሙሉ ድጋፉን ይሰጣል ..... » ሲል አስተያየቱን አቀረበ::

የኤርትራ ጉዳይ ወደ ተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከተዛወረበት ጊዜ አንስቶ፣ የመስኮብ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሙሴ ሞሎቶቭ፣ አቶ አክሊሉን ብዙ ጊዜ ሲያነጋግራቸው፣ የሶቪየት መንግሥት ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር እንድትቀላቀል በቀጥታ ባይደግፍም፣ እንደጠላት እየተከታተለ በቀጥታ ለማጥቃት እንደማይፈልግ ተስፋ ስጥቷቸው ነበር:: በኢትዮጵያም በኩል እስከዚህ እስከ ኅዳር 7 ቀን 1949 ዓ.ም ድረስ፣ ከመስኮብ የሚሰጠውን መግለጫ፣ ቀጥታ የሆነ የተቃውሞ መልስ ተሰጥቶ አያውቅም:: አሁን ግን የመስኮብ መልዕክተኛ የተናገረው፣ ጠላት የሆነው ጣልያን ከሚያደርገው ዲስኩር ጋር የተመሳሰለ እና፣ በተለይም በዚህ የኤርትራ ጉዳይ በተፋፋመበት ኮሚሲዮን ላይ ይህን የመሰለ አስተያየት የተሰነዘረው፣ ኢትዮጵያን ለመጉዳት ታስቦ ስለሆነ፣ አክሊሉ ሀብተወልድ መልስ መስጠት አለብኝ አሉ::

« ..... ሁለት ዓመት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ የአራቱ ኃያላን መንግሥታቶች፣ የመስኮብና የአሜሪካ፣ የእንግሊዝና የፈረንሣይ ዳኞች ኤርትራ



የኢትዮጵያ መልዕክተኞች፤

(ከግራ ወደ ቀኝ) ብላታ ኤፍሬም ተወልደመድህን፣ አቶ ተስፋዬ ተገኝ፤

(SEPT. 1949)
(ፎቶU.N)

ተልከው፣ የሕዝቡን ፍላጐት በመረመሩ ጊዜ፣ አብዛኞቹ ኤርትራውያኖች ወደ ጥንት አገራቸው ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ መጠየቃቸውን የሶቪየት መንግሥት ይዘነጋዋል ብለን አናስብም ነበር:: ...... የኢትዮጵያም ጥያቄ በትክክለኛ የታሪክ ማስረጃ እና፣ በትክክለኛ የሕዝብ ፍላጐት ላይ ተመሥርቶ የቀረበ መሆኑን፣ ጠላታችን ከሆነው ከጣልያን መንግሥት በስተቀር፣ በሌሎቹ እንደ ሶቪየት ሕብረት በመሳሰሉት ታላላቅ አገሮች ዘንድ፣ አጠራጣሪ ሆኖ ይገመታል ብለን አልጠበቅንም:: ...... የመስኮብ መልዕክተኛ እንደተናገረውም በዘርና በባሕል የሚመሳሰሉ አገሮች ሁሉ፣ ያለ ሕዝቡ ፍላጐትና ያለ ሕዝቡ ጥያቄ በግዴታ መዋሀድ አለባቸው ብላ፣ ኢትዮጵያ የማታዋን መሆኗን ማረጋገጥ እንወዳለን:: ...... የሩቁን ትተን በቅርቡ ዘመን የተፈጸሙትን ታሪኮች እንኳን ብንመለከት፤ ባለፉት ሠላሣ ዓመታት በመስኮብ አገር ከተካሄደው ሬቮሊሲዮን በኋላ፣ የልዩ ልዩ አገር ሕዝቦች በምን አኳኋን፣ በሶቪየት ሕብረት መንግሥት አስተዳደር ውስጥ እንደተዋሀዱ፣ ማስታወስ እንችላለን:: ያንድ አገር ሕዝብ ከሌላው ጋር የሚቀላቀለው፣ በሕዝቡ ፈቃድና ፍላጐት ብቻ መሆኑን ከተማመንበት፣ የዛሬ ስባት ዓመት በ1941 እና 42 ዓ.ም፤ እነ ኤስቶኒ (ESTONIE) ሌትዋኒ (LETTOINIE) እና ሊቱዋኒ (LITUANI) የተባሉት የመንግሥታት አገሮች፣ ብሔራዊ ነፃነታቸውን መስዋዕት አድርገው፣ በሶቪየት መንግሥት ውስጥ የተጠቃለሉት፣ በሕዝቦቻቸው ጥያቄ ወይስ በመሪዎቻቸው ፍላጐት ? መሆን አለመሆኑን መመራመር ያስፈልጋል ማለት ነው:: ...... እኔ ይህንን ስናገር፣ በሰው አገር የውስጥ ጉዳይ ለመግባት ወይም የመስኮብ ሬቮሊሲዮን፤ ለሰው ልጅ ነፃነትና ብልፅግና አዲስ በር ከፍቷል ብለው የሚያምኑትን አገሮች፣ ለመተቸት ወይም ተቃዋሚ ለመሆን አይደለም:: ማንም አገር፣ ማንም ሕዝብ፣ የሚበጀውንና የሚጠቅመውን የአስተዳደር ሥርዓት ለመምረጥ፣ ነፃነትና መብት አለው:: በዚህ አኳኋን እነ ኤስቶኒ በሶቪየት ሕብረት ውስጥ የተጠቃለሉት፣ በሕዝቦቻቸው ፈቃድና ፍላጐት ነው ከተባለ፣ ኮሎኒያሊስት ጣልያን በጦር ኃይል ገንጥሎ የወሰዳቸው ወንድሞቻችን ኤርትራውያኖች፣ ወደ እናት አገራቸው ወደ ኢትዮጵያ እንመለስ ብለው ሲጠይቁ፣ የተለየ ምርመራ ሊደረግባቸው አይገባም:: ....... በዚህ ኮሚሲዮን ላይ የሚካፈሉትን የተባበሩት መንግሥታት አባሎች፣ ኢትዮጵያ አጥብቃ የምትለምነው፤ ፍርድ እንዳይዛባ ብርቱ ጥንቃቄ እንዲደረግ ነው:: ኤርትራውያኖች ከእናታቸው ጋር ለመሆን፣ ኢትዮጵያም ልጆቿን ለመቀበል፣ እጅግ የተነፋፈቁና በጋለ ስሜት የሚጠባበቁ መሆናቸውን፣ የዓለም ዳኞች ማተኮር ይኖርባቸዋል:: ....... ኢትዮጵያ ቀደም ሲል እንዳመለከተችው « ንዑስ ኮሚቴ 17 » ለሀያ ቀናቶች ደክሜበታለሁ ብሎ ያቀረበው ረቂቅ ውሳኔ፣ የጣልያንን መንግሥት ለማስደሰት የተዘጋጀ ስለሆነ፣ ይህ ኮሚሲዮን ስህተት ላይ እንዳይወድቅ በጥብቅ አሳስባለሁ:: .... »

ከዚህ በላይ እንደታየው የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለሶቪየት መልዕክተኛ የሰጡት መልስ፣ በመስኮቦቹ እና በወገኖቻቸው ዘንድ የጠነከረ ሆኖ መገመቱ የማይካድ ነው:: ሆኖም በዚያን ሰዓት፣ በሶቪየት መልዕክተኞች መሪ ወንበር ላይ የነበረው ሚስተር አሩቲኡኒያን (AROUTIOUNIAN) ለአቶ አክሊሉ ንግግር መልስ ለመስጠት አልፈለገም:: በመሠረቱ ሶቪየት ሕብረትና ሳቴሊቶቹ፣ ለኢትዮጵያ የአሰብን የባሕር በር ሰጥቶ ከኤርትራ ጥያቄ ማስናበት ነው ብለው የወሰኑ ስለሆነ፣ የአቶ አክሊሉ ንግግር ከዚህ የለሰለሰም ቢሆን የመስኮብን አቋም ሊለውጠው እንደማይችል የታወቀ ነበር::

በዚህ ኮሚሲዮን ሥራ ላይ የተካፈሉት፣ ብዙዎቹ የመንግሥታት ወኪሎች፣ የጣልያን አፈ ጉባኤዎች በሚያሰሙት የፕሮፓጋንዳ ጩኸት ስለደነቆሩ፤

የኢትዮጵያን አቤቱታ መመራመር አልቻሉም። ሌሎቹም እንደ እንግሊዝና አሜሪካ የመሳሰሉት አገሮች፣ በዚያን ሰዓት «ንዑስ ኮሚቴ 17» ያቀረበውን ሬዞሉሽን ከመቀበል በስተቀር ሌላ መንገድ አልታይ አላቸው። በዚህ ሁኔታ ኢትዮጵያ ብቻዋን የምታደርገው ትግል፣ ጉዳዩን ሊለውጠው እንደማይችል ተረጋገጠ። በመጨረሻ፤ ኅዳር 7 ቀን 1949 ዓ.ም « ንዑስ ኮሚቴ 17 » ባዘጋጀው ረቂቅ ውሳኔ፣

1. ሊቢያ፤ ሶስቱም አውራጃዎቿ ሳይነጣጠሉ በመጭው ሁለት ዓመት ውስጥ ነፃነቷን እንድትቀበል፣

2. ሱማሌ፤ በተባበሩት መንግሥታት ስም ለአሥር ዓመታት፣ ጣልያን በሞግዚትነት ካስተዳደራት በኋላ፣ ነፃነቷ እንዲሰጣት፣

3. ኤርትራ፤ የተባበሩት መንግሥታት አምስት አባሎች ያሉበት መርማሪ ኮሚሽን ተልኮ፣ የሕዝቡ ፍላጐት ምን እንደሆነ እንዲታወቅና፣ በመጭው ዓመት የወደፊት ዕድሉ እንዲወሰን፣ ከሃምሣ ዘጠኝ አባል መንግሥታቶች ውስጥ፣ በአርባ ሰባት ድምፅ ብልጫ ተደግፎ፣ ሬዞሉሽኑ በጠቅላላው ጉባኤ እንዲጸድቅ ተላለፈ። የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ በዚህ በተደረገው ውሳኔ የተሰማቸውን ከፍተኛ ቅሬታና ሀዘን ከገለጹ በኋላ፣ የመጨረሻ ዕድላቸውን ለመሞከር በጠቅላላው ጉባኤ ላይ ይግባኝ ለመጠየቅ፣ የኮሚሲዮኑን የስብሰባ አዳራሽ በትካዜ መንፈስ ለቀው ወጡ።

## የጠቅላላው ጉባኤ ውሳኔ

ቅዳሜ ኅዳር 19 ቀን 1949 ዓ.ም ከእኩለ ቀን በኋላ በዘጠኝ ሰዓት፤ በአጀንዳ ቁጥር 19 የተመዘገበው፣ የቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ዶሴ፣ የመጨረሻውን ውሳኔ እንዲያገኝ ለጠቅላላው ጉባኤ ቀረበ።

በፊሊፒን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በዤኔራል ካርሎስ ሮሙሎ (CARLOS ROMULO) ሊቀመንበርነት የሚመራው፣ የአራተኛው ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ፣ በዋናው ኮሚሲዮን ተጠንቶ የቀረበለትን ረቂቅ ውሳኔ፣ የየመንግሥታቱ እንደራሴዎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት ጠየቀ። የመጀመሪያዎቹ ተናጋሪዎች የሆኑት የሶቪየት ሕብረትና ሳቴሊቶቹ፣ በዋናው ኮሚሲዮን 'የተዘጋጁትን መፍትሔዎች ከተቃወሙ በኋላ፣ በተለይ ሱማሌ ለጣልያን እንድትሰጥ፣ ወደ ኤርትራም መርማሪ ኮሚሽን እንዲላክ፣ የተባለው ሀሳብ ለምዕራባውያኖችና ለኮሎኒያሊስቶች ጥቅም ሲባል በመሆኑ፣ የተባበሩት መንግሥታት አባል አገሮች ሊያወግዙት ይገባል አሉ።

በሶቪየት ሕብረት መሪነት አራቱ አገሮች፣ ፖላንድና ቼኮዝሎቫኪያ፣ ቢሎሩሲያና ኡክሬን በአንድነት ሆነው ባቀረቧቸው ሀሳቦች ውስጥ፤

1ኛ/ ኤርትራና ሱማሌ መስኩብ ተካፋይ በሚሆንበት በተባበሩት መንግሥታት የሞግዚት አስተዳደር ኮሚቴ፣ ለአምስት ዓመታት ሲደራጁ ከቆዩ በኋላ፣ ነፃነታቸውን እንዲቀበሉ፤

2ኛ/ ለኢትዮጵያ በፋሽስት ዘመን ለደረሰባት በደል መካሻ እንዲሆናት፣ የአሰብ የባሕር በር ወደብ ተከልሎ እንዲሰጣት፣ የተሻለ መፍትሔ ነው ሲሉ፣

የአባል መንግሥታቶችን ድጋፍ ጠየቁ።

አምስቱም አገሮች በየተራ እየተነሱ በስሚቸው መግለጫዎች፣ ኮሎኒያሊስቶችና ኢምፔሪያሊስቶች በሆኑት በአሜሪካ፣ በእንግሊዞችና በፈረንሣዮች ተንኮል፣ የእነዚህ የድሆች አገሮች ዕድል እስካሁን ሳይወሰን ጊዜ የፈጀበትን ምክንያት በሰፊው አስረድተዋል። በተለይ የፖላንድ መልዕክተኛ ኮሎኒያሊስቶች የተባሉትን አገሮች ሲወቅስ የተናገረው ዘለፋ ብዙዎቹን መልዕክተኞች አስቋቸዋል። « ...... ባለፉት ሁለት ሳምንታት በዋናው ኮሚሲዮን ላይ ተሰብስበን በነበረ ጊዜ፣ የአንድ አባል መንግሥት መልዕክተኛ መግለጫውን ሲሰጥ፣ <u>በሕዝቦች ላይ የግፍ አስተዳደር መሥርቶ ሲያንሰራራ የኖረው ኮሎኒያሊዝም፣ በጠና ታሞ ለሕይወቱ ፍጻሜ በማጣጣር ላይ ይገኛል።</u> ..... » ብሎን ነበር። ይሁን እንጂ ይኸው ተናጋሪ የዘነጋው፤ ይህንን ለሞት የሚያጣጥረውን ኮሎኒያሊስት፣ እንደ ምንም አድነው <u>የቀድሞዎቹን ቅኝ ግዛቶቹን ለመረከብ እንዲችል፣ ግላድዌል እና ጀሲፕ የተባሉት፣ ሁለት የታወቁ የእንግሊዝና የአሜሪካ ሐኪሞች</u> ብርቱ ጥረት በማድረግ ላይ መሆናቸውን ነው፤ ብሎ ሲናገር፤ ለጊዜው አዳራሹ በሳቅ ሆሆታ ሞቆ ነበር። እንግሊዝና አሜሪካ፣ ሱማሌ ለጣልያን እንድትሰጥ በመደገፋቸው፣ ዛሬ የፖላንድ መልዕክተኛ ተቃዋሚ ሆኖ እንደዚህ ሲያፌዝ፣ እሱ ራሱ ከጥቂት ጊዜ በፊት ሱማሌን ብቻ ሳይሆን ኤርትራና ሊቢያም፣ ለጣልያን ኮሎኒያሊስት ካልተመለሱለት ብሎ ይጮህ እንደነበረ ጨርሶ ረስቶታል። ፖላንድ፣ ከመስኮብ ጋር ሆኖ ለጣልያን ሶስቱም የቀድሞ ቅኝ ግዛቶቿ እንዲሰጧት በሚደግፉበት ጊዜ፤ አሜሪካና እንግሊዝ ተቃዋሚዎች እንደነበሩ ትዝ አላለውም።

ሶቪየት ሕብረትና አራቱ ተከታዮቹ፣ ለዋናው ኮሚሲዮን ውሳኔ የቀረቡት መፍትሔዎች፣ መጽደቅ የለባቸውም ብለው ያደረጉትን ተቃውሞ፣ ኢትዮጵያ የምትስማማበት ቢሆንም፣ በለውጡ ከመስኮብ የሚቀርበው ሀሳብ አያረካትም። ኢትዮጵያ በኤርትራ ጉዳይ የምታደርገው ተጋድሎ፣ የአሰብን የባሕር በር ተቀብሎ ለመስናበት ሳይሆን፣ መሠረተ ታሪኳን እቦታው ለመመለስ መሆኑን እነዚህ አምስቱ የሶሻሊስት አገሮች አልተረዱላትም። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ በኋላ፣ ሁኔታዎቹ እንደአሳዩት፣ ኢትዮጵያ ኤርትራን ማግኘት የለባትም የሚል ጠላት ቢበዛባትም፣ አሰብን ለመውሰድ አንዳችም ተቃዋሚ አልነበራትም።

ሶቪየት ሕብረትና ተከታዮቹ ያላቸውን ተቃውሞ በሰፊው ካስረዱ በኋላ፣ በአርጀንቲና እና በፓኪስታን ግንባር ቀደምትነት የጣልያን ወገኖች በየተራ እየቀረቡ፣ በዋናው ኮሚሲዮን ተባርከው የቀረቡት መፍትሔዎች ያለ አንዳች ለውጥ በፍጥነት እንዲጸድቁ ጩኸታቸውን ማቀጣጠል ጀመሩ። ሩጫው በዚህ አኳኋን ከቀጠለ፣ የኅዳር 19 ቀን ቅዳሜ ሳይመሽ፣ የጣልያን ወገኖች የሚፈልጉትን



የኢትዮጵያ መልዕክተኞች አቶ አበበ ረታ እና ብላታ ዳዊት ዕቁባ እግዚእ፣ ከየመን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጋር፣

« ..... ኤርትራ ለኢትዮጵያ መመለስ የለባትም ብላችሁ ድምፃችሁን ለማሰማት ስትወስኑ፣ በኢትዮጵያ የሚኖሩትን ሀያ ሺህ የየመን ተወላጆች አብራችሁ አስቧቸው ....... »

(አበበ ረታ ኅዳር 1950 ኒውዮርክ)
(ፎቶ U.N)

በከፍተኛ ድምፅ ብልጫ፣ ድል እንደሚመቱ ለኢትዮጵያ መልዕክተኞች ግልጽ ሆኖ ታያቸው::

ባለፈው ግንቦት ወር በተደረገው የሶስተኛው ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ፣ ተጠንቶ ያለቀለት የኤርትራ ጉዳይ ሳይጸድቅ የቆየው፣ ለውሳኔ ችግር በፈጠሩት በሊቢያና በሱማሌ ጉዳይ እንደነበረ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ካስታወሱ በኋላ፤ « ... ከግንቦት እስከ መስከረም ባሉት አራት ወራት ውስጥ ምን ተዓምር ደርሶ፣ የኤርትራ ጉዳይ እንደገና ይመርመር የተባለበትን እውነተኛውን ምክንያት፤ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፣ ለአባሎቹ ማስረጃ መስጠት አለበት ...... » ሲሉ ጠየቁ:: የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንድ ሰዓት ያህል በፈጀው ንግግራቸው፤ በንዑስ ኮሚቴ 17 እና በዋናው ኮሚሲዮን የተዘጋጁት መፍትሔዎች፤ ምን ያህል የተዛቡና ከትክክለኛ ፍርድ የራቁ መሆናቸውን በመረዳት ጠቅላላው ጉባኤ እንዲሰርዘው፣ የመጨረሻ ዕድላቸውን በሞከሩ ጊዜ፣፣ ያቀረቧቸው ማሳሰቢያዎች በሚከተሉት ነጥቦች ላይ የተመረከዙ ነበሩ::

1. የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ባለው የአሠራር ሕግ መሠረት፣ ትናንት በከፍተኛ ድምፅ ብልጫ የተስማማበትን ጉዳይ ዛሬ በቀላሉ ያለአንዳች ምክንያት የሚያፈርሰው ከሆነ፣ ለዓለም ሠላም ደህንነት፣ ለአገሮችና ለሕዝቦች ነፃነት፣ ተግባሩን የሚፈጽም ነው ተብሎ እንዴት ሊታመን ይችላል ?

2. በዓለም ላይ ባደረሰችው ጥፋት ምክንያት እስከ ዛሬ ድረስ የተባበሩት መንግሥታት አባል ለመሆን ያልተፈቀደላት ጣልያን፤ ዛሬ በምን ሕግ ? በምን ደንብ ? በተባበሩት መንግሥታት ስም፣ ሱማሌን በሞግዚትነት እንድታስተዳድር ሥልጣን ይሰጣታል ? .....

3. በ1946 ዓ.ም በተካሄደው በፓሪሱ የሠላም ጉባኤ ውሳኔ መሠረት፣ ጣልያን የቀድሞ ቅኝ ግዛቶቿን መልቀቋን አረጋግጣ የፈረመችውን ውል እንድታከብር የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለምን አያስገድድም ? ..... እንግዲህ፣ የተፈረደበት አቅሙን እየተማመነ ፍርዱን ካልተቀበለ፣ ፍርድ ሰጭውም ደካማ ሆኖ የፈረደውን ማስፈጸም ካልቻለ፣ የዳኝነቱ ጠቃሚነት ወይም አስፈላጊነት እምን ላይ ነው ?

### የመንግሥታት እንደራሴዎች ሆይ

...... የጣልያን ወገኖች ከፍ ያለ ትብብር በማድረግ፣ የሮማ መንግሥት የሚፈልገውንና ኢትዮጵያን አደጋ ላይ የሚጥለውን መፍትሔ አዘጋጅተው አቅርበውላችኋል:: ዛሬ ይህ ውሳኔ ጸድቆ ጣልያን በቀላሉ ወደ ሱማሌ ከተመለሰች፣ ነገ ወደ ኤርትራ በአንድ መንገድ ለመሻገርና ከዚያም እንደለመደችው ኢትዮጵያን ለማጥቃት እንደምትሞክር፣ ባለፉት ሃምሣ ዓመታት ሶስት ጊዜ ተደጋግመው የደረሱት ሁኔታዎች በቂ ማስረጃዎች ናቸው::

...... የኤርትራ ሕዝብ፣ የታሪኩንና የዘሩን አንድነት ተመርኩዞ ኢትዮጵያዊነትን ሲጠይቅ፣ የሱማሌ ሕዝብ ለግፈኛው ጣልያን እንዳትስጡን እያለ ሲጮህ፤ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅታችን እንዴት አድርጎ የቆመበትን መሠረት ጥሶ፤ ያለበትን ኃላፊነት ስቶ፤ ከሕዝቦች ፍላጎትና ጥያቄ ውጭ የሆነ ፍርድ ያዘጋጃል ? ...... ብለው ከጠየቁ በኋላ ንግግራቸውን ሲፈጽሙ፤

-- በሕዝቦች መብትና በትክክለኛ ፍርድ ለሚያምኑ የተባበሩት መንግሥታት አባሎች፣ ሕግና መብት ለሁሉም እኩል እንዲከበር ለሚታገሉ መንግሥታቶች፣ ለምንኖርበት አስቸጋሪ ዓለም ለዛሬውም ሆነ ለወደፊቱ የሠላም ዋስትና እንዲኖር ኃላፊነቱ ለሚመለከታቸው ለአራቱ ኃያላን መንግሥታቶች፣ ኢትዮጵያ የአቤቱታ ድምጿን ደጋግማ ከማሰማት አታቋርጥም ...... » አሉ።

ከዚህ በላይ ባጭሩ የተገለጸውን የአቶ አክሊሉን ንግግር ያዳመጡ የመንግሥታት እንደራሴዎች፣ ኢትዮጵያ፤ እንዲጸድቅ በቀረበው ውሳኔ ምን ያህል እንደተጨነቀች፣ ከዚህም በላይ የገለጸችው አስተያየት ሁሉ፣ እውነትንና ትክክለኛ መሠረትን የጨበጠ መሆኑን ሳይገነዘቡት አልቀሩም። ነገር ግን የተባበሩት መንግሥታት የኤርትራንና የሱማሌን ጉዳይ ለመወሰን የተዘጋጀው፣ ሕግንና እውነትን ተመርኩዞ ሳይሆን፣ በጥቅም በተሳሰሩ ወገንተኞች ተወጥሮ ስለሆነ፤ የኢትዮጵያን አቤቱታ አዳምጦ የተገባውን ፍርድ ለማቃናት አንዳችም እርምጃ ለመውሰድ አልሞከረም።

በንዑስ ኮሚቴ 17 እና በዋናው ኮሚሲዮን ላይ ኢትዮጵያን ሲረዱ የሰነበቱት አገሮች ሁሉ፣ ጉዳዩ በጠቅላላው ጉባኤ መታየት ሲጀምር ድምፃቸውን ፀጥ አድርገው፣ የታዛቢነት አቋም የያዙ መስለው ታዩ። ከዚህም በላይ በዋናው ኮሚሲዮን ተዘጋጅተው የቀረቡት መፍትሔዎች ሳይጸድቁ ቢወድቁ፣ የጣልያን ወገኖች « ለኤርትራ ነፃነት » የተባለውን ጉዳይ እንደገና ቀስቅሰው ጉባኤውን ሊያደፈርሱት ይችላሉ የሚል ሥጋት አደረባቸው። በተለይ እንግሊዞች፣ መርማሪ ኮሚሽን ወደ ኤርትራ ቢላክ፣ የኢትዮጵያን ዕድል አያበላሸውም፤ ወደ ሱማሌም ጣልያን የምትመለሰው ለተወሰነ ጊዜ ስለሆነ፣ እኛ እያለን በኢትዮጵያ ላይ የሚሰነዘር አደጋ የለም እያሉ፣ አቶ አክሊሉን ለማጽናናት ሞከሩ። የኢትዮጵያን አቋም ከልባቸው ሲደግፉ የኖሩት የላይቤሪያ፣ የዩጐዝላቪያና የፊሊፒን መልዕክተኞችም የቀረበውን ሬዞሉሽን ከመቀበል በስተቀር ሌላ ምርጫ የለም ብለው ተስፋ ቆረጡ። በዚህ ሁሉ ሁኔታ፣ ኢትዮጵያ ምንም ዓይነት ተዓምር ይፈጠራል ብላ እንደማትጠብቅ የተረጋገጠ ሆነ።

**በበደል ላይ በደል**

ሱማሌ ለጣልያን እንድትሰጥ፤ የኤርትራ ሕዝብ እንደገና በአዲስ መርማሪ ኮሚሽን ፍላጐቱ እንዲታወቅ መወሰኑ አንሶ፣ በበደል ላይ በደል ተጨምሮ ኢትዮጵያን የበለጠ ያሳዘናት፣ ከአምስቱ መርማሪ ዳኞች መካከል አራቱ የጣልያን ወገኖች እንዲመረጡ መቅረባቸው ነው።

ከእስላም አገሮች ፓኪስታን፣ ከላቲን አሜሪካ ጓቴማላ፣ ከእስያ በርማ፣ ከአውሮፓ ኖርዌይ፣ ከእንግሊዝ ከመንዌልዝ አገሮች በዘር ልዩነት ፖሊሲ የሚመራው ደቡብ አፍሪካ፣ የተባበሩት መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን አባሎች እንዲሆኑ ቀረቡ። ወዲያው ብላታ ኤፍሬም ተወልደመድህን ተነስተው፣ ለጠቅላላው ጉባኤ በሰጡት መግለጫ፣ በኤርትራ ጉዳይ ፍርዳቸውን አስቀድመው የሰጡ አገሮች ለዳኝነት ሥራ መመረጥ የማይገባቸው መሆኑን ካስረዱ በኋላ፣ « ...... በተለይ የፓኪስታኑ ወኪል፣ በዚህ በተሰበሰብንበት አዳራሽ ኢትዮጵያን በመቃወም ያደረጋቸውን ንግግሮች ጉባኤው እያወቀ፣ እንዴት ዳኛ አድርጐ ይሾመዋል ? ...... » ሲሉ ጠየቁ። እንደተለመደው አሁንም የኢትዮጵያን አቤቱታ አዳምጦ፣ የቀረው

ቢቀር የተባበሩት መንግሥታት ትዝብት ላይ እንዳይወድቅ፣ የዳኞቹን አመራረጥ ለማስለወጥ ሳይሞከር ቀረ።

ስኞ ኅዳር 21 ቀን 1949 ዓ.ም ከእኩለ ቀን በኋላ በአሥር ሰዓት በኒውዮርክ የተሰበሰበው የተባበሩት መንግሥታት የአራተኛው ጠቅላላ ጉባኤ፣

- የኤርትራ ጉዳይ በድጋሚ እንዲመረመር፣
- ሱማሌ ለጣልያን እንድትሰጥ፣
- ሊቢያ እንድነቷ ተጠብቆ፣ ከሁለት ዓመት በኋላ ነፃነቷን እንድትቀበል፣

በንዑስ ኮሚቴ 17 እና በዋናው ኮሚሲዮን የጣልያን ወገኖች ያዘጋጁትን ውሳኔ በድምፅ ብልጫ አጸደቀ።

# የ አ ክ ሊ ሉ ም ሬ ት

*« ....... ዳቦ ለጠየቀ ድንጋይ ...... »*

አራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ፣ በኤርትራና በሱማሌ ጉዳይ፣ በጣልያን ጥረት የተዘጋጀውን ረቂቅ ውሳኔ ባጸደቀ ጊዜ፣ ኢትዮጵያ ምን ያህል እንደተበሳጨችና እንዳዘነች፣ የቀድሞዋ ኃይለሥላሴ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለመላው የመንግሥታት እንደራሴዎች የመረረ ስሜታቸውን የገለጹት በሚከተለው መልክ ነበር።

« ..... አገሬ ኢትዮጵያ በዓለም ሸንጐ ላይ ፍርድ ተነፍጓት ስታዝን፣ ለመጀመሪያ ጊዜ አይደለም። በ1936 ዓ.ም ፋሽስት ጣልያን ነፃነቷን ሲደፍርና ሕዝቧን በመርዝ ጋዝ ሲጨርስ፣ የዠኔቩ የመንግሥታት ማህበር የኃይለኛውንና የግፈኛውን ጥቅም ለመጠበቅ፣ ፍርድ የነፈጋት መሆኑን ታሪክ ለዘለዓለሙ ሲያስታውሰው ይኖራል። ዛሬም ከአሥራ ሶስት ዓመታት በኋላ፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የታናናሽ አገሮችን መብት በመጣስና ለኮሎኒያሊስቶች ጥቅም በማሰብ፣ ያጸደቀው የተሳሳተ ውሳኔ፣ በነገው ታሪኩ በስፊው የሚተችበትና ትዝብት የሚደረግበት እንደሚሆን አልጠራጠርም።

...... የኮሎኒያሊዝም ዘመን ተፈጽሟል በተባለበት ሰዓት፣ ጣልያን ዓይነ ደረቅ ሆና፣ ቅኝ ግዛቶቼ ካልተመለሱልኝ ብላ፣ ያቀረበችውን የግፍ ጥያቄ፣ እንኳንስ የሚደግፍላት ይቅርና፣ ይህን ሀሳብ ለተባበሩት መንግሥታት ሸንጐ እንድታቀርብ የሚፈቅድላት አይኖርም ብላ፣ ኢትዮጵያ ከፍተኛ እምነት ነበራት። ለካስ ጣልያን የምታስበውን ለማስፈጸም ምን ማድረግ እንዳለባት ደህና አድርጋ ታውቅ ኖርዋል። የዛሬው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እንዳለፈው የዠኔቩ የመንግሥታት ማህበር፣ አቅም ያላቸው አገሮች ደጋፊዎቻቸውን እያሰፉ፣ ጉዳያቸውን በፈለጉት መልክ የሚያስፈጽሙበት ሸንጐ እንደሚሆን፣ አርቀን ያልተመለከትን እኛ የድሆች አገሮች ብቻ ነን።



*« ....... ሀገሬ ኢትዮጵያ በዓለም ሸንጎ ላይ ፍርድ ተነፍጓት ስታዝን የመጀመሪያ ጊዜ አይደለም። ....... ኢትዮጵያ ያለፉት ታሪኮቿ በትክክል እንዳስረዱት፣ ለነፃነቷና ለመብቷ፣ በኮሎኒያሊስት ጣልያን ጋር በየጊዜው ስትዋጋ፣ ያሸነፈችው ብቻዋን ነው። የተጠቃችውም ብቻዋን ስለሆነ፣ አገሬ መቸውንም ለሚደርስባት አደጋ ከማንም እርዳታ አገኛለሁ ብላ አትጠብቅም። ዛሬም ሆነ ነገ ነፃነቷን ለመጠበቅ፣ ታሪኳን ለማስከበር አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረግ ያለባት፣ እሷ ራሷ ብቻ ነች። ....... »*

አክሊሉ ሀብተወልድ
(ኅዳር 21 ቀን 1949 ዓ.ም)
(ፎቶ U.N)

...... ዕድሜ ለአርጀንቲና መንግሥትና ለላቲን አሜሪካ አገሮች፤ ኮሎኒያሊስት ጣልያን በተባበሩት መንግሥታት ባንዲራ ታጅባ፣ ሱማሌ ላይ ተመልሳ እንድትነግሥ ተበይኖላታል። የሱማሌ ሕዝብ ግን የኮሎኒያሊስት ጣልያንን አስተዳደር አልቀበልም፣ ሲል ያሰማውን እቤቱታ ማዳመጥ አያስፈልግም ተብሎ መብቱ ተነፍጎታል።

...... ዕድሜ ለአርጀንቲናና ለፓኪስታን መንግሥታት፤ አብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ ከእናት አገሩ ከኢትዮጵያ ጋር እንዲቀላቀል የገለጸው ስሜት፣ በቂ አይደለም ተብሎ፤ የጣልያን ወዳጆች የተሰየሙበት የዳኞች ክለብ እንዲመረምሩት ተወስኖበታል።

...... የኤርትራ ሕዝብ ፍላጐት ምን እንደሆነ፣ በድጋሚ መመርመር አለበት ተብሎ ሲወሰን፣ የሱማሌ ሕዝብ ኮሎኒያሊስት ጣልያንን መቀበል አለመቀበሉን ለምን አይጠየቅም ? ...... ይህ ሁኔታ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሚካሄደው ፍርድ የተዛባና የተሳሳተ ለመሆኑ በቂ ማስረጃ አይሆንም ወይ ? ...... ለነዚህ ለማቀርባቸው ጥያቄዎች፣ የጣልያን ወገኖች ሆነው ፍርዳቸውን ከሰጡት አገሮች መልሱን ባገኝ፤ ምን ያህል ደስ ባለኝ ነበር። ነገር ግን ፍርዱ የተሰጠው በቀጥታ ለባለጥቅሙ ታስቦ ስለሆነ፣ ለተበደለው መልስ መስጠት ያስፈልጋል ተብሎ እንደማይታሰብ አውቃለሁ።

...... እኛ በጣም ጥቂቶች የሆንን፣ የአንድ እጅ የጣት ቁጥሮች የማንሞላ አፍሪካውያን፤ በዛሬው ሰዓት ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ትክክለኛ ፍርድ እናገኛለን ብለን መጓጓት የለብንም። ጊዜው ያመቸው ለነ አርጀንቲና እና ለመሳሰሉት መሆኑን ማመን አለብን። ጊዜው ፈቅዶ የወንድሞቻችን የአፍሪካውያን ነፃነት ቁጥሩ በየጊዜው እየጨመረ፣ ከላቲኖች ሕብረት እጥፍ ሆኖ፣ አስተያየታችን የሚደመጥበት ዘመን እንደሚመጣ፣ ተስፋችንን ማጽናት ይኖርብናል። ይህን ዕድል እኛ ባንደርስበት ከእኛ ቀጥሎ የሚመጣው ትውልድ እንደሚጠቀምበት አንጠራጠርም። እስከዚያ ድረስ ግን፣ ከአንዱ ወገን ወደ ሌላው እየተገለባበጡ፣ የፈለጉትን ለመጥቀም፣ የፈለጉትን ለመበደል፣ ጊዜው የፈቀደላቸው ዛሬ እንድነታቸውን አጠንክረው፣ ከጣልያን ጋር ተሰልፈው፣ በድምፃቸው ኃይል ያጠቁን አገሮች ናቸው።

የመንግሥታት አባሎች ሆይ፣

በጣልያን መንግሥት ፍላጐትና ብርቱ ጥረት፣ በአርጀንቲናና በፓኪስታን ደራሲነት፣ ተቀምጥ የተዘጋጀላችሁን ውሳኔ አጽድቃችኋል። ....... የአገሬ ህዝብና ከፍተኛው ቅሬታዋ፣ በድጋሚ የመርማሪ ኮሚሽን ወደ ኤርትራ እንዲላክ መወሰኑ የሚያስጋት ሆኖ አይደለም። ኢትዮጵያ፣ ልጆቿ የሆኑት ኤርትራውያኖች፣ ዛሬም ሆነ ነገ፣ የኢትዮጵያዊነት ስሜታቸውንና የአንድነት ፍላጐታቸውን የበለጠ እንደሚያረጋግጡ አትጠራጠርም። ነገር ግን፣ የአገሬ ህዝብና ቅሬታዋ፣ የዛሬ አራት ዓመት ለሁላችንም ሚዛኑ እኩል የሆነ ዳኛ ተመሠረተልን ብለን፣ ተስፋችንን የጣልንበት ይህ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፣ እንደአለፈው የገኔቡ የመንግሥታት ማህበር፤ የጣልያን መሣሪያ ሆኖ፤ ጣልያን በሚፈልገው ዓይነት ፍርዱን ሲሰጥ በማየቷ ነው። ለዚህም ትልቁ ማስረጃ በተባበሩት መንግሥታት ስም ሆነው የኤርትራን ሕዝብ ፍላጐት እንዲመረምሩ የተሰየሙት የኮሚሲዮኑ አባሎች፤ ኢትዮጵያን ሲዘልፉና ሲቃወሙ ከሰነበቱት መካከል፣ እንደ ፓኪስታን የመሳሰሉት መሆናቸው ነው። ...... ከሁለት ባለጋራዎች መካከል፣

እንዱን መርጦ ለመርዳት የተሰለፈውንና የተሟገተውን፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ አድርጎ ሲሾመው የታየው፣ በክፍለ ዘመናችን ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው ብዬ ብናገር፣ ተሳስተሃል የሚለኝ እንደማይኖር እርግጠኛ ነኝ።

...... የተባበሩት መንግሥታት ድርጅታችን አሠራሩ፣ አሁን በተነገረው መልክ ትክክል ነው ከተባለ፤ ኢትዮጵያ አንድ ነገር ጉድሎ በጉልህ የሚታያት፣ ለኤርትራ ጉዳይ፣ ጣልያን የመርማሪው ኮሚሽን አባል ሆና አለመመረጧ ነው። በዚህ ደንብ መሠረት ከሆነ፣ እንዲያውም የኮሚሽኑ አባል ሆኖ መመደብ ብቻ ሳይሆን፣ የመልዕክተኞቹም መሪ መሆን የሚገባት ጣልያን ነበረች። በጨካኙ የፋሽዝም ዘመን፣ የሙሶሊኒ እንደራሴዎች ሆነው በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ግፍ የፈጸሙትና፣ ዛሬም አዲሲቷ ለተባለችው ጣልያን፣ ታላላቅ ባለሥልጣኖች ሆነው በዚህ ስብሰባችን ላይ ሳያፍሩ አብረውን የስነበቱት እነ ኤንሪኮ ቸሩሊ፣ ለምን ሳይመረጡ እንደቀሩ አልገባኝም። የጣልያን መንግሥት በሚፈልገው ዓይነት ለመርማሪው ኮሚሽን ሥራ አፈጻጸም፣ ከነ ቸሩሊ የተሻለ የፋሽስት ሊቃውንት ሊኖር አይችልም ነበር።

የተከበራችሁ መልዕክተኞች

ጣልያን ተመልሶ ሱማሌን ሲይዝ፣ የነገ ትልሙ ምን እንደሆነ፣ ኢትዮጵያ የስጋቸበትን ምክንያት ለመረዳት አልፈለጋችሁም። እንደዚሁም ለኤርትራ በድጋሚ መርማሪ ኮሚሽን እንዲላክ፣ በንዑስ ኮሚቴ 17 እና በዋናው ኮሚሲዮን የተደረገው ጥረት ሁሉ፣ ለጣልያን ፍላጐት ማስፈጸሚያ መሆኑን፣ ኢትዮጵያ ያቀረበችው ማሳሰቢያና ማስረጃ በቂ ሆኖ አልታያችሁም። ስለዚህ፣ በኤርትራም ሆነ በሱማሌ ጉዳይ፤ ድል የተሰጠው ለኮሎኒያሊስት ጣልያን ስለሆነ፣ « ዳቦ ለጠየቀ ድንጋይ » እንደተባለው፣ በደሉ የተጣለው በአገሬ በኢትዮጵያ ላይ መሆኑን እንድትረዱት እጠይቃለሁ።

---- የአራተኛው ዓመታዊ ጉባኤ ከተጀመረበት ካለፉት ሁለት ወራቶች ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ፣ ከየመንግሥታቱ እንደራሴዎች በየጊዜው የተሰጡትን አስተያየቶች በጥልቅ እናስታውሳቸዋለን።

---- ብዙዎቹ፣ በኤርትራ ጉዳይ የኢትዮጵያ ጥያቄ ትክክል ነው እያሉ በየዲስኩሮቻቸው ሲያረጋግጡ ከከረሙ በኋላ፣ አሁን በመጨረሻው በጣልያን ወገኖች የተዘጋጀውን ውሳኔ ለማጽደቅ ድምፃቸውን ሲሰጡ አይተናል።

---- አንዳንዶቹም አዲሲቷ ጣልያን ከእንግዲህ ወዲህ ኢትዮጵያን እንዳታጠቃ፣ የተባበሩት መንግሥታት እርምጃ ይወስዳል እያሉ፣ የቴዎሪ ዋስትና ሲሰነዝሩ ሰምተናል። እንደዚሁም ኢትዮጵያን ቀሚረዳ ይሆናል በማለት፣ በቂ ጥናት ያልተደረገበትና ያልበሰለ መፍትሔ በድንገት አቅርበው፣ ተቀባይ በማጣት አየር ላይ ተንጠልጥሎ ሲቀርባቸው ተመልክተናል።

---- ሌሎች ደግሞ ከልባቸው የሚደግፉት ኮሎኒያሊስት ጣልያንን መሆኑ የማይታወቅባቸው እየመሰላቸው፣ « አዲሲቷ ጣልያን » « አዲሲቷ ሬፑብሊክ » « አዲሲቷ ዴሞክራሲ » በሚል ቀለም እየቀባቡ፣ የተባበሩት መንግሥታት የኢትዮጵያን ጥያቄና የጣልያንን ጥቅም የሚያረካ መፍትሔ ማግኘት አለበት በማለት፤ የቅጥፈት ዲስኩር ሲናገሩ ሰምተናቸዋል።

---- ኢትዮጵያ የረዥም ዘመን መራራ የሆነ ኢክስፔሪያንስ ስለአላት፣ ጣልያን የመጠሪያ ስሟ ሲለዋወጥ፣ በታሪክ ላይ ጥቁር ሆኖ የተመዘገበው ግፈኛው ሥራዋ፣ በአዲስ ምዕራፍ ይሸፈናል እያሉ፣ ወገኖቿ የሚነዙላትን ከንቱ ዲስኩር አታዳምጥም። የድሮዋ ተባለች የዛሬይቷ ጣልያን፣ ኮሎኒያሊስቷ ሆነች ፋሽስቷ ጣልያን፣ ምን ጊዜም ጠላታችን መሆኗን ያስመሰከረች ስለሆነ፣ የሚደረግላትን የስም መለዋወጥ በቁም ነገር አትመለከተውም።

---- በዚህ ጉባኤ ላይ ከላቲን አሜሪካ አገሮች ጋር ሆነው፣ ጓደኞቸው ለሆነችው ለኮሎኒያሊስት ጣልያን ሲለፉ የሰነበቱት እነማን መሆናቸውን፣ ደህና አድርገን ተገንዝበናል። እነዚህ አገሮች፣ በጀርባ እየሰሩ ለኢትዮጵያ የሚያስቡ መስለው ለመታየት፣ ያደረጉትንም ሙከራ በትዝብት አተኩረን መዝግበናል። ...... ኢትዮጵያ ያለፉት ታሪኮቿ በትክክል እንዳስረዱት፣ ለነፃነቷና ለመብቷ፣ ከኮሎኒያሊስት ጣልያን ጋር በየጊዜው ስትዋጋ፣ ያሸነፈችው ብቻዋን ነው። የተጠ ቃችውም ብቻዋን ስለሆነ፣ አገሬ መቸውንም ለሚደርስባት አደጋ ከማንም እርዳታ አገኛለሁ ብላ አትጠብቅም። ዛሬም ሆነ ነገ ነፃነቷን ለመጠበቅ፣ ታሪኳን ለማስከበር አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረግ ያለባት፣ እሷ እራሷ ብቻ ነች። በዚህ አቋማችን የበለጠ እንድንጸና እና እንዳችም ተስፋ እንዳያሞኘን፣ ይህ የአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ስብሰባችን ደህና አድርጐ አስተምሮናል።

## የተከበራችሁ መልዕክተኞች

---- ዛሬ ከፊታችሁ ቀርቤ ስናገር የምታዩኝ፣ ከዛሬ አሥር ዓመታት በፊት ፈራርሶ የተበተነው የጌኔቩ የመንግሥታት ማህበር፣ በ1936 ዓ.ም የፋሽስት ተገን ሆኖ፣ በአገሬ ላይ የፈጸመውን የግፍ በደል፣ ከኢትዮጵያ መልዕክተኞች አንዱ ሆኜ ከፍተኛ ሀዘን በዋጠው ስሜት የተመለከትኩ ነኝ።

---- ከዚያም ወዲህ በ1945 ዓ.ም ይህ የተባበሩት መንግሥታት ሲመሠረት፣ የአገሬ መልዕክተኛ ሆኜ ለድርጅቱ አቋም በልዩ ልዩ ኮሚቴዎች በሥራ የተካፈልኩና፣ በመጨረሻም በኢትዮጵያ ስም ቻርቱን የፈረምኩ ነኝ። ....... በ1945 ዓ.ም፣ እንደዚያ ብዙ ተስፋ ያደረግንበትና የለፋንበት ድርጅታችን፣ ከአራት ዓመታት በኋላ፣ ዛሬ በአሠራሩና በዳኝነቱ የተቁላተ አቅጣጫ ይዞ፣ አገሬን ከፍ ያለ ቅሬታና ሀዘን ላይ ይጥላታል ብዬ አላስብኩም ነበር።

---- በጥንታዊው ዘመን የዳኝነት ሥራ የሚፈጸመው፣ የጌቶቹንና የኃያላኖቹን ፍላጐት ለማርካት ስለሆነ፣ ደካማን መበደል አስፈላጊ እንደነበረ፣ ታሪክ እያወገዘ አስተምሮናል። ዛሬ በአለንበት በሀያኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ፣ ሥልጣኔ ተስፋፍቶ ዲሞክራሲ ድል መታ እየተባለ በሚጨፈርበት ዘመን፣ ፍርድ የሚሰጠው ለኃያላኖቹ ጥቅም መሆኑ ካልቀረ፣ የዛሬው ዓለም ከጥንቱ የሚለየው በምን መልኩ ነው ? ብለን መጠየቅ ያስፈልገናል። ለዚህ ጥያቄ ተገቢው መልስ በቶሎ ተገኝቶ ካልታረመ፣ የዛሬው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅታችን እንደ አለፈው እንደ ጌኔቩ የዓለም ማህበር የመሰበር ዕድሉ ሰፊ መሆኑ መታወቅ አለበት።

---- በዚህ በአራተኛው ዓመታዊ ጉባኤያችን ላይ፣ ፍርድ እንዳይጓደልና በኢትዮጵያ ላይ በደል እንዳይደርስ ያለማቋረጥ የታገሉትን የመንግሥታት



ሱማሌ ለጣልያን እንድትመለስ፣ ኤርትራ ልዩ መርማሪ ኮሚሽን እንዲላክባት፣ ለሮማ መንግሥት ድሉን ያስገኙት፣ አርጀንቲናው ሆሴ አርሴና ፓኪስታኑ ዛፍሩላህ ካን ደስታቸውን ሲገላለጡ፤

(ኅዳር 21 ቀን 1949 ኒውዮርክ)
(ፎቶ U.N)

እንደራሴዎች፣ በተለይም የላይቤሪያን፣ የዩጐዝላቪያንና የፊሊፒንን መልዕክተኞች ከልብ አመሰግናለሁ:: እንዲሁም የኤርትራ ጉዳይ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ፣ የኢትዮጵያን ጥያቄ ተገቢነቱን በማመን ከፍተኛ ድጋፍ የሰጡንን የታላቋ ብሪታንያን መልዕክተኞች ላመሰግን እወዳለሁ:: ኢትዮጵያ በጣልያን ፋሽስት በተጠቃችበት ጊዜ፣ ከታላቋ ብሪታንያ መንግሥትና ሕዝብ፣ ነፃነቷን ለማስመለስ የተሰጣትን ከፍተኛ እርዳታ መቼውንም አትዘነጋውም::

የተከበራችሁ የመንግሥታት እንደራሴዎች፣

ንግግሬን የምፈጽመው በአንድ ቃል ነው:: ይኸውም ኢትዮጵያ ውሳኔያችሁን የምትቀበለው እጅግ ከፍ ባለ ቅሬታና ሙሉ መሆኑን እንድትረዱት ብቻ ነው:: ...... »

የአክሊሉ ሀብተወልድ የምሬትና የብስጭት ንግግር፣ ኢትዮጵያ በተባበሩት መንግሥታትና በምዕራባዊያኖች ዘንድ ያላትን ሆኖት ያጨለመች መሆኑን ያሳያል በማለት፣ የአሜሪካና የታላቋ ብሪታንያ የፖለቲካ ታዛቢዎች ገምተዋል:: የጣልያን ወገን መሆናቸውን ፊት ለፊት እያሳዩ፣ ኢትዮጵያን ሲያጠቁ የሰነበቱትን አገሮች ብቻ ሳይሆን፣ ወዳጅ መስለው ጠላት የሆኑትንም አንዳንድ መንግሥታቶች፣ አቶ አክሊሉ ከወቀሳው አልዘለሏቸውም:: የእነዚህን አገሮች ስም ባይዘረዝሩትም ትዝብታቸውን የወረወሩት እነማን ላይ እንደሆነ ለመረዳት አያስቸግርም::

...... ያልበሰለና የተፍረከረከ መፍትሔ አቅርቦ ተቀባይ በማጣት አየር ላይ ተንጠልጥሎ የቀረው፣ አሜሪካኖች ንዑስ ኮሚቴ 17 ላይ ያቀረቡት የፌዴሬሽን ፕላን መሆኑ ግልጽ ነው:: እንዲሁም ለኢትዮጵያ ወዳጅ መስለው እየታዩ ድጋፋቸውና ጥረታቸው ለጣልያን መሆኑ የተከሰተባቸው፣ ፈረንሣዮችና ቤልጂኮች ናቸው:: የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በንግግራቸው መጨረሻ ላይ፣ ለታላቋ ብሪታንያ ምሥጋና ሲሰጡ፣ አሜሪካኖችን በዝምታ በማለፋቸው፣ ለብዙዎቹ ተመልካቾች አስገራሚ ነገር ሆኖ ታይቷል:: በኒውዮርክ ያለው የእንግሊዝ ሚሲዮን ስለዚሁ ጉዳይ ለሎንዶን ሪፖርት ሲያደርግ
« ...... አክሊሉ ሀብተወልድ ለታላቋ ብሪታንያ የላቀ ምሥጋና ሰጥቶ አሜሪካኖችን የተዋቸው፣ ኢትዮጵያ የማትፈልገውን የፌዴሬሽን ሀሳብ በማቅረባቸው ምክንያት ነው:: ...... » ሲል አስተያየቱን ሰጥቷል::

አክሊሉ ሀብተወልድ በአሜሪካኖች ላይ ካሳደሩት ቅሬታዎች አንዱ፣ በቂ ምክክርና ዝግጅት ሳይደረግበት ለጉባኤው የቀረበው የፌዴሬሽን ፕላን ቢሆንም፣ ዋናው መሠረታዊው ጉዳይ፣ በላቲን አሜሪካ አገሮች ኦርኬስትራ የሮማ መንግሥት ኢትዮጵያን ሲበድል፣ አሜሪካኖች በቸልታ ተመልክተዋል በማለት ነው:: አዲሲቷ የተባለችው ጣልያን፣ ምዕራባዊነቷና የኔቶ ድርጅት አባልነቷ፣ ለአሜሪካኖች ትልቅ ቁም ነገር በመሆኑ፣ ዋሽንግተን፣ ኢትዮጵያን ከልቡ ለመርዳት አልፈለገም ብለው፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እጅግ አዝነዋል::

የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ግን፣ ምንም እንኳ ቀደም ሲል በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት ላይ የፈጸማቸው በደሎች የማይረሱ ቢሆኑም፣ በኤርትራ ጉዳይ የኢትዮጵያ ጥያቄ በከፊልም ቢሆን እንዲወሰን ድጋፉን በሚገባ ሰጥቷል::

ሄክቶር ሜክኒል የታላቋ ብሪታንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴታ ባደረገው ንግግር፣ ኢትዮጵያን የሚያረካ ውሳኔ ባለመደረጉ ያዘነ መሆኑን ከገለጸ በኋላ፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የመልዕክተኞች ቡድን ያሳየውን የተከበረ አቋም አመስግኗል:: ከዚህም አያይዞ፣ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለጠቅላላው ጉባኤ ያሰሙት የመረረ ቃል ከደረሰው ሁኔታ ጋር ስንመዝነው ሊያስደንቀን አይገባም ብሏል::

ከአክሊሉ ሀብተወልድ የመጨረሻ ንግግር በኋላ፣ አንዳንድ አገሮች እየተነሱ የኢትዮጵያ ቅሬታ ትክክል መሆኑን መቀበል አለብን የሚል ቃል ሲወረውሩ ይሰማ ነበር:: ሆኖም ፍርዱ ከተሰጠ በኋላ፣ እነዚህን የመሳሰሉት መልካም ቃላቶች የሚሰጡት ጥቅም እንደሌለ የታወቀ ነው::

ለኅ ኅዳር 21 ቀን 1949 ዓ.ም ከእኩለ ቀን በኋላ በአሥር ሰዓት፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በኤርትራና በሱማሌ ጉዳይ በሰጠው ውሳኔ፣ ኢትዮጵያ በከፍተኛ ቅሬታ፣ ጣልያን በጋለ ደስታ፣ የተባበሩት መንግሥታትን የስብሰባ አዳራሽ ለቅቀው ወጡ::

## በአዲስ አበባ እና በሮማ

ኅዳር 21 ቀን 1949 ዓ.ም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፣ ለኤርትራና ለሱማሌ ጉዳይ የሰጠው ውሳኔ ኢትዮጵያን እጅግ ያሣዘነ በመሆኑ፣ በአዲስ አበባ ከፍ ያለ ቁጣና ብስጭት ሲነፍስ፣ በሮማ ከተማ የአልቺዴ ደጋስፐሪ መንግሥትና ደጋፊዎቹ፣ ፍርዱ ትክክል ነው እያሉ በየአደባባዩ የፈንጠዝያ ከበሮ ሲደልቁ ሰነበቱ::

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በተደረገው ውሳኔ የተሰማቸውን ከፍተኛ ቅሬታ፣ ለመላው የተባበሩት መንግሥታት አባሎች በልዩ መልዕክት ሲያስገነዝቡ፣ የጣልያን ጠቅላይ ሚኒስትር ደግሞ በበኩሉ፣ አዲሲቷ ሬፑብሊክ ምንም እንኳን የአባልነት መብቷን ያልተቀበለች ብትሆንም፣ የተባበሩት መንግሥታት ባደረገው ውሳኔ፣ የተሰማትን ጥልቅ ደስታና በድርጅቱም ላይ ያላትን የጸና ዕምነት አሟሙቆ ገለጸ::

በአሜሪካ የጣልያን አምባሳደር አልቤርቶ ታርኪያኒ፣ ለጠቅላይ ሚኒስትር ደጋስፐሪ እና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኮምት ስፎርሳ፣ ከኒውዮርክ ወደ ሮም ባስተላለፈው የደስታ መግለጫ ቴሌግራም፣ «.... በዚህ በአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ፣ የተመኙት ሁሉ ያልተሳካላቸው ኢትዮጵያውያኖች ናቸው:: ከእንግሊዞች ጋር ተስማምተው ኤርትራን ለሁለት ለመካፈል ያደረጉት ዝግጅት ከሽፎባቸዋል:: ...... ከእንግዲህ ወዲህ አክሊሉ ሀብተወልድ በዚያ በሚያታክት ዲስኩሩ፣ በጣልያን ላይ የሚያወርደውን ስድብ ማቆም ይገደዳል ..... » ብሏል::

የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ በኒውዮርክ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ስለአደረገው ውሳኔ፣ ለንጉሠ ነገሥቱ በረዥም ቴሌግራም የላኩት ራፖር እንደደረሰ፣ የኢትዮጵያን አቋም ለመወሰን፣ ጃንሆይ በገነተ ልዑል ቤተመንግሥታቸው ከፍተኛ ስብሰባ አደረጉ:: ልዑል አልጋወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋወሰን፣ ልዑል መኰንን መስፍነ ሐረር ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ፣ ቢትወደድ

መኰንን እንዳልካቸው ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ራስ አበበ አረጋይ የአገር ግዛት ሚኒስትር፣ ጸሐፊ ትዕዛዝ ወልደጊዮርጊስ ወልደዮሐንስ የጽሕፈትና የፍርድ ሚኒስትር፣ አቶ ገብረወልድ እንግዳ ወርቅ የጽሕፈት ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር የስብሰባው ተካፋዮች ነበሩ:: ስብሰባው ሲጀመር፣ በቅድሚያ ከኒውዮርክ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ የላኩት ራፖር፣ ለጉባኤው እንዲገለጥና ከዚያ በኋላ አስተያየት ቢሰጥበት ይሻላል ሲሉ፣ የጽሕፈት ሚኒስትሩ ያቀረቡት ሀሳብ እንዲፈጸም፣ የንጉሠ ነገሥቱ መልካም ፈቃድ ሆነ::

« ...... የላቲን አሜሪካ፣ የዓረቦችና የእስያ አገሮች ለጥቅማቸው ሲሉ የጠላታችን የጣልያን ደጋፊዎች በመሆናቸውና በጉባኤው ላይ ከፍተኛ የድምፅ ብልጫ ስላላቸው፤ በመጨረሻ ስለ ኤርትራና ስለ ሱማሊ ጉዳይ የተሰጠው ውሳኔ ግርማዊነትዎ የሚደክምላትን ኢትዮጵያ በብዙ ረገድ አሳዝኗል ...... » ሲሉ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ በራፖራቸው መግቢያ ላይ የተሰማቸውን ከፍተኛ ሀዘን ገለጠ:: የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ከኒውዮርክ ባስተላለፉት ቴሌግራም ለጃንሆይ ያስረዱት ዋና ዋናዎቹ ነጥቦች የሚከተሉት ነበሩ::

1. ግርማዊነትዎ ገና ከመጀመሪያው እንደተመለከተው፣የዛሬው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እንደአለፈው የጄኔቭ የመንግሥታት ማህበር፣ ዳኝነቱን የሚያከናውነው ለኃይለኞችና ለብልጦኞች ጥቅም ስለሆነ፤ በአሁኑ ሰዓት ከዚህ ሸንጎ ትክክለኛ ፍርድ መጠበቅ አልተቻለም:: ዛሬ፣ የአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ የሰጠው ውሳኔ፣ ይህንን ደህና አድርጎ ያስገነዘበናል::

2. አብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ፤ከኢትዮጵያ ጋር አንድ መሆንን እንደፈለገ፣ በአራቱ ኃያላን መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን ከተረጋገጠ በኋላ፣ በድጋሚ እንደገና የጠላታችን ደጋፊዎች የሆኑ እንደ ፓኪስታን የመሳሰሉት ዳኞች፣ የሕዝቡን ሀሳብ ይመርምሩ ተብሎ ተወሰነ::

3. አብዛኛው የሱማሌ ሕዝብ፤ በሞግዚት መተዳደር አለባችሁ ከተባልን፣ ለማንም አገር ስጡን፤ ጣልያንን ግን እንዳታስገቡብን እያለ ሲወተውት፣ የሚያዳምጠው አጥቶ እንደገና በቀድሞ ጠላቱ እጅ እንዲወድቅ ተፈረደ::

4. አብዛኛው የሊቢያ ሕዝብ፤ ለነፃነቱም ሆነ ለአንድነቱ፣ ለወሬ የሚመች እንኳን እንቅስቃሴ ሳያደርግ፣ ዓረቦቹንና የእስላም አገሮችን ለማስደሰት ሲባል፣ ሶስቱም አውራጃዎች በአንድነት ተዋህደው ከሁለት ዓመት በኋላ ነፃነቱ እንዲሰጠው ተበየነ::

5. በስብሰባው ላይ ከዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ያገኘነው እርዳታ አጥጋቢ አለመሆኑን፣ በተለይ ደግሞ የፈረንሣይና የቤልጂክ አቋም እጅግ የሚያበሳጭ እንደነበረ ለግርማዊነትዎ የምገልጸው ከፍ ባለ የቅሬታ ስሜት ነው:: አሜሪካኖች ከልባቸው ሊረዱን ቢፈልጉ ኖሮ፣ የላቲን አሜሪካ አገሮች ከጣልያን ጋር ሆነው የሚያደርሱብንን ጥቃት ለማቆም ይችሉ ነበር:: ፈረንሣዮች ለጣልያን ሲሠሩ፣ አሜሪካኖች ችላ ሲሉን፣ ካለፉት ስድስት ወራቶች ጀምሮ በኤርትራ ጉዳይ የወሰዱትን አቋም፣ እስከ መጨረሻው ለማስፈጸም የሞከሩት እንግሊዞች በመሆናቸው፣ ስጉባኤው

ባሰማሁት የመጨረሻው ንግግር ላይ፣ የግርማዊነትዎን መንግሥት ምሥጋና አቅርቤላቸዋለሁ።

6. ወደ ኤርትራ መርማሪ ኮሚሽን እንዲላክ መደረጉ፤ጉዳዩን ለአንድ ዓመት ከማዘግየቱ በስተቀር፣ ዞሮ ዞሮ የኢትዮጵያ ጥያቄ እንደሚፈጸም የታወቀ ነው እያሉ፣ የአሜሪካና የፈረንሣይ መልዕክተኞች ሊያጽናኑን ሞክረዋል። እኔም የመረጣችኋቸው ዳኞች የሚሰጡትን ፍርድ በቅድሚያ ካወቃችሁት ግሩም ነው። ኢትዮጵያ ግን የሚፈረድባትን ሆነ ወይም የሚፈረድላትን ከዳኞቹ እስክምትሰማ ከመጠበቅ በስተቀር፤ የትንቢት አስተያየት መስጠት አትፈልግም ብያቸዋለሁ።

ግርማዊ ጃንሆይ፣

ብዙ የተደከመበትንና ብዙ የተጠበቀውን ተገቢ ፍርድ ባለማግኘታችን፣ በራሴና አብረውኝ በተሠለፉት የግርማዊነትዎ መልዕክተኞች ስም ሆኜ፣ የተሰማኝን ጥልቅ ሀዘን እገልጣለሁ። በተለይ በሱማሌ ጉዳይ የተደረገው ውሳኔ በዝምታ ሊታለፍ የማይገባ ስለሆነ፣ የግርማዊነትዎ ከፍተኛ የቅሬታ አስተያየት ለመላው የተባበሩት መንግሥታት አባሎች በአስቸኳይ እንዲላክ ዝቅ ብዬ በታላቅ ትህትና አሳስባለሁ። ....... »

ይህ ካቶ አክሊሉ የተላከው ራፖር ለጉባኤው ከተነበበ በኋላ፣ የመጀመሪያው ተናጋሪ ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ እንዲሆኑ ንጉሠ ነገሥቱ ፈቀዱ።

« ...... የኤርትራ ጥያቄ በዓለም ዳኞች ፊት ቀርቦ መታየት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ፣ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ያለእንዳች እረፍት ጉዳዩን ዕለት በዕለት በመከታተል፣ ምን ያህል እንደደከሙበት፣ የደረሱትን ችግሮች ሁሉ ምን ያህል እንደተቋቋሙት፣ በጠቅላላ አነጋገር ከመጥቀስ በስተቀር፤ ዝርዝሩን በመተንተን አንዘልቀውም።

...... አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ለግርማዊነትዎ እንዳመለከተው ሁሉ፣ የቱባበሩት መንግሥታት፣ ዳኝነቱን የሚያከናውነው ከፖለቲካና ከኤኮኖሚ ጥቅም ጋር እያይዞ ስለሆነ፣ ሕግን በተመረኮዘ ሀቅ፤ ፍርድ ሊገኝ የሚቻል አልሆነም። በዚህ አኳኋን ጠላታችን ጣልያን የላቲን አሜሪካ አገሮችን፣ ዓረቦችንና የእስላም መንግሥታቶችን በጥቅም እየደለለ ብዙ ወገኖች ስለተሰለፉለት፣ በዚህ በአራተኛው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ለውሳኔ በስሎ የቀረበውን የኤርትራን ጉዳይ አሰናክሎብናል። ከዚህም በላይ ይኸው ጠላታችን እንደገና ጐረቤታችን ሆኖ፣ የተለመደ ተንኮሉን ለማጥመድ እንዲመቸው ወደ ሱማሌ የመመለስ ዕድሉ ተቃንቶለታል። በዚህ ሁሉ ምክንያት በአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ስብሰባ ላይ ፍርዱ የተሳካለት ጣልያን በመሆኑ፣ በዓለም የፍርድ ሸንጐ ላይ ኢትዮጵያን አሸነፍኩ እያለ ጠላታችን በፕሮፓጋንዳ ቢሸልልብን አይገርመንም። ...... ይሁን እንጂ ግርማዊነትዎ በሚያምንበት ዓላማ የቆረጠ ስለሆነ፣ በዘመነ መንግሥትዎ እናትና ልጅ የሆኑት ኢትዮጵያና ኤርትራ፣ እቀድሞ ታሪካቸው ተመልሰው አንድ እንደሚሆኑ አንጠራጠርም። እንዲሁም በግርማዊነትዎ ታላቅ መሪነት የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነቱን

የበለጠ አጽንቶ፣ የጠላታችንን ጉርብትና ለመቋቋምና ነፃነታችንን ለመጠበቅ እንደምንችል እርግጠኞች ነን።

...... በዚህ በተመሳቀለው ዓለም ላይ፣ ትክክለኛ ፍርድን ማግኘት፣ መከራንና ችግርን መቋቋም፣ ለግርማዊነትዎ አዲስ ነገር አይደለም። አገራችንን ከፋሽስት ቀንበር ነፃ ለማድረግ፣ ቀጥሎም በፕሮቴክቶራ (PROTECTORA) አስተዳደር እንድንታሠር፣ የቃል ኪዳን ወዳጅ ከተባለ መንግሥት፣ ከተጐነጐነብን ክፉ ጠንቅ ለማላቀቅ የቻሉት፣ <u>በልዩው ትእግስትዎ እና በጠንካራው ዕምነትዎ ነው።</u> ስለዚህ ዛሬም ሆነ ነገ፣ አገራችን የሚደርስባትን ችግር ሁሉ ለመመከት የምንችለው፣ ይህንኑ የግርማዊነትዎን ዓላማና ቆራጥ መንፈስ በመከተል ስለሆነ፣ ለሥጋትና ለብስጭት ቦታ አንሰጠውም።

...... በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዘንድ የግርማዊነትዎን መምሪያና ከፍተኛ አደራ የተቀበለው የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ቡድን፣ በዓለም ጉባኤ ላይ ያሳየውን አስደናቂ የሆነ ያገር ፍቅር ተጋድሎ ጃንሆይ በየዕለቱ ተከታትለውታል። ቀደም ሲል እንደተገለጸው፣ ከዓለም ማህበር ሸንጐ ፍርድ የሚገኘው እውነትን በተከተለ መንገድ ቢሆን ኖሮ፣ የግርማዊነትዎ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ፣ ባለው የረቀቀ የሕግ ችሎታ ከጠላቶቻችን ጋር ያደረገው ያ ሁሉ ሙግት ድልን እንደሚያስገኝለት አይጠረጠርም ነበር። ምን ይሆናል ? ዳኝነቱ የሚካሄደው ለተለየ ግብ ስለሆነ፣ « እውነት » አሸናፊ እንዳይሆን፣ የኢትዮጵያ ጥያቄ ለጊዜው ተሰናክሎ እንዲዘገይና፣ የጣልያን ፍላጐት እንዲፈጸም ተደርጓል። ይሁን እንጂ ይህ በዚህ ሳምንት የተካሄደው የተባበሩት መንግሥታት ችሎት፣ ለኤርትራ ጉዳይ፣ ባለፈው ስብሰባው ስምምነት የተደረሰበትን ውሳኔ፣ አላጸድቅም ብሎ ሌላ እክል ፈጠረበት እንጂ፣ የመጨረሻ ፍርዱን አልሰጠም። ፍርዱ የሚሰጠው፣ መርማሪዎቹ ዳኞች ወደ ኤርትራ መጥተው የሕዝቡን አስተያየት ካዳመጡ በኋላ፣ በመጭው ዓመት ስለሆነ፣ እኛም ሌት ተቀን መሥራትና መጠንከር ያለብን በዚሁ ጊዜ ውስጥ ነው። ...... በመጨረሻም የግርማዊነትዎን መልካም ፈቃድና ትዕዛዝ የምለምነው፣

1ኛ/ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ባቀረበው ሀሳብ መሠረት፣ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባሎች ከጃንሆይ የሚላክላቸው ልዩ መልዕክት በአስቸኳይ እንዲተላለፍ፣

2ኛ/ በአገር ውስጥና በውጭ አገር በቅደም ተከተል ለሚፈጸመው ተግባር፣ ፕሮግራሙን የጽሕፈትና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች አዘጋጅተው፣ በአስቸኳይ ሥራው እንዲጀመር አስፈላጊ መሆኑን በታላቅ ትህትና አሳስባለሁ። ...... »

በጃንሆይ ሰብሳቢነት የሚካሄደው ጉባኤ ሥራውን ሲጀምር ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ የሰጡት ማብራሪያ ሁለት ዓይነት ግብ እንዳለው በትክክል ያሳያል። የመጀመሪያው፣ በኒውዮርክ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ቡድን፣ በተለይም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ያደረጓቸው ጥረቶች እንከን እንደማይገኝባቸው ለማስገንዘብ ነው። ሁለተኛው ደግሞ፣ በኤርትራ ጉዳይ፣ ከጽሕፈትና ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች በስተቀር የጠቅላይ ሚኒስትሩም ሆነ የአገር ግዛት ሚኒስትሩ እጅ እንዳይገባበት በሩን ለመዝጋት ነው። ከጽሕፈት ሚኒስትሩ መግለጫ በኋላ፣ በስብሰባው ተካፋይ

የሆኑት ታላላቅ ሰዎች፤ አስተያየታቸውን እንዲያቀርቡ የንጉሠ ነገሥቱ መልካም ፈቃድ ስለሆነ፣ የመጀመሪያው ተናጋሪ ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ ሆኑ።

« ...... አሁን ከሁሉም በኩል እንደሰማነው፣ ከዓለም ማህበር የተደረገብን ውሳኔ በጣም የሚያሳዝን ነው። ይኸ ትልቅ የተባለ ማህበር፤ በአገራችን ላይ በደል እየሠራ ጠላታችንን ጣልያንን ይጠቅማል ተብሎ አይታሰብም ነበር። ነገሩ እንደዚህ ከሆነ ማህበርተኛነታችን የሚጠቅመን ለምኑ ነው ? ...... ማለት የተገባ ይሆናል። የሀማሴን ሕዝብ፤ መሠረቱም ታሪኩም ኢትዮጵያ መሆኑ የታወቀ ነው። ሀማሴኖች ለብዙ ዘመን ጣልያን ቢገዛቸውም፣ የታላላቅ መንግሥታት ዳኞች አገራቸው ድረስ መጥተው ሲያነጋግሯቸው « ኢትዮጵያ ነን » ብለው መቆማቸውን ሰምተናል። እንግዲህ ይኸ ሁሉ ከሆነ በኋላ፣ የታላላቆቹ ዳኝነት የማይበቃ ሆኖ ሌሎች ከያለበት የተለቃቀሙ ዳኞች፣ ጥያቄች ሳይቀሩ፣ ነገሩን እንደገና ይመርምሩት ተብሎ መፈረዱ፣ የዓለም ማህበር ከኛ ወገን አለመሆኑን ያረጋግጥልናል። ...... አሁን ለዚህ ምን ይበጃል ? ብለን ብናስብ፣ ጸሐፊ ትእዛዝም እንደተናገረው እነዚህን ተመርጠዋል የተባሉትን ዳኞች፣ በወግ ከመቀበል በስተቀር ሌላ ነገር ማድረግ አይቻልም። ሁለተኛም ጠላታችን ጣልያን ወደ መቅደሾ (ሱማሌ) እንዲመለስ የተፈረደውን በይግባኝም ለማስለወጥ አልተቻለም ተብሏል። ሆኖም ጠላታችን ጣልያን፣ ከድንበራችን አጠገብ የሚሰፍረው ለጦርነት መሆኑን ዓለም እንዲሰማው ማድረግ ይሻላል የተባለውን ሀሳብ በቶሎ መፈጸም ያስፈልጋል። ሌላው መጨመር ያለበት፣ በዛሬው ሰዓት ከኦጋዴን ግዛታችን ብዙው ክፍል በእንግሊዞች እጅ እንዲቆይ የተደረገ ስለሆነ፣ እነሱም ወዳጆቻችን ስለሆኑ፣ በወሰናችን ላይ ጣልያኖች የሚያደርጉብንን ሁሉ እየተከታተሉ እንዲነግሩን አደራውን ማጥበቅ የተገባ ነው።

...... መቼም ይኸ « ኤርትራ » የተባለው ነገር አንድ ጊዜ ተዠምሯል። የተዠመረ ነገር እጫፍ እስኪደርስ መቀጠል አለበት። ስለዚህ፣ የሀማሴኑ ሕዝብ ሌላ ዳኛ ከዓለም ማህበር የተላከበት መሆኑን አውቆ እንዲጠብቅ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ከዚህ ሌላ የሚታየኝ ነገር የለም።.... »

## ጠቅላይ ሚኒስትር ቢትወደድ መኰንን

« ...... ከጦርነቱ ፍጻሜ ጀምሮ፤ በኤርትራና በሱማሌ ጉዳይ ግርማዊነትዎ ያደረገው ያልተቆጠበ ጥረት፣ ምን ያህል አስቸጋሪና ምን ያህል አድካሚ እንደሆነ ሁላችንም በቅርብ ሆነን ያየነው ነው። ከግርማዊነትዎ ተመርጠው ከፍተኛ መምሪያና ኃላፊነት ተሰጥቷቸው የተላኩት መልዕክተኞችም፣ በማይጠረጠር ብዙ ደክመውበታል። የዚህ የመጨረሻው ስብሰባ ውጤት የሚያሳዝንና የሚያስገርም ቢሆንም፣ ተስፋ አያስቆርጥም። ከእንግዲህ፤ ሁላችንም በምን አኳኋን ጥረት ማድረግና መሥራት እንደሚያስፈልገን ጃንሆይ ውሳኔውንና መምሪያውን እንዲሰጡን እንጠብቃለን። ....... በተጨማሪ ለማስታወስ የምፈልገው፣ ልዑል ራስ ካሣ ስለተናገሩት በኦጋዴን በኩል ስለአለው ስለ እንግሊዞች ጉዳይ ነው። ጣልያኖች በኦጋዴን በኩል እንግሊዞችን እታልለው በዚያ ስፈር ድንበር እያለፉ ግዛት ለማስፋፋት፣ ከዚያም አልፎ ኢትዮጵያን ለማጥቃት መሞከራቸው እንደማይቀር የታወቀ ነው። በአውሮፓ አቆጣጠር በ1885 ዓ.ም፣ ጣልያኖች መጀመሪያ ምፅዋን ለመያዝ የቻሉት ከዚያም ቀስ በቀስ ወደ መላው ኤርትራ የዘለቁት፣ የእንግሊዞችን ድጋፍና ወዳጅነት ይዘው ነው። አሁንም ይህን የመሰለው ታሪክ በሌላ አኳኋን

እንዳይደገም፣ በግርማዊነትዎ ጥረት እንግሊዞች እንደሚረዱን ተስፋ እናደርጋለን:: ...... ቀደም ሲል ጸሐፊ ትእዛዝ እንደተናገረው፣ ለኤርትራ ጉዳይ ከዛሬ ጀምሮ ለሚሠራው ሥራ ፕሮግራም ማዘጋጀቱ የተገባ ነው:: ይኸ የሚዘጋጀው ፕሮግራም ግን፣ በጽሕፈትና በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ብቻ ሳይወሰን ሁላችንም የምንካፈልበት እንዲሆን ያስፈልጋል:: ሁሉም በየበኩሉ ኃላፊነት ተቀብሎ ድርሻውን ከፈጸመ ውጤቱ ሊያምር ይችላል:: .... »

ራስ አበበ አረጋይ ያገር ግዛት ሚኒስትር

« ...... ከእኔ በኩል የሚጨመር ነገር ቢኖር ብዙም ጥቂት ነው:: እሱም ከዚህ ቀደም ያልታሰበበት ነው ለማለት አይደለም:: በዚህ በዓለም ማህበር በኩል የተወሰነውን የኤርትራ አገር ሕዝብ እንዲስማና፣ መርማሪዎቹ ዳኞቹም በሚመለሱበት ጊዜ የሚሆነውን ሁሉ ተዘጋጅቶ እንዲጠብቅ ያስፈልጋል:: መቼም ሀማሴኖች ከዚህ ቀደም ሊመረምሯቸው የመጡትን የታላላቅ መንግሥታት ዳኞች በመቀበልም፣ ስለ ኢትዮጵያዊነት የተባለውንም በመግለጽ፣ ልምድ ስለወሰዱ፣ አሁን ለሁለተኛ ጊዜ ሥራው ሊደናገራቸው አይችልም:: ቅድም እንደተነገረው፣ ይህን ለመሰለ ትላቅ የፖለቲካ ሥራ መድሀኒቱ ትዕግሥት ነው ቢባልም፣ ከዚሁ ጋራ በቆረጠ መንፈስ ታጥቆ ካልተሠራ ትዕግሥት ብቻውን ፍሬ ሊያመጣ አይችልም:: እስካሁን የጃንሆይ ድካም ስፊ ስለሆነ፣ የወደፊቱም ሥራ ድካም ሳይጫነው በደህና እንዲፈጸም፣ ለየሚኒስቴሩ የኃላፊነት ድርሻውን እየለዩ በአደራ መስጠት ይጠቅማል:: በተለይም ዳኞቹ በሚመጡበት ጊዜ፣ በኰሎኔል ነጋ ኃይለሥላሴ (ሳይዘን አፊሰር) ላይ የሚወድቀው ሥራ እና ኃላፊነት ከባድ ስለሆነ፣ በሥራ ረዳቶችም ሆነ በማናቸውም ጉዳይ፣ ከአሁኑ እንዲታሰብለት ያስፈልጋል:: በተረፈ ሁሉም የተነገረ ስለሆነ፣ በእኔ በኩል ሌላ የሚጨመር ነገር የለም:: ...... »

የጃንሆይ ውሳኔ

« ....... ሁላችሁም በየበኩላችሁ ከተናገራችሁት ውስጥ፣ እንዳንድ የሚለቀም ፍሬ ነገር አለ:: ራስ ካሣ እንዳልከው ጣልያን ወደ ሱማሌ እንዲመለስ ስለተደረገ፣ ኦጋዴን የሚገኘው የቃል ኪዳን ወዳጃችን የታላቋ ብሪታንያ ጦር፣ ማናቸውንም የጠላት ተንኮል እንዲከታተልልን እንጠይቃለን:: በዚህ በኩል የተናገርከው ከእኛም ሀሳብ ጋር የሚገጣጠም በመሆኑ ደስ ተሰኝተናል::

...... የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ስለ ኤርትራ ውሳኔውን በሰጠ ጊዜ፣ አክሊሉ ሀብተወልድ የመጨረሻውን ንግግር ሲያደርግ፣ ምንም እንኳን አሜሪካንን ነጥሎ ማስቀረቱ የተገባ ባይሆንም፣ የወዳጃችንን የታላቋ ብሪታንያን መንግሥት በእኛ ስም ሆኖ ማመስገኑ ማለፊያ ሠርቷል:: ስዚህም በኦጋዴን በኩል ለምናስበው ጉዳይ የሚረዳን ይሆናል:: ....... ስለ ኤርትራ ዋና ጉዳያችን የምናዝነው፣ ለብዙ ጊዜ የደከምንበት ጉዳይ ካለቀ በኋላ፣ የተባበሩት መንግሥታት እንደገና ይመርመር ብሎ ውሳኔውን ስለአዘገየብን ነው እንጂ፣ ኤርትራን እንድናጣት ፈርዶብናል ብለን አይደለም:: ሁላችሁም ጨረፍ አድርጋችሁ ተናግራችሁታል:: አሁን እኛ ተነስተን በተባበሩት መንግሥታት የተወሰነውን አሻፈረን እንቀበልም ብንል፣ ተጠቃሚው ጠላታችን ጣልያን እንጂ እኛ አይደለንም:: ስለዚህ ምንም እንኳ

ፍርዱ በአድልዎ መፈጸሙን በትክክል ብናውቀውም፣ አክሊሉ ለጉባኤው እንዳስረዳው፣ በምር ሀዘናችንን ከመግለጽ በስተቀር ሌላ ማድረግ አንችልም።

...... ቀደም ሲል ራስ ካሣ ተናግረኸዋል። የኤርትራን ሕዝብ ለመመርመር ከያለበት የተለቀሙት ዳኞች ሲመጡ፣ ምንም እንኳን የጠላታችን ወገኖች መሆናቸውን ብናውቅም፣ ከእኛ በኩል ግልፊያ አቀባበል ማድረግና የሚጠይቁትን መመለስ የተገባ ነው። ሁለተኛም በሉግሌ ጉዳይ አክሊሉ እንዳመለከተን፣ በተደረገው ውሳኔ እኛ የተሰማንን ከፍተኛ ቅሬታ ለዓለም መንግሥታት መሪዎች፣ በአስቸኳይ እንዲነገራቸው አስፈላጊውን ማድረግ ነው።

...... መቼም ሁላችሁም ዛሬ ያለንበትን ከባድ ችግር ተረድታችሁታል። በእኛም በኩል ደህና አድርጋችሁ እንድታውቁት የምንፈልገው አንዳንድ ነገር አለ። ...... ከሁሉ በፊት እንድታውቁት የሚያስፈልገውም ይኸንን የኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ መመለስ ዋና ጉዳይ አድርገን ስንዠምረው፣ እስከ መጨረሻው ድረስ ለመድከምና ከግፍ ለማድረስ ቆርጠን የተነሳንበት ነው እንጂ፣ እንቅፋት ሲያጋጥመን ማሀል ላይ ለመቆም ሀሳባችን አለመሆኑን ነው። ኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ቆርጠን ከተነሳንበት ዋናው ጉዳይ አንዱ፣ ከኮሎኒያሊስት የተወሰደብን ግዛታችን ለዘለዓለሙ በባዕድ እጅ ተይዞ፣ ታሪካችንም ተቆርጦ እንዳይቀር ብለን ስለሆነ፣ የዠመርነውን እስከ ግፍ እንደምናዘልቀው የተረጋገጠ ነው።

...... አበበ አረጋይ በተናገርከው ውስጥ፣ ለዚህ ወደፊት ለሚጠብቀን ከባድ ሥራ የትዕግሥት መሣሪያነቱ የታመነ ቢሆንም፣ ቆራጥነት ከሌለ ትዕግሥት ብቻውን ድል እንደማይመታ ከጥንት የበለጠ የምናውቀው ስለሆነ፣ በዚህ በኩል የተጨነቅክበት ነገር አስፈላጊ አይሆንም። ...... በዓለም ጉባኤ የተወሰነብንን፣ የኤርትራ ሰዎች በቶሉ እንዲያውቁት ያልከውም ቀደም ብሎ ታስቦበት አስፈላጊው ተደርጓል። አሥመራ ያለው ሳይዘን አፈሰራችን ነጋ ኃይለሥላሴ እንደነገረን፣ የተባበሩት መንግሥታት መርማሪ ዳኞች እንዲመጡ መደረጉን፣ የኤርትራ ዋና ዋና ሰዎች በደስታ መቀበላቸውን አረጋግጠልናል። በደስታ ይቀበላሉ የተባለውም፣ የኤርትራ ሕዝብ ከልቡ ኢትዮጵያዊ መሆኑን ዳኞቹ በበለጠ እንዲረዱት ለመደራጀት ይመቻል በማለት መሆኑን ነጋ ኃይለሥላሴ ገልጾልናል። እኛም እንደምንገምተው፣ የኤርትራ ሕዝባችን ምንም የጠላታችን ተንኮል ቢበዛበትና የውጭ እጅ እየገባ ቢያስቸግረውም ኢትዮጵያዊነቱን ያስከድዋል ብለን አናስብም። ...... ወልደጊዮርጊስም፣ ገብረመስቀል ሀብተማርያምንና አስፍሐ ወልደሚካኤልን አነጋግሮ የእነሱም ሀሳብ ከነጋ ኃይለሥላሴ ጋር የሚስማማ ሆኖ አግኝቶታል። ...... ዳኞቹ በሚመጡ ጊዜ፣ ነጋ ኃይለሥላሴ ላይ ስለሚወድቀው ከባድ ሥራ ተጠቅሷል። ነጋን ለዚያ ቦታ መርጠን የሾምነው እኛው ራሳችን ስለሆንን፣ የጣልንበትን ኃላፊነት ደህና አድርገን እናውቀዋለን። ዳኞቹም ሲመጡ ሥራው ስለሚጨምር፣ በሠራተኛም ሆነ በሌላ በኩል የሚቸገርበት ነገር ካለ፣ ነጋ ራሱ ለእኛ በቀጥታ ማመልከት ይገባዋል።

...... በዚህ በኤርትራ ዋና ጉዳያችን ወደፊት ለሚጠብቀን ከባድ ሥራ የእያንዳንዱ የኃላፊነት ድርሻ እየተለየ እንዲሰጥ፣ መኰንን እንዳልካቸውና አበበ አረጋይ፣ ሀሳባችሁን አስማምታችሁ ጠይቃችኋል። ...... በእኛ በኩል ይኸ ጥያቄ በዚህ ስብሰባ ለምን እንደተነሳ አስፈላጊነቱ አልታየንም። ሆኖም እስካሁን ስንሠራ እንደቆየነው፣ ማናቸውም ጉዳይ የሚካሄደው በእኛ መሪነት ስለሆነ፣ ችግር

አጋጥሞን አያውቅም:: በየዕለቱ ለምንደክምባቸው ሥራዎች እንደ አስፈላጊነቱ በጽሕፈት ሚኒስትራችን በኩል ትእዛዝ ስለምንሰጥ፣ እናንተንም የሚመለከተው ነገር አይጐድልባችሁም::

...... ወልደጊዮርጊስ እንደተናገርከው ለተባበሩት መንግሥታት ዋና መላክተኞችን አድርገን ከፍተኛ አደራና እምነት የጣልንበት አክሊሉ ሀብተወልድ፣ ከእሱም ጋር አብረውት የተላኩት ኤፍሬም ተወልደመድህንና ተሰፋዬ ተገኝ፤ እንዲሁም ሌሎቹም ምን ያህል በብርቱ እንደደከሙ እናውቃለን:: የሰጠነውን መምሪያ በሚገባ ተከትሎ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራችን ይኸ ቀረ በማይባል አኳኋን፣ በዓለም ጉባኤ ፊት በሰፊው ተከራክሮበታል:: አንዳንድ መንግሥቶች የኤርትራ ጉዳያችን እንዲሰናከል የሚያቀርቧቸውን የተንኮል ጥያቄዎች በሚገባ በመመለስ፣ በተለይም ከጠላታችን ከጣልያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጋር፣ ሳይታክት ፊት ለፊት ተሟግቶ ዝም በማሰኘት በሥራው ሁሉ ተደስተናል:: ጠቅላላው ጉባኤም ያልተገባውን ውሳኔ ሲያጸድቅብን፣ አክሊሉ ያደረገው ንግግር የኛን ሀሣብ ደህና አድርጐ የተከተለ በመሆኑ ግልፅ አድርጓል:: ለወደፊቱም ይኸው የመልዕክተኞቻችን የጠነከረ መንፈስ እንዲቀጥልና የድካማችንን ውጤት ፊጣሪያችን እንዲባርክልን አጥብቀን እንለምነዋለን:: ...... »

ከዚህ በላይ እንደታየው በጃንሆይ የማጠቃለያ ንግግር የተገለጹት ሁሉ፣ በስብሰባው ላይ ለቀረቡት ሀሳቦች መልሱን የሚሰጡ ናቸው:: በተለይ ራስ ካሣ በሰጡት አስተያየት፣ « ....... መቼም ይኸ የኤርትራ ጉዳይ አንድ ጊዜ ተጀምሯል:: የተጀመረ ነገር እጫፍ እስኪደርስ መቀጠል አለበት::... » ሲሉ የወረወሩት ቃል የተለየ ትርጉም ያለው መሆኑን ያልፉት አንዳንድ ሁኔታዎች ያመለክታሉ:: ንጉሠ ነገሥቱም የወንድም ጓደኛቸው መሠረታዊ አስተያየት ምን እንደሆነ ከማንም የበለጠ ስለሚያውቁ፣ የኤርትራን ጉዳይ ስንጀምረው እጫፍ ለማድረስ ቆርጠን ስለሆነ፣ እንቅፋት በገጠመን ቁጥር ማህል ላይ ለማቆም አናስብም የሚል መልስ ሰጥተዋል::

ገና ከጠዋቱ፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ክስደት እንደተመለሱ፣ ኤርትራና ሱማሌን ወደ ኢትዮጵያ ለማቀላቀል የመጀመሪያው ሥራዬ ነው ብለው በተነሱ ጊዜ፤ ራስ ካሣ እነዚህ ጉዳዮች ቅድሚያ የሚሰጣቸው ሆነው አልታዩዋቸውም:: ራስ ካሣ የሚያስቡትን ለጃንሆይ አልደበቁም:: አስተያየታቸውም የተመረከዘው በሚከተሉት ነጥቦች ላይ እንደነበረ ይነገራል::

...... ጥንታዊ ታሪክንና የግዛት ድንበርን እነበረበት ለመመለስ ብርቱ ጥረት ማድረግ ተገቢ ቢሆንም፣ ለአገር ጥቅም ለሚታሰቡት ሥራዎች ሁሉ ቅደም ተከተል መስጠት ያስፈልጋል:: በጠላት ወረራ ምክንያት የተለየነው አገርና ሕዝብ፣ ከአምስት ዓመት በኋላ ስንመለስ ያገኘነው፣ መልኩንና አኳኋኑን ለውጦ ነው:: በተለይ ይኸ በአርበኝነት ጫካ ሳይገባ፣ ለስደት እውጭ ሳይወጣ የኖረው ሕዝብ፣ በጣልያን የአስተዳደር ዘመን ድሮ ያላየውን ከልማዱ ውጭ የሆነ አንዳንድ ነገሮችን ቀምሷል:: አሁን አፍ አውጥቶ አይናገረው እንጂ፣ በአስተዳደር በኩል ቢሆን፣ በዳኝነትና በኑሮም አኳኋን ቢሆን፣ በጣልያን ዘመን ለእኔ የሚጠቅም ነገር ነበር ብሎ፤ በልቡ የሚያስብ ብዙ ሰው መኖሩ የማይታበል ነው:: አሁን እንደምናየው፣ ከእንግዲህ ወዲህ የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደ ጥንቱ አንድ አድርጐ፣ በሥልጣን ለመግዛት ብዙ ችግር መኖሩ የሚካድ አይደለም:: ...... በዚህ ሁሉ ነገር ላይ፣ በአለንበት በአሁኑ ሰዓት የመንግሥት ዋና የመጀመሪያ ሥራ መሆን ያለበት፣

1ኛ/ በጠላት ምክንያት የተበላሸውን ያገር ልማድና አስተዳደር አቦታው መመለስ፣

2ኛ/ የአገሩ አንድነትና የንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣን እንዳይናጋ፣ መሠረት እንዲጨብጥ ማድረግ፣

3ኛ/ ጻኝነት ሳይጓደል ክርስቲያንነትንና ሥርዓትን ማጥበቅ፣

4ኛ/ ሕዝቡን ማሠራትና የአገሩ ሀብት እንዲዳብር ማድረግ ነው::

...... አሁን በእጃችን ያለው የኢትዮጵያ ግዛትና ሕዝብ፣ አንድነቱ በማይላላ አኳኋን ሲጠበቅ፣ በአንድ ንጉሠ ነገሥት ሥልጣንና በአንድ ሰንደቅ ዓላማ ከጫፍ እስከ ጫፍ በትክክል የሚገዛ መሆኑ ሲረጋገጥ፣ አገሩም ለምቶ ጥጋብ ሆኖ፣ የመንግሥቱ ቋት ሲሞላ፣ በመጀመሪያ ሀማሴኖች፣ ቀጥሎም እንደ አኳኋኑ ታይቶ ሱማሌዎች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ መጠየቅ፣ ወይም እነሱ እንምጣ ቢሉ መቀበል፣ የተገባ ነው:: እንደዚህ ከሆነ፣ መንግሥትም አገሮቹን ተረክቦ ለማስተዳደር፣ ሕዝባችንም የጥንት ወንድሞቹንና ወገኖቹን ተቀብሎ ለማላመድ የሚከብድ አይሆንም:: ይኸ ሁሉ ሳይደራጅና በተለየም የአገሩ ሀብት ሳይዳብር፣ ግዛት ቢሰፋ፣ የሕዝብ ቁጥር ቢጨምር፣ አሁን ያለውን ችግር የበለጠ ከማባባስ በስተቀር የሚጠቅም ነገር የለም:: ....... እየተደጋገመ የሚነገረው፣ ኢትዮጵያ፣ የፈረንጆቹን ሥልጣኔ ፀቶሎ ለማግኘት ያልቻለችው፣ በባሕር በር እጦት ምክንያት ነው እየተባለ ነው:: ሕዝባችንን ለማሠልጠን ዋና ቁልፉ የባሕር በር ከሆነ፣ በእንግሊዞች እርዳታ፣ አሰብ ከወሎ ጋር እንዲሆን ለምን ከአሁኑ አይደከምበትም ? ...... አሁን ባለው ችግር ላይ ሌላ፣ ተጨማሪ የአስተዳደር ጣጣ ለመሸከም ከመቸከል፣ ይኸ ሁሉ በእርጋታ ቢታሰብበት ይሻላል:: .... »

ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው የራስ ካሣ ሀሳብ በአፍ ታሪክ እንደሚነገረው «ኤርትራውያኖች ለኢትዮጵያ ጠንቀኞችና መርዘኞች ስለሆኑ እዚያው አሉበት ይቅሩ» የሚል አልነበረም:: የመስፍኑ አስተያየት ባጭሩ ሲጠቃለል፣ የአገራችን አስተዳደር ሳይጠነክር፣ የመንግሥት ሀብት ሳይዳብር፣ ተለያይተው የኖሩትን ሕዝቦች ለመሰብሰብ መቸኮል እያስፈልግም የሚል ነው:: እርግጥ፣ በዚህ አመለካከት የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት ኤርትራን ለማስመለስ መሥራት ያለበት፣ ኢትዮጵያ ከበለጸገችና የአስተዳደር ኃይሏም ከጠነከረ በኋላ ነው ከተባለ፣ እስከዚያ ድረስ፣ ወንድሞቻችን ኤርትራውያኖች በማን እጅ ተይዘው እንደሚቆዩ የተሰጠ ሀሳብ የለም:: ታሪኩ እንደሚያሳየው፣ በዚያን ዘመን በጣም አብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ ኢትዮጵያዊነቱን ለማግኘት ቁርጠ የተነሣ ነው:: በዚያን ጊዜ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት የዚህን ሕዝብ ስሜት በማጋል ፋንታ ችላ ቢል ኖሮ፣ ኤርትራ ተመልሳ የጣልያን ክሎኒ እንደምትሆን ጥርጥር አልነበረውም:: እንዲሁም በዚያን ሰዓት ጠላታችን ጣልያን፣ ኢትዮጵያን የሚያህል ጠንካራ ታጋይ ባይገጥማት ኖሮ፣ ኤርትራን መልሶ የመያዝ ዕድሏ የተረጋገጠ ይሆንላት ነበር:: ስለዚህ፣ ማናቸውም ጉዳይ መመዘንና መታየት ያለበት በዘመኑ ካለው የፖለቲካ ሁኔታ ጋር ነው::

የራስ ካሣ ሥጋት፣ ምንም እንኳ ቤቱ ሳይሰናዳ፣ ጓዳው ሳይሟላ፣ የጥንት ተወላጆችን ለመሰብሰብ መጣደፍ አያስፈልግም የሚል ቢሆንም፣ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በኩል ደግሞ፣ ቤተዘመዱ እንደገና ለጠላት ተሰጥቶ፣ አገሩ የጠላት

ጦር ማደራጃ እንዳይሆን፣ ባለው አቅም ተሟግቶ ማስጣልና፣ ስብሰቦ መያዝ ያስፈልግ ነበር። እንደ እውነቱም ከሆነ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት፣ የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተፈጽሞ የሠላም ድርድር ሲደረግ፣ ወዲያውኑ የኤርትራን ጥያቄ ማቅረቡ ትክክል ብቻ ሳይሆን ግዴታውም ጭምር ነበር። ራስ ካሣ ኃይሉ የኤርትራ ጉዳይ ሲጀመር አስተያየታቸውን እንደገለጡት ሁሉ፣ በአፈጻጸሙም ላይ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር የምትቀላቀለው « ፌዴሬሽን » በተባለ የአስተዳደር ሥርዓት በመሆኑ፣ ያላቸውን ቅሬታ አልሸሸጉም።

በዚህ በገነተ ልዑል ቤተመንግሥት ታላቅ ስብሰባ ላይ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩና የአገር ግዛት ሚኒስትሩ፣ በኤርትራ ጉዳይ ለሚከናወኑት ሥራዎች፣ የየሚኒስትሩ የኃላፊነት ድርሻ እየተለየ እንዲሰጥ ያቀረቡት ሀሳብ፣ ንጉሠ ነገሥቱን ያልጣማቸው መሆኑን በማጠቃለያ ንግግራቸው አስምተዋል። በመሠረቱ የቢትወደድ መኩንን እና የራስ አበበ ሙከራ፣ ሌላው ቢቀር በአገር ውስጥ የሚሠራው የኤርትራ ጉዳይ፣ በሙሉ ተጠቃልሎ ከተያዘበት ከጽሕፈት ሚኒስትሩ እጅ በመጠኑም ቢሆን ተቀንሶ፣ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እና ለአገር ግዛት ሚኒስትሩ እንዲሰጥ ለማስደረግ ነበር። ነገር ግን አፈሬ ወልጊዮርጊስ በእጃቸው ያለውን ሥልጣን፣ እንኳንስ ለማካፈል ይቅርና፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እና አገር ግዛት ሚኒስትሩ ዘንድ ቢኖር እንኳ፣ ካጋጠማቸው ለመውሰድ የማይመለሱ ስለሆነ፣ የተደረገው ሙከራ ውጤት አለመስጠቱ አያስደንቅም።

የአገር ግዛት ሚኒስትሩ ሲናገሩ በሰጡት አስተያየት፣ የንጉሠ ነገሥቱን ትዕግሥት በማድነቅ ብቻ ሥራው ካልተሠራ፣ ትዕግሥት ብቻውን ጀግና ሆኖ አያሸንፍም የሚል ስሜት በጃንሆይ ላይ አሳድሮ ስለነበረ፣ የፖለቲካውን ጥበብና የትዕግሥትን መሣሪያነት ከማንም የበለጠ የሚያውቁት ራሳቸው ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መሆናቸውን ሳያስገነዝቡ ማለፍ አልፈለጉም። በመሠረቱ፣ ራስ አበበ አረጋይ ጃንሆይን የሚዳፈሩና የሚጋፉ ሰው አልነበሩም። በንግግራቸው ውስጥ ስለ « ትዕግስት » ጉዳይ የጠቀሱት ያሳሰቡት ትርጉም ተሰጥቶበት ነው እንጂ፣ አበበ አረጋይ እጅግ የሚያከብሯቸውን ንጉሠ ነገሥት በአግባቡ ለመንካት ይናገራሉ ተብለው የሚጠረጠሩ አይደሉም።

በዚህ ስብሰባ ላይ በተደረገው የሀሳብ መለዋወጥ፣ ስለ ኤርትራ የተባበሩት መንግሥታት የወሰነውን ከመቀበልና፣ በሱማሌም ጉዳይ የንጉሠ ነገሥቱን ከፍተኛ ቅሬታ ለአባል መንግሥታቶች በቴሌግራም እንዲገለጽ የቀረበውን ከማጽደቅ በስተቀር፣ ሌላ አዲስ ፖሊሲ አልተቀየስም። በኤርትራ በተለይም በሱማሌ ጉዳይ፣ የተባበሩት መንግሥታት ያሳየው ሁኔታ በአለፈው ዘመን በአሠራሩ ጉድለት ከፈረሰው ከገኔቩ የመንግሥታት ማህበር ጋር መመሳሰሉንና፣ አሁን ደግሞ እሱም በተራው ለመጥፋት አደጋው የሚያንገብብበት መሆኑ በጠነከረ ቃል እንዲገለጽ፣ ከኒውዮርክ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ በጥብቅ አሳሰበው ነበር።

የጃንሆይ መልዕክት ከልማዱ አነጋገር ወጥቶ የከረረ እንዲሆን ንጉሠ ነገሥቱ አልተስማሙም። ዞር ዞሮ ፍርዱን ማስለወጥ አለመቻሉ የተረጋገጠ ስለሆነ፣ በጠነከሩ ቃላቶች፣ ከድርጅቱ ጋር መቃቃሩ ለምን ይጠቅማል ? የሚለው ሀሳብ ስለአሸነፈ፣ ከኒውዮርክ የተዘጋጀው ረቂቅ ቴሌግራም፣ በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ብዙ እርማት ተደርጉበታል።

« ...... እኔ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ታማኝ አባል፣ ጣልያን፣ ሱማሌ ተመልሳ አስተዳዳሪ እንድትሆን በመወሰናችሁ፣ በጥልቅ የተሰማኝን ቅሬታ እንድትገነዘቡት ድምፄን አሰማችኋለሁ:: .... » በሚል መግቢያ፣ ለህምሣ ዘጠኝ የተባበሩት መንግሥታት አባሎች በተላከው ንጉሣዊ መልዕክት ላይ፣ የተገለጹት ዋና ዋናዎቹ ጉዳዮች የሚከተሉት ነበሩ::

« ..... የዛሬ አሥራ ሶስት ዓመት፣ ሰማዕትነትን የተቀበለችው አገሬ፣ ዕድሏ በጠወለገበት ሰዓት፣ በተወደደው ሕዝቤ ላይ የደረሰውን መከራ ለማመልከት፣ በመንግሥታት ማኅበር ፊት የቀረብኩ፣ የነፃ አገሮች መሪዎች ከሆኑት ነገሥታት መካከል የመጀመሪያው ነኝ ስል ያኮራኛል::

...... ፍርድ ሲጓደል ጠንቁ ምን እንደሚያስከትል፣ በዚያን ጊዜ ለመንግሥታት ማህበር ያደረግኩት ንግግር፣ ትንቢት ሆኖ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ዘመን ታላቅ ጥፋትና ጉዳት መድረሱን አሳይቷል:: ...... ዛሬ ደግሞ ለተባበሩት መንግሥታት የማሰማው ቃል፣ ለሁለተኛ ጊዜ የሚነገር ትንቢት ተብሎ እንዲቆጠርልኝ ሳይሆን፣ ለትክክለኛ ፍርድ፣ የሕሊና መቀስቀሻ እንዲሆን አስቤ መሆኑን እንድታውቁልኝ እፈልጋለሁ::

...... የጄኔቩ የመንግሥታት ማዘበር፣ ለትክክለኛ ፍርድ ሳይሠራ ቀርቶ ስለፈረሰ፣ ከዛሬ አራት ዓመት በፊት አዲስ በተቋቋመው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ላይ፣ እኔና ሕዝቤ ያደረግነው ዕምነትና ተስፋ ወሰን አልነበረውም::

...... ጣልያን ተመልሳ ሱማሌን እንድትይዝ ሲወሰንላት፣ በአገሬ በኢትዮጵያ ላይ የሚደርሰው አደጋ ባለመታሰቡ፣ እኔና ሕዝቤ ከፍ ያለ ሥጋት እንዲያድርብን አስገድዶናል:: ባለፉት ዘመናት ተደጋግመው የደረሱት ታሪኮች እንደመሰከሩት፣ ጣልያን ወሰን እየጣሰች፣ አገሬን ለመውረር ጦር ያዘጋጀችው፣ መነሻዋን ከዚሁ ከጐረቤት አገር አድርጋ መሆኑን የተባበሩት መንግሥታት የፍርድ ሸንጐ ሊሰተው አይገባም ነበር::

...... ጣልያን ወደ ሱማሌ እንድትመለስ ከተደረገ፣ ለአገሬ ይቀራል ተብሎ የማይታሰብ ታላቅ አደጋ መሆኑ፣ በመልዕክተኞቼ አንደበት በተጣራ አኳኋን ከተገለጠ በኋላ፣ ድጋፋቸውን ለጣልያን የሰጡት አባል አገሮች፣ በጊዜው ላይ የሚታያቸውን ጥቅም በመሻማት፣ መሠረታዊ የሆነውን የታሪክ ኤክስፔሪየንስ ረስተውታል:: ...... ትክክለኛን ፍርድና የኮሌክቲፍ ሴኪውሪቴ መሠረታዊን ሀሳብ ይፈጽማል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት የተባበሩት መንግሥታት፣ ይዘን የመሰለ አደገኛ ውሳኔ በማድረጉ፣ መላው አባል አገሮች ቅሬታዬንና ጥልቅ ሀዘኔን እንዲገነዘቡት ማድረግ ዓይነተኛ ተግባሬ ነው:: —

...... በመንግሥታት ማህበር አባሎች መካከል የሚፈጸመው ጥቃቅን ጥቅም፣ ትክክለኛ ፍርድን እንዴት እድርጐ እንደሚያዛባ፣ አንድ ቀን «እውነት» የተሸፈነውን ገልጦ ድል የሚመታበትን ጊዜ ለማየት እንደምበቃ፣ ያለኝን ጽኑ ዕምነት፣ የመልዕክቴ መደምደሚያ አደርገዋለሁ::...... »

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት

በጉኑተ ልዑል ቤተመንግሥት በዚህ መልክ ተዘጋጅቶ ለተባበሩት መንግሥታት አባሎች የተላከው ቴሌግራም በኒውዮርክ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች እንደጠበቁት አልሆነላቸውም። ...... በአቶ አክሊሉ አስተያየት፤ ዛሬ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለኤርትራና ለሱማሌ የሰጠው ፍርድ፣ የአባልነት መብት የሌላትን የግፈኛዋን ጣልያንና የአጃቢዎቿን የላቲን አሜሪካ አገሮችን መምሪያ ተቀብሎ መሆኑን፤ ንጉሠ ነገሥቱ የዓለም ሕዝብ እንዲያውቀው ማጋለጥ ነበረባቸው። ባለፈው የጄኔቭ የመንግሥታት ማህበር፣ ፍርድ የተነፈጋቸው ንጉሠ ነገሥት፣ በጠለቀ የሀዘን ስሜት የተናገሩት ትንቢት ደርሶ የታየላቸው ስለሆነ፤ የዓለም የዜና ማሠራጫ ድርጅቶች የጃንሆይን መግለጫ የሚያዳምጡት በጥንቃቄና በአክብሮት ነው። በዚህ መልካም ዝናቸው በመጠቀም፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአባል አገሮችን የእኩልነት መብት እያፈረሰ፣ በጥቅም ለተሳሰሩ ወገኖች መሣሪያ ሆኖ መገኘቱን በሚገባ አጋልጠው ቢያወግዙት፣ በዓለም ላይ ኢትዮጵያ ብዙ ተቆርቋሪዎችና ደጋፊዎች እንደምታገኝ አይጠረጠርም ነበር።

ይሁን እንጂ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ምንም እንኳን የውጭውን ዓለም አስተሳሰብና የፖለቲካውን አካሄድ ቢያውቁትም፣ በዚያን ዘመን እንደ እነ ቲቶ እና ኔህሩ በምዕራብና በምሥራቅ ኃያላን መካከል፣ ወዲያና ወዲህ እያሉ መጠቀምን የሚፈልጉ አልነበሩም። ከዚህም በላይ በአካባቢያቸው ያሉት ሁሉ፤ ጃንሆይ ለዓለም መሪዎች የሚልኩት መልዕክት ሆነ፣ ወይም የሚያቀርቡት ሀሳብ፣ እያንዳንዱ ቃል የተመዘነና፣ የንጉሠ ነገሥቱን የክብር ደረጃ የያዘ እንዲሆን፣ በጥብቅ የሚቆጣጠሩ ናቸው። እንግዲህ፤ በዚህ ዓይነት በነበረው በዘመኑ አስተሳሰብ፣ አቶ አክሊሉ እንደተመኙት፣ የተባበሩት መንግሥታት የፈጸመውን ፍርደ ገምድል ሥራ፤ በዓለም ላይ ለማጋለጥና ከዚህም ጋር የድርጅቱ ሕይወት ሥጋት ላይ እንዲወድቅ የተለየ ጥረት ማድረግ፣ ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ጨዋ የሆነ መሪ ተግባር ሆኖ አልታያቸውም። የኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ መመለስ፣ የአምላክ እርዳታ ተጨምሮበት ከፍጻሜ እንዲደርስ የተቻለውን ከማድረግ በስተቀር፣ ለኅ ኅዳር 21 ቀን 1949 ዓ.ም ኒውዮርክ ላይ የታየውን አሳዛኝ ፍርድ ማጋጋሉ፣ ጠቃሚ አይደለም ብለው፣ ንጉሠ ነገሥቱ ሠላማዊውን መንገድ መረጡ።

የተባበሩት መንግሥታት በሰጠው ፍርድ፣ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ቅሬታ ሲያድርባት በሮማ መንግሥት ዘንድ የታየው ደስታ ወሰን አልነበረውም።
« .... ጣልያን የኢትዮጵያን ምኞች ውድቅ አስደርጋ ድል መታች ...... » በሚል ቃል፣ ሕዝቡን ለመቀስቀስና ከፍተኛ ድጋፍ ለማግኘት የደጋስፐሪ መንግሥት ብዙ ጥረት አድርጓል።

« ...... በፋሽስትነቷ በፈጸመችው ግፍ ምክንያት፣ እስከዛሬ ድረስ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአባልነት መብት የተነፈጋት ጣልያን፣ ዝነኛውን መሠረታዊ ታሪኳንና የሥልጣኔ ዕድገቷን የሚያከብሩላትና የሚያውቁላት ብዙ ወዳጆች ስለአሏት፤ የጠላቷን ቅስም መስበር አላቃታትም። ዛሬ የሱማሌ ግዛቷ ተመልሶላታል። በመጭውም ዓመት ኤርትራ በእጇ እንደምትሆን አይጠረጠርም። ለሊቢያ ነፃነት እንዲሰጥ ሲወሰን፣ በመማክርቱ ጉባኤ ጣልያን ከፍተኛ ቦታ ስለተሰጣት፣ በአገሩ ላይ የሚኖሩትን የዜጐቿን መብትና ደህንነት ለመጠበቅ የምትችልበትን መንገድ አግኝታለች ...... » እየተባለ፣ በአልቺዴ ደጋስፐሪ መንግሥት የሚነዛውን ፕሮፓጋንዳ፣ አብዛኛው የጣልያን ሕዝብ አምኖ በመቀበል በደስታ ሲጨፍር ከርሟል።

# ክፍል አምስት

## የኤርትራ ጉዳይ በአምስተኛው ጠቅላላ ጉባኤ

## (የካቲት - ታህሣሥ 1950)

ገጽ


1. መርማሪው ኮሚሽን በኤርትራ ..... 284
2. መርማሪው ቡድን ከኢትዮጵያ ጋር ..... 288
3. የኤርትራ ጉዳይ ይመለከተናል የሚሉ አገሮች ..... 291
4. የአምስቱ ኮሚሽነሮች ዳኝነት ..... 292
5. የፌዴሬሽን መፍትሔ ..... 299
6. የአምስተኛው ጉባኤ ሂደት ..... 306
7. የመጨረሻው ውሳኔ ..... 313
8. ደስታና ቅሬታ ..... 321
9. ለኤርትራ ሕገ መንግሥት ዝግጅት ኮሚሽነር ተመረጠ ..... 329
10. በአሥመራ አዲስ ሳይዘን አፈሰር ..... 330
11. የማቲየንሶ ሕገ መንግሥት ..... 333

# መርማሪው ኮሚሽን በኤርትራ፤

የኤርትራ ሕዝብ ለወደፊት ዕድሉ ምርጫው ምን መሆኑ፣ በድጋሚ ተጣርቶ እንዲቀርብ ስለተወሰነ፡ ኅዳር 21 ቀን 1949 ዓ.ም ከተባበሩት መንግሥታት የተመረጡት አምስቱ መርማሪ ዳኞች፡ ከየካቲት 14 ቀን እስከ ሚያዝያ 6 ቀን 1950 ዓ.ም ድረስ ለሰባት ሳምንታት የመረብ ምላሽ ሕዝቦችን ፍላጐትና ስሜት ሲያጠኑ ከረሙ::

ከነዚህ ከአምስቱ የመርማሪ ኮሚሽን አባሎች መካከል፣ ትክክለኛና ሚዛን ያለው አስተያየት ሊሰጥ ይችላል ብላ፡ ኢትዮጵያ ዕምነቷን የጣለችው በኖርዌዩ መልዕክተኛ ላይ ብቻ ነበር:: ጓቴማላና ፓኪስታን ጉዞአቸውን ወደ ኤርትራ ከመጀመራቸው በፊት፣ የጣልያን መንግሥት የሚፈልገውን ራፖር አዘጋጅተው እንደአጠናቀቁ፡ እንዲሁም በዘር መድልዎ የተመሠረተው የደቡብ አፍሪካ ወኪልም፣ የኤርትራን ጉዳይ ጣልያንን በሚረዳ መልክ እንደሚያጠና ኢትዮጵያ እርግጠኛ ነበረች:: አምስተኛው የቡድኑ አባል የሆነው የበርማ መልዕክተኛ፣ የመጨረሻው አቋሙ ምን እንደሚሆን በግልጽ ባይታወቅም፡ በተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ላይ ከሚሰጠው ትችት እንደተገመተው፡ ለኢትዮጵያ ደጋፊ ይሆናል ተብሎ ተስፋ አልተደረገበትም::

በዚህ አኳኋን የምርመራው ሥራ ከመጀመሩ በፊት የአምስቱ ዳኞች አቋም ሲታይ፡ አብዛኞዎቹ አባሎች ጣልያን ለኤርትራ የነደፈውን ፕላን የሚደግፉ ስለሚሆኑ፡ የኢትዮጵያ ተስፋ የመነመነ ሆኖ ይታያል:: ይሁን እንጂ በኤርትራ ምድር እነ ራስ ኪዳነ ማርያም እና እነ ደጃች በየነ ባራኺ፡ እነ መላከ ሠላም ዲሚጥሮስና እነ ተድላ ባይሩ፡ እነ ከንቲባ ያስማንና እነ ሼህ እላሚን ባሉበት፡ ጠላቶቻችን እነ ኢብራሂም ሡልጣንና እነ ወልደአብ ወልደማርያም እንዴት አሸናፊ መሆን ይችላሉ ? የሚል ተስፋ እየተደረገ፡ በተለይ በኘ ልዑል ቤተመንግሥት አካባቢ ሞራልን ለማጠንከር ሙከራ መደረጉ አልቀረም::

የሮማ መንግሥትም በበኩሉ፡ ጓቴማላ፣ ፓኪስታንና ደቡብ አፍሪካ የኔው ናቸው ብሎ ፍጹም እርግጠኛ ሲሆን፡ ከኖርዌይ መልዕክተኛ እርዳታ እንደማያገኝ ያውቅ ነበር:: እንዲሁም በበርማው መልዕክተኛ ላይ ሙሉ ዕምነት አላሳደረም:: ከአምስቱ ዳኞች መካከል አራቱ፡ የጣልያን ሀሳብ ደጋፊዎች ሆነው ፍርዳቸውን እንዲሰጡ፣ የበርማን መልዕክተኛ በገንዘብ ለመደለል፣ የሮማ መንግሥት እርምጃ ወሰደ:: ስለዚሁ ጉዳይ በጣልያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዚያን ዘመን የዲፕሎማቲክ ኮሬስፖንዳንሶች ውስጥ የተገኘው ዶክመንት፡ ለበርማ መልዕክተኛ ማባበያ የተወሰነ ገንዘብ ለመስጠት ከበላይ ባለሥልጣን መወሰኑን ይገልጻል:: የጣልያን መንግሥት በኤርትራ ጉዳይ የሚፈልገውን ለማግኘት ከፍተኛ ጥረት ያደረገው፡ የኮሚሽኑን አባል በገንዘብ በመግዛት ብቻ ሳይሆን፣ ለበርማ መንግሥት የኤኮኖሚና የቴክኒካል እርዳታ እንሰጣለን የሚል የማታለያም ዕቅድ እንደነበረው ዶክመንቱ አመልክቷል:: በመጨረሻ ውጤቱ እንደታየው፡ የበርማ ወኪል የተመደበለትን ጉቦ ይቀበል አይቀበል፡ ለተባበሩት መንግሥታት በሰጠው አስተያየት፡ የጣልያን ታማኞች ከሆኑት ከጓቴማላ እና ከፓኪስታን ጋር አልተሰለፈም::

የመርማሪው ኮሚሽን ቡድን አሥመራ ከመድረሱ በፊት፣ በጣልያን መንግሥት በኩል የተደረገው ዝግጅት፣ ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እና ለካቢኔአቸው

አጅግ የሚያሳስብ ነበር። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት፣ ኮሎኔል ነጋ ኃይለሥላሴን በአሥመራ ላይዘን አፊሰር አድርገው እንደሾሟቸው ሁሉ፤ የጣልያኑ መሪ አልቺደ ደጋስፐሪም በበኩሉ፤ ኮምት ዲ ግሮፔሎ (COUNT DI GROPELLO) የተባለውን ሁብታም ፋሽስት መርጦ፣ በኤርትራ የሮማ መንግሥት ዋና ወኪል አድርጎ መደበው።

ኮምት ዲ ግሮፔሎ ከሮማ ጭኖት የመጣው የጣልያን ሊሬና የእንግሊዝ ፓውንድ ወሰን የሌለው በመሆኑ፤ የማህበረ ፍቅረ ሀገር አባሎችን በገንዘብ እየደለለ፣ ለነ ኢብራሂም ሡልጣን ፓርቲ እንዲሰለፉ ለማድረግ ዋና ዓላማው ሆነ። በእውነትም በዚሀ ረገድ ያደረገው ጥረት፤ ጥሩ ውጤት የሚሰጥ ምልክት አገኘበት። ከአንድነት ወገኖች መካከል አንዳንዶቹ ገንዘቡ ስለአታለላቸው ወደ ነፃነት ግንባር ፓርቲ እየሄዱ ሲመዘገቡ ታዩ። ጥጋበኞቹ በኤርትራ የሚኖሩት ጣልያኖችና ክልሶቹም፣ ድሉ የኛ ነው እያሉ መፎከራቸውን ቀጠሉ። በኮምት ዲ ግሮፔሎ የተነደፈው ፕሮግራም፤ የተባበሩት መንግሥታት የመርማሪው ኮሚሽን ቡድን ኤርትራ ሲደርስ፤ ስማንያ በመቶ የሚሆነው የኤርትራ ሕዝብ የሚፈልገው፤ በጣልያን የኤኮኖሚ አርዳታ ነፃነትን አግኝቶ ለመኖር መሆኑን ለማሳመን ነበር።

የማህበረ ፍቅረ ሀገር መሪዎች አንደ ጣልያን መንግሥት ፓውንድና ሊሬ በቁና እየሰፈረ የሚረጭላቸው ስለሌለ፤ ጠላታቸውን የሚቋቋሙበት ሌላ ዘዴ መፍጠር ግዴታቸው ሆነ። እዚህ ላይ የንጉሠ ነገሥቱ ላይዘን አፊሰር ኰሎኔል ነጋ ኃይለሥላሴ፤ የአንድነቶች ኃይል ደክሞ ለጠላት ምቹ እንዳይሆን፤ ያደረጉት ጥረትና ያሳዩት ጠንካራ ሞራል የሚደነቅ ነበር። ነጋ ኃይለሥላሴ ከውትድርና ሞያቸው ጋር በተፈጥሮ መንፈስ ጠንካራና በሚያምኑበት የሚጸኑ በመሆናቸው፤ ኮምት ዲ ግሮፔሎ በገንዘብ ኃይል የሚያጠምድባቸው ሤራ ጨርሶ አላስጋቸውም። « ..... የኤርትራ ሕዝብ መሠረታዊ በሆነው በኢትዮጵያ ታሪኩ የሚኮራና ለነፃነቱ የቆረጠ በመሆኑ፤ ተመልሶ የጣልያን አሽከር ለመሆን በገንዘብ አይደለልም ...... » የሚለው የነጋ ኃይለሥላሴ አቋም፤ የአንድነት ወገኖችን ሞራልና ኃይል አጠናክሮ፤ የጠላትን ተንኮል ለመቋቋም ትልቅ መሣሪያ ይሆነናል ብለው፤ የማህበረ ፍቅረ ሀገር አባሎች አርምጃ ወሰዱበት። የነጋ ፕላን በዚህ ብቻ አይቆምም። ኮምት ዲ ግሮፔሎ በገፍ የሚበትነው ገንዘብ በእውነትም የፍቅረ ሀገርን ድርጅት የሚያዳክምና የተቃዋሚዎቹን ወገኖች የሚያጠነክር ከሆነ፤ አንድነቶች ጣልያኖቹንና ርዝራዦቻቸውን ለማስደንገጥ፣ ኃይልን ከመጠቀም በስተቀር ሌላ መንገድ አይኖራቸውም የሚል ነበር።

ኮምት ዲ ግሮፔሎ በደረሰው መረጃ፣ ከአንድነቶች ጀርባ ሆኖ ሽፍቶች እየመለመለ የሚያሰለጥንና በጣልያኖችና በወገኖቻቸው ላይ አደጋ የሚያስጥለው፤ የንጉሠ ነገሥቱ ላይዘን አፊሰር ኰሎኔል ነጋ ኃይለሥላሴ ስለሆነ፤ እሱን አስገድለን ካልተገላገልን ፕሮግራማችን ሊከናወን አይችልም አለ። በዚያን ዘመን የጣልያን የውጭ ጉዳይ ምክትል ሚኒስትር የነበረው ሴናተር ብሩዛስካ ከብዙ ዓመታት በኋላ ሲያጫውተኝ፤ « ..... ነጋ ኃይለሥላሴን ለማስገደል፣ ዲ ግሮፔሎ ያቀረበውን ሀሳብ አልተቀበልነውም። ኰሎኔል ነጋ፣ በጣት ከሚቆጠሩት የንጉሠ ነገሥቱ ከፍተኛ መኰንኖች አንዱ የነበረ፣ በአርበኝነትም የተካፈለ፣ ኢትዮጵያ ነፃነቷ በተመለሰም ጊዜ የጦር ሚኒስቴርን በዋና ጸሐፊነት በማቋቋም የታወቀ ሰው ስለሆነ፤ እሱን ማስገደል፤ በኢትዮጵያና በኤርትራ በሚኖሩት በመላ የጣልያን ዜጎች ሕይወት ላይ፣ ማስፈረድ ይሆናል ብለን፤ የዲ ግሮፔሎን ዕቅድ አፍርሰናል ...... ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ኰሎኔል ነጋን በአሥመራ ላይዘን አፊሰር አድርገው በሾሙ ጊዜ፣

እንግሊዞች እንዳይቀበሉ ወይም አግሪመንቱን እንዲያዘገዩ ብዙ ደክመን ነበር:: ኩሉኔሉ፣ ጣልያንን አምርሮ የሚጠላ ከመሆኑም በላይ፤ በተፈጥሮም ደፋርና ኃይለኛ ሰው ነው እየተባለ ስለሚነገር፣ በኤርትራ ላሉት ዜጎቻችን ሕይወትና እኛም ለምንከተለው ፖሊሲ አስጊ እንደሚሆንብን እናውቅ ነበር ...... ለምሳሌ የተባበሩት መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን ኤርትራ ሲደርስ፤ የነፃነት ግንባር ደጋፊዎች ሀሳባቸውን ለመግለጽ እንዳይችሉ ሞራላቸውን ለመስበር፤ ሃምሣ ስድስት (56) የጣልያን ዜጎች በአንድነት ፓርቲ ሽፍቶች የተገደሉት በነጋ ኃይለሥላሴ ዝግጅት ነው ብሎ የመረጃው ክፍላችን አመልክቶን ነበር:: ..... ለማናቸውም እኛ በንጉሠ ነገሥቱ ላይዘን አፊስር ላይ እንዳችም እርምጃ አልወሰድንም ...... » አለኝ:: ምን ዓይነት እርምጃ ? ጣልያኖች ሊያደርጉ የሚችሉት ማስገደል ብቻ ነበር:: እሱንም ፈርተው አልሞከሩትም:: ሃምሣ ስድስት ጣልያኖች ከተገደሉ በኋላ፣ ክምት ዲ ግሮፔሎ ኮሎኔል ነጋን ገና በሩቅ ሲያዩቸው በፍርሃት ሲንቀጠቀጥ ይታይ እንደነበረ ይነገራል::

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የማህበረ ፍቅሪ ሀገር ድርጅት የገንዘብ ደሀ ቢሆንም፣ መንፈስ ጠንካራ ሆኖ ለውጊያ በመዘጋጀቱ የነፃነት ግንባር የተባለው በሮማ መንግሥት የተቋቋመው ፓርቲ ቅስሙ ተሰብሮ ፍርክርኩ ወጣ:: እነ ኢብራሂም ሡልጣንም የነፃነቱን ግንባር ለቅቀው የተድሞውን «የራቢጣ ኤል ኢስላሚያ» የተባለውን ባንዲራ ለማጥለቅ ሲሯሯጡ ታዩ:: የአንድነት ማህበር አባሎችም ደጋፊዎቻቸው ስለተጠናከሩላቸውና አቅም ስለተሰማቸው፤ ይህ የነፃነት ግንባር የተባለው የጣልያን ድርጅት፣ ከኤርትራ ምድር ውስጥ እንዲጠፋ ከተደረገ፣ ከወንድሞቻችን ከራቢጣ ኤል ኢስላሚያ ፓርቲ አባሎች ጋር ጦርነት አንከፍትም አሉ:: ራቢጣዎችም የጣልያኑን ድርጅት ለማጥፋትና የተድሞ አቋማቸውን ይዘው ለመቀጠል መስማማታቸውን አስታወቁ:: በዚህ ሁኔታ በኤርትራ ውስጥ እጅግ ተፋፍሞ የነበረው የርስ በርስ ውጊያ በቶሎ መብረድ ቻለ:: *

የእንግሊዝ ወታደራዊ አስተዳደር ኃላፊዎች፤ የነፃነት ግንባር የተባለው የጣልያን ድርጅት፤ የአብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ ምኞት ነፃጭ መስሎ የመርማሪ ኮሚሽኑን ቡድን እንዲያታልል አይፈቅዱም ነበር:: እንዲሁም የአንድነት ወገኖች ተቃዋሚዎቹን ሁሉ ደምስሰው የኤርትራን ሕዝብ የሚወክሉት እነሱ ብቻ እንዲሆኑ አለመፈለጋቸው ግልጽ ነበር:: በዚያን ዘመን እንግሊዞች መፍትሔ ነው ብለው የሚያምኑት፤ የኤርትራ ምዕራቡ ቆላ ከሱዳን ጋር ተቀላቅሎ፤ ሌላው በሙሉ ወደ ኢትዮጵያ እንዲዋሀድ ስለሆነ፤ የመርማሪው ኮሚሽን ቡድን በዚህ አስተያየት እንዲመራ የተቻላቸውን ከመድረግ አልተቆጠቡም::ለዚህም ግብ «የነፃነት ግንባር » የተባለው የጣልያን ድርጅት ተበትኖ የራቢጣ ኤል ኢስላሚያ ፓርቲ እንደገና ማንሰራራቱን አልጠሉም::

ከሶስት ዓመት በፊት፣ የአራቱ ኃያላን መርማሪ ቡድኖች ወደ ኤርትራ ሲመጡ እንዳደረገው ሁሉ፤ አሁንም የተባበሩት መንግሥታት መርማሪ ዳኞች ሲደርሱ፤ የተቀበላቸውና አስፈላጊውንም የሥራ ፕሮግራም ደልድሎ ያዘጋጀላቸው፣ የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ወታደራዊ አስተዳደር ነው:: መርማሪዎቹ ዳኞችም

* ቃለ መጠይቅ አስፍሐ ወልደሚካኤል

በኤርትራ ግዛት እየተዘዋወሩ የሕዝቡን አስተያየት በማዳመጥና፣ ቀጥታ በሆነም መንገድ ከሕዝብ ወኪሎች ጋር በመነጋገር ሁለት ወር ያህል በቆዩበት ጊዜ፡ በሥራቸው ላይ አንዳችም እንቅፋት አላጋጠማቸውም::

« ኢትዮጵያ ወይ ሞት » ብለው የተነሱት የአንድነት ወገኖችም፣ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ተጠናክረው የአብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ የሀሳብ ገላጮች መሆናቸውን ለማሳመን በቅተዋል:: ከአምስቱ መርማሪ ኮሚሽን አባሎችም መካከል፣ ከጓቴማላና ከፓኪስታን በስተቀር፣ ሌሎቹ ኖርዌይ, በርማና ደቡብ አፍሪካ፡ የማህበረ ፍቅረ ሀገር ድርጅት የአብዛኛውን የኤርትራን ሕዝብ ስሜት ያቀፈ መሆኑን ለመረዳት ችለዋል:: ለምሳሌም ያህል የሠራዬ አውራጃ ሕዝብ በተለይ አዘጋጅቶ ለመርማሪው ኮሚሽን ቡድን ያቀረበላቸው ትርዕይት፡ እጅግ የሚደነቅ መሆኑን ከጓቴማላና ከፓኪስታን በስተቀር ሌሎቹ ኮሚሽነሮች አምነውበታል::

...... በአንድ ሰፊ ሜዳ ላይ ዙሪያውን ብዙ ሺህ ሕዝብ የጨፈቃ አጥር መስሎ ተሰብስቦ፣ በየአራቱ ግዕዝን ማህል ላይ፡ ዋና ዋና ያገር ሽማግሌዎች ባገር ልብስ ጃኖ ኩታ አሸብርቀው ቦታ ይዘው ይጠባበቃሉ:: በስተደቡብ በኩል አንዲት በቅርብ ቀን የወለደች ላም ከልጇ ተነጥላ ታሥራለች:: በስተሰሜን በኩል ያች ከእናቷ የተነጠለች ጥጃ ታሥራ፣ ወላጇን በሩቅ እያየች ትጮሃለች:: እናት ላም ደግሞ ልጇን ፍለጋ እምቧ እያለች ድምጿን ታሰማለች:: ዝግጅቱ በዚህ ዓይነት ከተጠናቀቀ በኋላ፡ የተባበሩት መንግሥታት መርማሪ ዳኞች ከሥፍራው ደርሰው በሕዝቡ የተመረጡትን ዋና ዋና ሰዎች ሲያነጋግሩ፣ ይህ የላሚቷና የጥጃዋ ትርዕይት ተጀመረ:: ስጉጥ መስሉ ከተሰበሰበው ሕዝብ ማህል ቦታ ይዘው ከሚጠ ባበቁት ታላላቅ ያገር ሽማገሌዎች መካከል፡ ቀደምትና አንጋፋ የሆኑት ራስ ኪዳነማርያም ገብረመስቀል፣ ከሥፍራው በስተሰሜን በኩል ታሥራ ወደ ምትጮኸው ጥጃ ዘንድ ሄደው፣ የታሠረችበትን ገመድ በመቀስ ሲቆርጡ፡ ጥጃዋ ሮጣ እናቷ ዘንድ ሄዳ ተለጠፈች:: ይህ ትርዕይት የመረብ አጥር ፈርሶ እናትና ልጅ እንዲገናኙ የኤርትራ ሕዝብ ጽኑ ፍላጉት መሆኑን፡ ኮሚሲዮኑ እንዲረዳው ከመጠየቅ በስተቀር፡ ዲስኩርና ሀተታ በማብዛት ጊዜያችሁን አናጠፋባችሁም ብሎ፣ የሠራዬ አውራጃ ሕዝብ ከተባበሩት መንግሥታት የተጠየቀውን ስሜቱንና ፍላጐቱን አስረዳ::

ቀደም ሲል እንደተገለጸው፣ የጣልያን መንግሥት የኤርትራንና የኢትዮጵያን አንድነት ማህበር አባሎችን በገንዘብ ኃይል እያስከዳ፣ የነፃነት ጠ ያቂዎችን ቁጥር አበራክቶየመርማሪ ኮሚሲዮኑን የድጋፍ አስተያየት ለማግኘት ያደረገው ጥረት ሁሉ አልተሳካለትም:: ብዙ ሰዎች ከኮንት ዲ ግሮፔሎ በገፍ የሚበተነውን ገንዘብ ቢቀበሉም፡ በመጨረሻው የጣልያን ወኪል እንደተመኘው፡ የመርማሪው ማህበረ ፍቅሪን ለቅቀው ወደ እነ ኢብራሂም ሡልጣን አልሄዱም:: የመርማሪው ኮሚሽን ቡድን በሚያልፍባቸው መንገዶች ጣልያኖቹና ክልሶቹ እየተሰለፉ የሮማን መንግሥት ባንዲራ ለማውለብለብ ባደረጉት ዝግጅት ላይ ሕዝቡ አልተባበራቸውም:: እንዲያውም ዲ ግሮፔሎ አሠርቶ በብዛት ያሠራጨውን አረንጓዴ ነጭ ቀይ የሆነውን የጣልያንን ባንዲራ፡ ሕዝቡ ነጩን ቀለም ወደ ቢጫ እየለወጠ መንገዶቹና መንደሮቹ ሁሉ፣ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ እንዲያሸበርቁ አድርጐባቸዋል:: በጠቅላላው በጣልያን በኩል የተዘጋጀው ሤራ አንዳችም ውጤት አላመጣም:: ያ ሁሉ ገንዘብ ተበትኖ ብዙ የተለፋባቸው የጣልያን አሽከሮች የሆኑት እነ ኢብራሂም ሡልጣን፣ የመጨረሻው ባዶ ቀፎ ይዘው ብቻቸውን ቀሩ:: ድር

ቢያብር አንበሳ ያሥር እንደሚባባለው፣ አንድነቶች በደልብ ተጠናክረው፣ ገንዘብ ሳያታልላቸው ማናቸውም ኃይል ሳያስጋቸው፣ «ኢትዮጵያ ወይ ሞት» ብለው የቆረጡበትን ዓላማ የተባበሩት መንግሥታት ለላካቸው መርማሪ ዳኞች በትክክል አስረድተዋል::

## መርማሪው ቡድን ከኢትዮጵያ ጋር

ከየካቲት 14 ቀን እስከ ሚያዝያ 6 ቀን 1950 ዓ.ም ድረስ፣ የተባበሩት መንግሥታት መርማሪ ከሚሽነሮች መላውን የኤርትራን ግዛት እየተዘዋወሩ፣ የሕዝቡን ፍላጐትና ስሜት ሲያዳምጡ ከከረሙ በኋላ፣ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታትን የኢትዮጵያን አስተያየት ለመስማት ከአሥመራ ወደ አዲስ አበባ ተጓዙ::

አምስቱ የቡድኑ አባሎች አዲስ አበባ በደረሱ ጊዜ፣ አክሊሉ ሀብተወልድ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የተቀበሏቸው፣ « ...... ከሎኒያሊስት ጣልያን ከእናት አገሩ ከኢትዮጵያ ተነጥሎ፣ ለብዙ ዓመታት ሲያሰቃየው የኖረውን የኤርትራን ሕዝብ የወደፊት ዕድል ለመወሰን፣ በተባበሩት መንግሥታት የተመረጣችሁትን ዳኞች፣ አገሬ እንኳን ደህና መጣችሁ ብላ አክብሮቷንና ደስታዋን ትገልጥላችኋለች ...... » በሚል ቃል ነበር::

በመሠረቱ በኤርትራ ጉዳይ የኢትዮጵያ ጥያቄና አቋም ምን መሆኑ በተባበሩት መንግሥታት ጉባኤዎች ላይ በሰፊው ተደጋግሞ ስለተገለጸ፣ የመርማሪው ኮሚሽን አባሎች ያልሰሙት ወይም ያልተረዱት ነገር ይኖራል ማለት አይቻልም:: ሆኖም ጥያቄው የቀረበው በቀጥታ ከኰሚሽነሮቹ ስለሆነ፣ የኤርትራ ሕዝብ ሕይወት ከኢትዮጵያ ተነጥሎ ሊኖር እንደማይችል፣ የንጉሠ ነገሥቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በሰፊው ለማስረዳት መልካም አጋጣሚ ሆኖላቸዋል:: ከአንድ ሰዓት በላይ በፈጀው ሰፊ መግለጫቸው ውስጥ፣ አክሊሉ ሀብተወልድ መርማሪዎቹን ዳኞች ለማስገንዘብ የሞከሩት፣ እንደሚከተለው ነበር::

« ..... በኤርትራ ውስጥ በልዩ ልዩ ሥፍራዎች በተጓዛችሁበት ጊዜ፣ ሰብዙ ሺህ ዓመታት « ኢትዮጵያ » በሚለው መጠሪያ ስሟችን፣ በጥንታዊው ታሪክ ያወቃችሁትን አገር፣ በውን ለማየትና ሕዝቡንም ለማነጋገር ዕድል አግኝታችኋል::

....... በአዲሮሰና በአዲ ሳቅጠ፣ በዘመነ ሳባ የነበረውን የኢትዮጵያን ሥልጣኔ የሚመሰክሩትን ሐውልቶችና፣ ከምፅዋ አቅራቢያ በሚገኘው በአዶሊስ ከተማ፣ ገናናውን የአክሱምን ንጉሠ ነገሥታዊ ግዛት የሚያመለክቱትን ጥንታዊ ቅርሶች ተመልክታችኋል:: በምፅዋ አቅራቢያም በነበራችሁበት ጊዜ፣ በ1886 ዓ.ም ዛሬ ኤርትራ ተብሎ በኮሎኒያሊስት የተሰየመው፣ ቀድሞ መረብ ምላሽ የተባለው አውራጃ ገዥ የነበሩት ራስ አሉላ፣ አገሩን ለመውረር የመጣውን የጣልያንን ጦር ድል የመቱበትን፣ ሰሐጢንና ዶጋሊን ጐብኝታችኋል::

...... ምንም እንኳ ኮሎኒያሊስት ጣልያን ለሃምሣ ዓመታት ቢለያየንም፣ ኤርትራውያንና ኢትዮጵያውያን፣ በዘር ሆነ በባሕል፣ በቋንቋ ሆነ በኑሮ ጠባይ፣ ምን ያህል የተሳሰሩና ተመሳሳይ ሕዝቦች መሆናቸውን ተገንዝባችኋል:: ...... በኤርትራ ግዛት በየገጠሩ ስትዘዋወሩ፣ ከኢትዮጵያ ጋር የሚመሳሰሉትን አንድ ዓይነት የመኖሪያ ቤቶችን አሠራር፣ አንድ ዓይነት የሆኑትን የኑሮ ጠባዮች፣ አንድ ዓይነት



የተባበሩት መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን አባሎች ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር፣

ከግራ፤ በርማ፣ ኖርዌይ፣ የU.N ወኪል
ከቀኝ፤ ጓቴማላ፣ ደቡብ አፍሪካ፤ ፓኪስታን፤

(ሚያዝያ 1950)

የሆኑትን አለባበሶች፣ አንድ ዓይነት የሆኑትን የባሕልና የአነጋገር ዘይቤዎች፤ አንድ ዓይነት የሆኑትን የመጠሪያና የማዕረግ ስሞች ተመልክታችኋል::

...... ከኢትዮጵያ ጋር ከምንሆን ጣልያን እንደገና ገዢታ ለነፃነት ታብቃን፤ የሚሉትን፤ ከራሳቸው በስተቀር የሕዝብ ተወካይነት የሌላቸውን፣ የነ ደጃዝማች አብርሃ ተሰማንና የነ ግራዝማች ኢብራሂም ሡልጣንን መግለጫዎች ሰምታችኋል:: እንደዚሁም የአብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ እንደራሴዎች የሆኑትን፤ እጅግ የተከበሩትን የራስ ከሳንማርያም ገብረመስቀልን፤ የደጃዝማች በየነ ባራኪንና በምዕራቡ ቆላ ሕዝብ ዘንድ እጅግ የታወቁትን የከንቲባ ያሰማንን አስተያየት አዳምጣችኋል:: ታላቁ አርበኛ ራስ ኪዳንማርያም፤ በዶጋሊና በአድዋ ጦር ሜዳዎች ላይ ከግፈኛው ጣልያን ጋር የተደረጉትን ውጊያዎች በመተንተን፣ የሰሟችሁን ትክክለኛ የምስክርነት ቃል ሰምታችኋል::

የኤርትራ ሕዝብ ምንም እንኳ ያለ ውዴታው ከአገሩ ከኢትዮጵያ ተለይቶ እንዲኖር ቢገደድም፤ ሰው ሠራሽ የሆነውን የመረብን ወሰን እያቋረጠ ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ ለመኖር አንዳችም አገዳ አይደረገበትም:: በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ በእርሻና በንግድ ሥራ የሚተዳደሩት ኤርትራውያኖች ቁጥራቸው ከሁለት መቶ ሺህ (200.000) በላይ ሲሆን፣ እንደዚሁም አንድ ሺህ ስድስት መቶ የሚሆኑት በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ውስጥ ከፍተኛ ኃላፊነት ይዘው በኢትዮጵያዊነት ያገለግላሉ::

የተከበራችሁ መልዕክተኞች፤

ኤርትራ ነፃ መንግሥት ሆና ራሷን ችላ መተዳደር ትችላለች ብሎ ሕዝቡን በዚህ ዓላማ ለማሠለፍ፣ ብዙ ሚሊዮን ሊሬ የሚፈጨው የጣልያን መንግሥት፤ የአገሪቱ ኤኮኖሚ አቅም እጅግ የጠበበ መሆኑንና፣ ሕዝቡም ከኢትዮጵያ ተለይቶ ለመኖር አለመቻሉን ደህና አድርጎ ያውቃል:: ከአንድ ዓመት ጊዜ በፊት ይኸው የጣልያን መንግሥት በሰስተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ላይ በሰጠው መግለጫ፣ ኤርትራ በድህነት የተቆራመደችና ድንቁርና ያጠቃት አገር በመሆኗ፣ ያለ ጣልያን እርዳታ መኖር ስለማትችል፤ የሮማ መንግሥት ተረክቦ ሕይወት እንዲሰጣት ያስፈልጋል እያለ፤ ይነዛው የነበረውን የቅጥፈት ፕሮፓጋንዳ፤ ሁላችሁም እንደምታስታውሱት እርግጠኛ ነኝ:: እንደዚሁም ያለ ጣልያን እርዳታ እና ያለ ጣልያን የኤኮኖሚ ድጎማ ሕይወቷ ሊንቀሳቀስ አይችልም ብሎ ከፍ ያለ ዲስኩር ይነዛበት የነበረችውን አገር፣ ከአራት ወራት በኋላ፤ በአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ላይ፣ ይኸው የሮማ መንግሥት እንዳችም ሀፍረት ሳይሰማው፣ ኤርትራ ነፃነቷን ለመቀበል ያላት የኤኮኖሚ አቅም በቂ ነው ሲል ያቀረበውን የቅጥፈት አስተያየት፤ በትዝብት አዳምጣችኋል:: ...... ዛሬም በኤርትራ እየተዘዋወራችሁ የሕዝቡን ፍላጎትና የአገሩንም ሁኔታ በምታጠኑበት ጊዜ፣ « የነፃነት ግንባር » ተብሎ በጣልያን ገንዘብ የተቋቋመውን ፓርቲና የሕዝብ ድጋፍ የሌላቸው መሪዎቹም ይህንኑ የጣልያን ሀሳብ ገላጮች ሆነው የሚያደርጉትን ጥረት ተመልክታችኋል::

..... አሁን የፖለቲካውን ጉዳይ ትተን በኤርትራ የኤኮኖሚ ሕይወት ላይ በመጠኑ ለማተኮር ብንሞክር፣ ወደ ኤርትራ ለሚገቡት የምግብና የንግድ ዕቃዎች ዋንኛዋና ብቸኛዋ ምንጭ ኢትዮጵያ መሆንዋን በግልጽ ታዩታላችሁ:: በኤርትራ ውስጥ ከሚንቀሳቀሰው የንግድ ልውውጥ ውስጥ፣ ሰማንያ አራት በመቶ (84 %) የሆነው

የምግብና የጥራጥሬ እህል የሚላከው ከኢትዮጵያ ነው:: እነዚህ ወደ ኤርትራ የሚላኩትም የምግብ ሸቀጦች ለዳቦና ለፓስታ ተፈላጊ የሆነው የስንዴ እህል ብቻ ሳይሆን፣ በተለይ ለአብዛኛው ሕዝብ ተፈላጊ የሆነው ጤፍ፣ ገብስ፣ ማሽላ፣ በቆሎ፣ ምሥር፣ ባቄላና ሌሎቹም እንደ በርበሬ የመሳሰሉት ሁሉ ናቸው:: በዚህ አኳኋን የኤርትራ የኤኮኖሚ ሕይወት ከኢትዮጵያ ጋር እጅግ የተሳሰረ መሆኑን ስትመለከቱ፤ የጣልያን መንግሥት ኤርትራ ራሷን የቻለች ነፃ መንግሥት ትሆናለች እያለ የሚለፍፈው ሁሉ፤ የትጥፈት ፕሮፓጋንዳ መሆኑን ለመገንዘብ አያዳግታችሁም:: ..... እኔ ይህን ሁሉ ስናገር፤ ለተባበሩት መንግሥታት ለምታቀርቡት ራፖር ማስተካከያ ሊሆን ይገባል ብዬ ተፅዕኖ ለማድረግ አይደለም:: የተጣለባችሁን ከፍተኛ ኃላፊነትና፣ ፍርድ እስጣጥም ረገድ ሊኖራችሁ የሚገባውን የአስተዋይነት ነፃ መንፈስ የማከብር ነኝ:: ሆኖም በኤርትራ ጉዳይ የኢትዮጵያን አስተያየት መስማት አለብን ብላችሁ ስለጠየቃችሁኝ፣ የማስበውን ለማስረዳት ስሞክር ጊዜያችሁን በመውሰዴ ይቅርታ እጠይቃለሁ:: ኢትዮጵያ ምንጊዜም፣ የተባበሩት መንግሥታት ትክክለኛ ዳኛ እንዲሆን ስትሟገት የኖረች ስለሆነ፤ የእናንተን አስተያየትና ውሳኔ ለመስማት የምትጠብቀው እጅግ ከፍ ባለ ናፍቆት ነው:: ...... »

# የኤርትራ ጉዳይ ይመለከተናል የሚሉ አገሮች አስተያየት

የመርማሪው ኮሚሽን ቡድን አዲስ አበባ መጥቶ የኢትዮጵያን አቋም በዝርዝር ካዳመጠ በኋላ፤ ራፖሩን ከማጠናቀቁ በፊት፤ በመጀመሪያ ለኤርትራ የወደፊት ዕድል የሚደረገው ውሳኔ በቀጥታ ይመለከተኛል ከሚለው ከጣልያን መንግሥት፤ ቀጥሎም በሁለተኛ ደረጃ፣ ከእንግሊዝና ከፈረንሣይ እንዲሁም ከግብፅ፤ በጽሑፍ የቀረቡለትን አስተያየቶች መዝግቧል::

የአዲሲቷ ሬፑብሊክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ ሚያዝያ 17 ቀን 1950 ዓ.ም ለመርማሪው ኮሚሽን በላከው ደብዳቤ፤ ለኤርትራ ጉዳይ መፍትሔው ነፃነትን ከመስጠት በስተቀር ሌላ ምርጫ አለመኖሩን አጠንክሮ ከገለጸ በኋላ፤ በጣልያን ከፍተኛ እርዳታ ኤርትራ ነፃ መንግሥት ሆና ብትቋቋም፣ ኢትዮጵያን የሚጎዳ ወይም ቅር የሚያሰኝ ምክንያት ሊኖር አይችልም አለ:: ካርሎ ስፎርሳ አስተያየቱን በመቀጠል፣ ጣልያን ኤርትራን ቅኝ ግዛቷ አድርጋ የያዘችው፣ ከኢትዮጵያ ቀምታ አለመሆኑን እና፣ አገሪቱም ሠልጥና ከዚህ ደረጃ ለመድረስ የበቃችው፤ ከብዙ ትውልድ ጀምሮ ተያይዘው በመጡት በጣልያን ዜጎች መስዋዕትነት መሆኑን፣ ኮሚሲዮኑ እንዲገነዘብለት ጠይቋል::

እንግሊዝና ፈረንሣይ ለመርማሪው ኮሚሽን በላኳቸው ደብዳቤዎች፣ የአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ በተካሄደ ጊዜ፤ ሁለቱም አገሮች በየበኩላቸው ከገለጿቸው አቋሞች የተለየ ሀሳብ የሌላቸው መሆኑን አመልክተዋል:: ይኸውም፤ እንግሊዞች፣ ከኤርትራ ግዛት ውስጥ ወደ ሱዳን እንዲቀላቀል ከሚፈልጉት ከምዕራባዊው ቆላ በስተቀር፤ ሌላው በሙሉ ከኢትዮጵያ ጋር እንዲዋሀድ ባቀረቡት ሀሳብ የሚጸኑ መሆናቸውን ሲያረጋግጡ፤ ፈረንሣዮች ደግሞ፣ ለኤርትራ የሚዘጋጀው መፍትሔ፤ የጣልያንን እና የኢትዮጵያን ጥያቄዎች በእኩል ደረጃ የሚያረካ መሆን አለበት የሚሉትን የተለመደውን ጠማማ

አስተያየታቸውን በድጋሚ አሳስበዋል:: በተጨማሪም እንግሊዞች በጽሁፍ በሰጡት አስተያየት ውስጥ፤ ለኤርትራ ጉዳይ መፍትሔው « ነፃነት » ነው ተብሎ በጣልያን በኩል የቀረበው ሀሣብ፤ የአገሩ ኤኮኖሚ አቅም የማይችለው መሆኑን ካስረዱ በኋላ፤ ጣልያን በምንም ዓይነት ወደ ኤርትራ እንድትመለስ የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት አለመደገፉን አስታውቀዋል::

በሐምሌ 1946 ዓ.ም በፓሪስ በተደረገው የሰላም ጉባኤ ላይ፤ ከኤርትራ ግዛት የምፅዋ ወደብ ባለቤትነት እኔን ይመለከታል በማለት ቀርባ የነበረችውና፣ ለማመልከቻዋ ተቀባይ አጥታ የተመለሰችው ግብፅ፤ የተባበሩት መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን አስተያየቷን ለማዳመጥ ጠይቋት ነበር። በዘመኑ የነበረው የንጉሥ ፋሩክ መንግሥት በሰጠው መግለጫ፤ የኤርትራ ሕዝብ የወደፊት ዕድሉን ራሱ እንዲወስን ግብፅ መደገፏን ከገለጸ በኋላ፤ የተባበሩት መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን ሥራውን አጠናቅቆ ራፖሩን ከማቅረቡ በፊት፤ አስተያየት መስጠት ተገቢ አይሆንም ብሏል:: ይሁን እንጂ፣ መርማሪው ኮሚሲዮን የሚያቀርበው ሀሳብ፤ ባለፈው ጊዜ የአራቱ ኃያላኖች መርማሪ ቡድን ከሰጠው አስተያየት የተለወጠ እና፤ የኤርትራን ሕዝብ ፍላጐት የማይከተል ሆኖ ከተገኘ፣ ግብፅ በጉዳዩ ላይ፣ የራሷን አቋም ከመውሰድ አትቆጠብም ሲል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሳላህ ኤል ዲን (SALAH EL-DIN) አስታውቋል::"

የመርማሪ ኮሚሽኑ ቡድን ተገቢ የሆነ አስተያየት ካቀረበ፣ ግብፅ የራሰዋን አቋም ትወስዳለች ተብሎ የተሰጠዉ ሀሳብ፣ ምን ለማለት እንደሆነ ግልጽ ሆኖ አልታየም:: በዚያን ሰሞን የግብፅና የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ሲወያዩ፣ የንጉሥ ፋሩክ መንግሥት በተቻለዉ መጠን ለኢትዮጵያ ጥያቄ ድጋፉን እንደሚሰጥ ቃል ሰጥተቷል::

## የአምስቱ ኮሚሽነሮች ዳኝነት

ሀ/ ጉቴማላና ፓኪስታን

ቀደም ሲል እንደተነገረው፤ ጉቴማላና ፓኪስታን የመርማሪው ኮሚሽን ቡድን አባሎች ሆነው ሲመረጡ፤ የሚሰጡት ፍርድ የጣልያንን ፍላጐት የሚያሟላ እንደሚሆን በግልጽ የታወቀ ነበር:: በዚሁ መሠረት ኤርትራን እየተዘዋወሩ በመጐብኘትና ከሕዝቡ የሚቀርበውን አስተያየት በማዳመጥ ለሁለት ወራት ቢቆዩም፤ ከጉዳዩ መነሻ ጀምሮ የጣልያን ደጋፊዎች ሆነው ሲታገሉበት የቆየውን ሀሳብ፣ ለማሻሻል ወይም ለመለወጥ አልሞከሩም::

በእነሱ ምርምር፤

ኢትዮጵያና ኤርትራ አንድ አገር የነበሩ እና፤ በሁለቱ ሕዝቦች መካከል ያሉት የዘርና የባሕል ግንኙነቶች እጅግ የተሳሰሩ ናቸው እየተባለ የሚነገረው ሁሉ መሠረት የለውም:: ኤርትራውያኖች፣ በኢትዮጵያውያኖች ላይ መራራ የሆነ ጥላቻ ስለአላቸው፣ ምንም ዓይነት ግንኙነት አለን ብለው አያምኑም:: ወደፊትም እንዲኖራቸው አይፈልጉም::

በእነሱ ጥናት፣
አጅግ አብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ በተለይም ሰባ በመቶ (70%) የሚሆኑት እስላሞች የሚጠይቁት ነፃነት ነው እንጂ፣ ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀልን አጥብቀው የሚቃወሙ ናቸው::በብዛት ክርስቲያኖች ይኖሩበታል በተባለውም በደጋው አውራጃ ውስጥ ያሉት ኤርትራውያኖች፣ አብዛኛዎቹ ነፃነትን የሚጠይቁ ናቸው::

በእነሱ አመለካከት፣
እስከዛሬ ድረስ ለኤርትራ ኢኮኖሚ ሕይወት ጣልያኖች ያደረጉት አስተዋፅኦ፣ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነው:: በአገሩ ውስጥ የተዘረጉት አውራ ጎዳናዎችና የባቡር መስመሮች፣ የወደብ ሥራ ዝግጅቶችና ለሕዝብ አገልግሎት እንዲውሉ የተገነቡት ሕንፃዎች፣ ጣልያን ለኤርትራ ዕድገት የመሠረተውን ዘመናዊ የቴክኒዎሎጂ ጥበብ የሚመሰክሩ ናቸው:: .....ለእንዱስትሪም አገልግሎት የተቋቋሙት የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫዎችና፣ ለአገሪቱ የኢኮኖሚ ሕይወት አስፈላጊ የሆኑት ልዩ ልዩ ፋብሪካዎች የሚሰጡት ጥቅም እጅግ የሚደነቁ ናቸው:: ከዚህም በላይ ጣልያኖች ለኤርትራ ሕዝብ ያቋቋሙት የእርሻ ምርት ዝግጅቶችና የከብት እርባታዎች ዘመናዊውን የልማት ሥራ ቅልጥፍና የተከተሉ በመሆናቸው፣ ኋላ ቀር ለሆኑ አገሮች ሁሉ ምሳሌነታቸው በጣም ጠቃሚ ነው::

በእነሱ አስተያየት፣
የኤርትራን ግዛት ለኢትዮጵያ እና ለሱዳን ለማከፋፈል፣ ከዚህ ቀደም በታላቋ ብሪታንያ የቀረበው ሀሳብ፣ ከፍተኛ አደጋ የሚያስከትልና ጠንቀም በአካባቢው በሚገኙት አገሮች ላይ ተዛምቶ ሠላምን የሚነሳ ነው:: ኤርትራውያኖች፣ እስላሞቹም ሆኑ ክርስቲያኖቹ፣ አገራቸው ለባዕድ መንግሥታት እንድትከፋፈል አይፈቅዱም::

በእነሱ ሙሉ ዕምነት፣
ለኤርትራ ጉዳይ ትክክለኛው መፍትሔ፣ አገሪቱ በተባበሩት መንግሥታት የበላይ መሪነት ለአሥር ዓመታት በሞግዚት አስተዳደር ከቆየች በኋላ፣ ነፃነቷን ማግኘት ብቻ ነው::

ከዚህ በላይ እንደታየው ጓቴማላና ፓኪስታን በሰጡት አስተያየት፣ ምን ያህል የጣልያንን ስሜትና ፍላጎት እንደተከተሉ መገንዘብ ይቻላል:: የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ የአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ሲፈጸም ባደረጉት ንግግር፣ ለመርማሪው ኮሚሽን አባልነት ጣልያን ለምን እንዳልተመረጠ አልገባኝም፣ ሲሉ የገለጹት የምሬት አስተያየት ይታወሳል:: አቶ አክሊሉ እንደተናገሩት፣ በዚያን ጊዜ፣ ጣልያን ዳኛ ሆኖ ባይመረጥም፣ እንደ ጣልያን ሆነው የሚፈርዱለትን ጓቴማላንና ፓኪስታንን ስለአስመረጠ፣ ቅሬታ አልተሰማውም::

እነዚህ ሁለት አገሮች በሕብረት ሆነው ስለ ኤርትራ የወደፊት ዕድል ባቀረቡት መፍትሔ፣ አገሪቱ ነፃነቷን ከመቀበሏ በፊት ለአሥር ዓመታት በተባበሩት መንግሥታት የበላይነት በሞግዚት መተዳደር አለባት ሲሉ፣ ልክ ለሱማሌ እንደተደረገው በተባበሩት መንግሥታት ባንዲራ፣ ሞግዚት አስተዳዳሪው ጣልያን እንደሚሆን እርግጠኞች ሆነው ነው::

ለ/ <u>በርማ፣ ደቡብ አፍሪካና ኖርዌይ፤</u>

እነዚህ ሶስት አገሮች፣ ለኤርትራ መፍትሔ በዝርዝር ያደረጉት ጥናትና በመጨረሻም ያቀረቡት ራፖር ሙሉ በሙሉ አንድ ዓይነት ነው ባይባልም፣ አንድ ዓይነት በሆነ መሠረታዊ አቋም ላይ መገኘታቸውን ያሳያል:: ሶስቱም አገሮች የኤርትራን ጉዳይ የመረመሩት ቅንና እውነተኛ በሆነ መንገድ እንጂ፣ ጓቴማላና ፓኪስታን እንዳደረጉት፣ ለግል ጥቅም ሲሉ ጆሮአቸውን ከዓይናቸው አስበልጠው የጠላት መሣሪያ አልሆኑም::

የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ኢትዮጵያ፣ ገና ከመጀመሪያው ትክክለኛ ፍርድ የሚገኘው ከኖርዌይ ብቻ ነው ብላ ዕምነቷን ስታጸና፣ በደቡብ አፍሪካ ዳኝነት ምንም ዓይነት ተስፋ አለማድረጓና፣ በበርማም መልዕክተኛ ላይ ጥርጣሬ ማሳደሯ ይታወሳል:: ነገሩ ያልተጠበቀ ሆነ:: የጣልያን ደጋፊነቱ ሳይታለም የትፈታ ነው የተባለው የደቡብ አፍሪካ ኮሚሽነር፣ ለኤርትራና ለኢትዮጵያ ሕዝቦች የአንድነት ሕይወት የሚደግፍ አስተያየት ሰጭ ሆኖ ተገኘ:: እንደዚሁም የበርማ መልዕክተኛ የድጋፍ አስተያየቱን ለሮማ መንግሥት እንዲሸጥ፣ ለግል ችግሩ ማቃለያ የሚሆን የአሜሪካ ዶላር ቢዘጋጅለትም፣ በመጨረሻው <u>መብላት ከሁለት፣ መፍረድ ለእውነት</u> እንደተባለው፣ በእውነት ያምነበትን፣ የኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር መተሳሰር አስፈላጊነት በሚገባ አረጋገጠ። ከሁሉ ይበልጥ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ያስደነቃቸው የደቡብ አፍሪካ አቋም ነበር:: የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድ በዚያን ጊዜ ፓሪስ ስለነበሩ፣ ስለዚሁ ጉዳይ ለንጉሠ ነገሥቱ በላኩት ልዩ ማስታወሻ እንዲህ ብለዋል::

« ..... ግርማዊነትዎ በሚደክሙበት በኤርትራ ጉዳይ፣ ከመርማሪው ኮሚሲዮን አባሎች መካከል የደቡብ አፍሪካ፣ መልዕክተኛ ድጋፍ ማግኘታችን ጠቃሚ ነው:: ሆኖም ይህን የድጋፍ አስተያየት ያገኘነው፣ በዘር ልዩነት ፖሊሲ ላይ ከተመሠረተው ከደቡብ አፍሪካ መንግሥት አለመሆኑን ግርማዊነትዎ እንዲያውቀው በትህትና አሳስባለሁ:: እንዲሁም አንዳንድ ሰዎች እንደሚሰጡት አስተያየት ይህ ድጋፍ የተገኘው ታላቋ ብሪታንያ በደቡብ አፍሪካ መንግሥት ላይ ፕሬሲዮን PRESSION (ተጽዕኖ) በማድረጓ ምክንያት ነው፣ የሚባለው ሁሉ ትክክል አይደለም:: እኔ ባገኘሁት ኢንፎርማሲዮን (መረጃ) የደቡብ አፍሪካ መልዕክተኛ የሆነው ጄኔራል ቴሀሮን (THERON) በአገሩ ላይ ያለውን <u>የዘር ልዩነት ፖሊሲ የሚቃወም ሰው በመሆኑ፣ በራሱ ዕምነት የወሰደው እርምጃ ነው</u> እንጂ፣ ከደቡብ አፍሪካ መንግሥት የተሰጠው መመሪያ የለም:: ስለዚህ ለግርማዊነትዎ ለማሳሰብ የምፈልገው፣ ጄኔራል ቴሀሮን የስጠን እርዳታ ጠቃሚያችን ቢሆንም፣ የግርማዊነትዎ ኢትዮጵያ በደቡብ አፍሪካ መንግሥት ተደገፈች ተብሎ ተፋፍሞ ቢወራ በጥቁር ሕዝብ ዘንድ መልካም ግምት ስለማይኖረን፣ ጃንሆይ ዘንድ ለሚቀርቡት ለእንግሊዝ አምባሳደርም ሆነ ለሌሎቹ፣ ስለደቡብ አፍሪካ ጉዳይ ምንም ዓይነት መልካም አስተያየት እንዳይሰጥ ነው:: ...... ጃንሆይ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ይመለከቱታል:: በኤርትራ ጉዳይ የአቀርዳት ግዛት ወደ ሱዳን እንዲቀላቀል የታሰበው፣ በመርማሪው ኮሚሽን አለመደገፉን እንግሊዞች ሲያውቁት፣ ለኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም ያሳዩትን ድጋፍ ያቀዘቅዛሉ የሚል ሥጋት አለኝ:: ለማናቸውም ሁኔታውን በግልጽ ለመረዳት የአምስቱ ዳኞች ራፖር ተዘጋጅቶ በኦፊሲየል እስኪቀርብ ብንጠብቅ ይሻላል:: ...... » እንደተለመደው የጃንሆይም መልስ በፍጥነት ፓሪስ ተልኳል::



የኢትዮጵያ ዋና ተቃዋሚ የሆነው፣ የፓኪስታን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዛፍሩላህ ካን፤

(ፎቶ U.N)

*ይድረስ ካቶ አክሊሉ፤*

*« ..... ስለ ደቡብ አፍሪካ ጉዳይ ያደረግከው መከታተል ደስ አሰኝቶናል:: ይኸ በጥቁር ሕዝቦች ላይ የነገሠው የፈረንጅ መንግሥት መልዕክተኛ፤ አስተያየቱን ወደ ወዳጃችን ወደ ኖርዌይ በማስጠጋቱ የተገባ ዳኝነት ቢሠራም፤ በእኛ በኩል ምሥጋና እንዲሰጠው አልፈቀድንም:: የታላቋ ብሪታንያም አምባሳደር እኛ ዘንድ ሊቀርብ፤ ስለ ደቡብ አፍሪካ ዳኝነት አንሥቶ አስተያየታችንን ቢጠይቀን፤ ግልፅ አድርጓል ማለታችን እንደማይቀር ትረዳዋለህ:: በዚህ ላይ የሚጨመር እንዲኖር በእኛም በኩል የታሰበ ነገር የለም:: በእንግሊዞች በኩል ስለአደረብህ ሥጋት የገለጥክልን እኛንም አሳስቦናል:: ከመርማሪዎቹ ዳኞች ራፖር በኋላ፤ የኤርትራ ዋና ጉዳያችን በተባበሩት መንግሥታቶች ጉባኤ ሲታይ፤ ወዳጆቻችን እስከ ዛሬ የሰጡንን ድጋፍ የሚያቀዘቅዙት ከሆነ፣ ከባድ ችግር ሊፈጥርብን አይችልም ወይ ? ይኸ ጉዳይ አሳሳቢ ስለሆነ፣ የሚያስፈልግ ከመሰለህ እኛው ራሳችን ወደ እንግሊዝ አገር ሄደን ከመሪዎቹ ጋር ከመነጋገር ወደ ኋላ ስለማንል ጠ ቃሚነቱን አጥንተህ የምታስበውን በቶሎ እንድታቀርብልን ይሁን ...... »*

አቶ አክሊሉ ለንጉሠ ነገሥቱ እንደአሳሰቡት፣ **የኖርዌይ**፣ የበርማና የደቡብ አፍሪካ ኮሚሽነሮች ያዘጋጁት መፍትሔ፤ ለኢትዮጵያ **መልካም** ሲሆን፤ እንግሊዞች የሚፈልጉትን የአቀርዳትን ወደ ሱዳን መቀላቀል ጉዳይ **አልደገፉትም**::

**ሶስቱም አገሮች፤**

አብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ ወደ ኢትዮጵያ **መመለስን** የሚፈልግ መሆኑን አምነውበታል::በተለይም በደጋዎቹ አውራጃዎች **ያሉት** የኤርትራ ተወላጆች ራሳቸውን ኢትዮጵያዊ አድርገው **እንደሚቆጥሩ** ተመልክተዋል::

**ሶስቱም አገሮች፤**

ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር መሆን የሰባትም **ብሎ የሚጥሩት**፣ የምዕራቡ ቆላ የእስላም ሊግና የነፃነት ግንባር የተባሉት **ፓርቲዎች**፤ በቂ የሆነ የሕዝብ ድጋፍ እንደሌላቸው ተገንዝበዋል።

**ሶስቱም አገሮች፤**

ኤርትራ ራሷን ችላ ለመኖር የማትችል **አገር መሆንዋን**፤ የወደፊቱም ተስፋዋ በእርሻ ሀብት **በበለጸገችው በኢትዮጵያ ላይ** የተመሠረተ ስለሆነ፤ የሁለቱ አገሮች በፖለቲካና **በኢኮኖሚ መተሳሰር** እጅግ አስፈላጊነቱን ተስማምተውበታል::

**ሶስቱም አገሮች፤**

ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር እጅግ ጥብቅ የሆነ የዝምድና ሐረግ ያለውን የኤርትራ ሕዝብ፣ ከእናት አገሩ ከኢትዮጵያ ጋር ለማዋሀድ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት ያቀረበው ጥያቄ ተገቢ ሆኖ አግኝተውታል::

እነዚህ ሶስት አገሮች በእነዚህ በተዘረዘሩት አራት ነጥቦች ላይ የምርመራቸውን ውጤት ካስተባበሩ በኋላ፤ ኤርትራና ኢትዮጵያ አብረው በሠላምና በሕብረት ሊኖሩ የሚችሉበትን የመተዳደሪያ ዘዴ ሲያመቻቹ በመካከላቸው የሀሳብ ልዩነት ተፈጠረ:: በርማና ደቡብ አፍሪካ ለኤርትራና ለኢትዮጵያ አንድነት ለዘለቄታው ጥሩ መፍትሔ የሚሆነው፤ በፌዴሬሽን



ከበርማና ከደቡብ አፍሪካ በቀረበው የፌዴሬሽን መፍትሔ ላይ፣ የብራዚል፣ የሜክሲኮና የቺሊ መልዕክተኞች፣ የተባበሩት መንግሥታት ጊዚያዊ ኮሚቴ ሲወያዩ፣

(ሐምሌ 1952)
(ፎቶ U.N)

አስተዳደር ሲወስን ነው ሲሉ፣ የኖርዌይ መልዕክተኛ ለሁለቱ አገሮች አንድነት የፌዴሬሽን ሕግ አያስፈልግም አለ።

የኤርትራና የኢትዮጵያ ውህደት በፌዴሬሽን ሥርዓት እንዲሆን በርማ እና ደቡብ አፍሪካ ከቀረቡት ሀሳብ፣ የኖርዌይ መልዕክተኛ የሚለይበትን ምክንያት፣ በዝርዝር ከገለጻቸው መሠረታዊ ጉዳዮች፣ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ነበሩ።

1. ኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ የምትመለሰው፣ የኢትዮጵያዊነት ነፃነትና የእኩልነት መብት ተሰጥቷት፣ በመንግሥቱም አመራር ሙሉ ተካፋይ ሆና ነው እንጂ፣ ለባዕድ መንግሥት አስተዳደር የቆየች ሆና መገመት የለባትም።

2. ኤርትራ ራሷን ችላ ነፃ መንግሥት ለመሆን የኢኮኖሚ አቅሟ አይፈቅድም ተብሎ ከታመነበት፣ የፌዴሬሽንም አስተዳደር ለመቀበል ያላት [illegible] ኃይልና የውስጥ መተዳደሪያ ገቢ [illegible] ነው ማለት አይቻልም። ስለዚህ፣ ኤርትራ ነፃ መንግሥት እንድትሆን በተባለው ሀሳብ እና፣ በፌዴሬሽን የውስጥ መንግሥት አቋቋም የራስ አስተዳደር መብቷ እንዲኖራት በቀረበው መፍትሔ መካከል፣ ልዩነት አለው ለማለት የሚያበ ግብ ምክንያት የለም።

3. አብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ ከእናት አገሬ ከኢትዮጵያ ጋር ልቀላቀል ብሎ ሲጠይቅ፣ ከዚህም [illegible] የኤርትራ የኤኮኖሚ ሕይወት አሁንም ከኢትዮጵያ ጋር [illegible] መሆኑ ሲታወቅ፣ እነዚህ ወንድማማች የነበሩ አገሮች [illegible] ፌዴሬሽን አስተዳደር መሆን አለበት ተብሎ በግዴታ የሚደረገው [illegible] ወደፊት በሁለቱ ሕዝብ መካከል ግጭትና አለመግባባት የሚፈጥር [illegible]።

4. የኤርትራ የወደፊት ዕድል አንድ ተገቢ የሆነ ውሳኔ ሳያገኝ እንደዚሁ አሁን ባለበት ሁኔታ ከቆየ፣ የአገሪቱን ሕይወት ፀበርቄ የሚያቃውሰውና የሕዝቡንም ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥለው ስለሆነ፣

1ኛ/ ከምዕራቡ [illegible] በስተቀር፣ ሌላው የኤርትራ ግዛት በሙሉ ከኢ[illegible] አስተዳደር ጋር እንዲ[illegible]

2ኛ/ አብዛኛው የምዕራቡ ቆላ አውራጃ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ጋር ለመቀላቀል አለመፈለጉን ስለአስታወቀ፣ ለተወሰነ ጊዜ አሁን ባለበት ሁኔታ በእንግሊዞች አስተዳደር እንዲቆይና፣ ወደፊት ልዩ ጥናት ተደርጐ እንዲወሰን፣

ሲል የኖርዌይ መልዕክተኛ አስተያየቱን ደምድሟል።

ስለ ምዕራቡ አውራጃ ጉዳይ የመርማሪው ኮሚሽን ሥራ እንደተጀመረ ለሞን፣ የደቡብ አፍሪካ መልዕክተኛ የእንግሊዞችን ሀሳብ በመከተል፣ መፍትሔው ከሱዳን ጋር መቀላቀል ነው ብሎ ነበር። ነገር ግን መርማሪው ቡድን የኤርትራን ግዛት እየተዘዋወረ በሚጐበኝበት ጊዜ፣ የቆላውም ሆነ የደጋው ሕዝብ፣ የአቆርዳትን አውራጃ ወደ ሱዳን መቀላቀል አጥብቆ የሚቃወም በመሆኑ፣ የእንግሊዞች ምኞት

ተሰፋ እንደሌለው የደቡብ አፍሪካው መልዕክተኛ በፍጥነት ተገነዘበ። ወዲያውም የበርማ ኮሚሽነር ለኤርትራ ጉዳይ መፍትሔው፣ የአገሪቱ ግዛት ሳይነጣጠል፣ በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር ቢቀላቀል ነው ሲል ያቀረበውን ሀሳብ፣ ጄኔራል ቴሀሮን መስማማቱን ገለጸ።

እነዚህ የበርማና የደቡብ አፍሪካ መልዕክተኞች ለፌዴሬሽን መፍትሔ አስተያየታቸውን ያስተባበሩት የሚከተሉትን ምክንያቶች በመደርደር ነበር።

1. ምንም እንኳን ከጠቅላላው የኤርትራ ሕዝብ መካከል አብዛኛው፣ ከኢትዮጵያ ጋር አንድነትን የሚፈልግ ቢሆንም፣ እርባ ከመቶ የሚደርሰው ሕዝብ ደግሞ፣ ከኢትዮጵያ ጋር መሆን እንደማይፈልግ መዘንጋት ስለማይቻል፣

2. ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተለይታ አሁኑኑ ወይም ወደፊት ነፃ ትሆናለች ቢባል፣ በኤኮኖሚ ረገድ ራሷን ለማስተዳደር የማትችል ከመሆኗም በላይ፣ ኢትዮጵያዊነትን የጠየቀው የኦርቶዶክስ ሀይማኖት ተከታይ የሆነውና የደጋው ነዋሪ ሕዝብ ከፍ ያለ የፖለቲካ ብጥብጥ ሊፈጥር ስለሚችል፣

3. ኤርትራ በሙሉ ከኢትዮጵያ ጋር መዋሀድ አለባት ተብሎ የተወሰነ እንደሆነ፣ ብዛት ያላቸውን የእስላሞቹን ጥላቻ ሊያባብሱና፣ በውጭም አገሮች ጣልቃ ገብነት ወደ እርስ በርስ ግጭት የሚያመራ ስለሚሆን፣

ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ሕይወቷን የምታስተሳስረው በሕግ በተመሠረተ በፌዴሬሽን አስተዳደር ከሆነ፣ በውስጥም ሆነ በውጭ አመለካከት ትክክለኛ ሚዛን ያለው ፍርድ ሆኖ፣ ተቀባይነትን ያገኛል ሲሉ <u>የበርማና የደቡብ አፍሪካ መልዕክተኞች፣ ውሳኔያቸውን አቀረቡ።</u>

እንደሚታወሰው ዩናይትድ ስቴትስ፣ ከጥቅምት 1949 ዓ.ም ጀምሮ ለኤርትራ ጉዳይ መፍትሔ ነው ብሎ ያሰበው፣ አገሩን ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን በማቀላቀል ነው።

ታላቋ ብሪታንያ ግን የፌዴሬሽን መንፈስና አስተዳደር፣ ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት ትርጉሙ የማይታወቅ እጅግ አስቸጋሪ ነገር ይሆናል ብሎ ከማመኑም በላይ፣ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ሲጥርበት የቆየውን የኤርትራን ምዕራብ ቆላ ከሱዳን ጋር የማቀላቀል ዕቅድ፣ ከበርማና ከደቡብ አፍሪካ የቀረበው መፍትሔ እንደሚያሰናክልበት፣ ግልጽ ሆነ።

## የፌዴሬሽን መፍትሔ

የተባበሩት መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን ቡድን ጥናቱን ከፈጸመ በኋላ፣ ያዘጋጀውን ራፖር ሰኔ 28 ቀን 1950 ዓ.ም ለጊዜያዊ ኮሚቴ (INTERIM COMMITEE) አቀረበ።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው፣ የበርማና የደቡብ አፍሪካ ኮሚሽነሮች በሕብረት ሆነው ባቀረቡት ሪፖርት፣ ኤርትራ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘውድ ሥር በፌዴሬሽን ተቀላቅላ የውስጥ አስተዳደሯን የምትመራበት መንግሥት ይኖራታል ብለው ነበር:: ይህን መፍትሔ ከሌሎቹ ቅድሚያ በመስጠት ጊዜያዊው ኮሚቴ እንዲነጋገርበት ዶክመንቱ ሲቀርብ፣ በበርማና በደቡብ አፍሪካ ሪፖርት ላይ ተገልጾ የነበረው የፌዴሬሽን ዓይነት መልኩን ለውጦ ተገኘ:: ይኸውም ንጉሠ ነገሥቱ ምንም ዓይነት ሥልጣን ሳይኖራቸው ለወጉ ብቻ የፌዴሬሽኑ አስተዳደር የበላይ መሪ ተብለዉ፣ በኤርትራ የሚቋቋመው መንግሥት በሙሉ ሥልጣን አገሩን ይመራል የሚል ሆነ:: የፌዴሬሽኑ ትርጉም እስከዚህ ድረስ በተጭበረበረ ሁኔታ ተለዋውጦ ለጊዜያዊው ኮሚቴ የቀረበው፣ ጣልያኖች በተለመደ ተንኮላቸው በጀርባ ገብተው፣ የበርማን መልዕክተኛ ይዘው በቀመሙት ተንኮል ሳይሆን እልቀረም ተብሎ ተጠርጥሯል:: ለዚህም ማስረጃ የሆነው፣ በመጀመሪያ ከተጻፈው ተለውጦ የቀረበውን የፌዴሬሽን አሠራር ትርጉም፣ የበርማ መልዕክተኛ ሲሰማ፣ ልክ አይደለም ብሎ አለመቃወሙ፣ ወይም ቢያንስ በግልጽ አለመቃወሙ ነው::

ንጉሠ ነገሥቱ ያለ አንዳች ሥልጣን ለፕሮቶኮል ብቻ የበላይ መሪ እንዲሆኑ የታቀደው የፌዴሬሽን ፎርሙላ፣ ለኤርትራ ነፃነት ይሰጣት ከሚለው ከጣልያን ምኞት ጋር የሚመሳሰል ስለሆነ፣ ኢትዮጵያ በምንም መንገድ የማትቀበለው መሆኑን የንጉሠ ነገሥቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አስታወቁ::

« ...... ስብዙ ሺህ ዓመታት በዓለም ላይ የተከበረ ነፃነቷን ይዛ የኖረች ኢትዮጵያ ከሕዝቦቿ መካከል ነፃ ሆና ከማታውቀው እና፣ በሕዝብ ቁጥር ከጠቅላላው ኢትዮጵያውያን አንድ ሀያኛ ከማትሆነው፣ ከኤርትራ ግዛት ጋር በፌዴሬሽን አትተሳሰርም:: ከኢትዮጵያ ጋር ተቀላቅላ በፌዴሬሽን የምትተዳደረው ኤርትራ መሆኗ በግልጽ መታወቅ አለበት ...... » ካሉ በኋላ፣ አቶ አክሊሉ ንግግራቸውን ሲፈጽሙ፣ « ..... በዚህ የተባበሩት መንግሥታት የጊዚያዊ ኮሚቴ ውስጥ የሚደረገው ሙከራ፣ ከዚህ ቀደም በኤርትራ ሕዝብ ዘንድ ተቀባይ አጥቶ የወደቀው የጣልያን የነፃነት ፎርሙላ፣ እንደገና ነፍስ እንዲዘራ ከሆነ፣ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ደህንነቷ አደጋ ላይ እንደወደቀ ቆጥራ፣ አስፈላጊውን እርምጃ ከመውሰድ አትቆጠብም ..... » ሲሉ አስጠነቀቁ::

በዚህ አኳኋን አቶ አክሊሉ የሰጡትን መግለጫ የጊዜያዊው ኮሚቴ ሊቀመንበርና ምክትሉ ስለደገፉት፣ በፌዴሬሽኑ አስተዳደር ንጉሠ ነገሥቱ ምንም ዓይነት ሥልጣን እንዳይኖራቸው፣ ባልታወቀ መንገድ በተንኮል ተቀነባብሮ የቀረበው ሀሳብ እንዲሰረዝ፣ ስምምነት ተደረገ:: ወዲያውም፣ ..... ኤርትራ በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር የምትቀላቀለው በንጉሠ ነገሥቱ የዘውድ ሥልጣን ሥር ነው ...... ብለው፣ ሰኔ 28 ቀን 1950 ዓ.ም በርማና ደቡብ አፍሪካ በሪፖርታቸው ላይ የጻፉት አስተያየት የሰጡበት፣ ኦሪጅናሉ ዶክመንት ቀርቦ ንግግር እንዲደረግበት ኮሚቴው ወሰነ::

የበርማ፣ የደቡብ አፍሪካና የኖርዌይ ኮሚሽነሮች፣ ጣልያን ለጥቅሙ ሲል ለኤርትራ ነፃነት ካልተሰጠ ብሎ ያደረገውን ጥረት፣ ሕዝቡ እንደማይደግፈው ቢያረጋግጡለትም፣ የላቲን አሜሪካ ወዳጆቹን ይዞ፣ በተባበሩት መንግሥታት ጓዳ አንዳንድ ተንኮል በመጠምጠም፣ ምኞቱን ለመፈጸም ተስፋውን አልቆረጠም:: የተባበሩት መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን ወደ ኤርትራ እንዲልክ የተደረገው እና አብዛኞዎቹም ዳኞች የተመረጡት፣ በጣልያን ፍላጐትና ብርቱ ጥረት መሆኑን

እናስታውሳለን። አሁንም የመርማሪው ኮሚሽነሮች ቡድን ሪፖርት በጊዜያዊው ኮሚቴ ሲጠና እንደታየው ሁሉ፤ ቀጥሎም ጉዳዩ በፖለቲካ ኮሚሲዮን ተመርምሮ በጠቅላላው ጉባኤ እስከሚወሰንበት ጊዜ ድረስ፤ የጣልያን የተንኮል ስንስለት እየተቀጣጠለ አብሮ ከመጓዝ አያቋርጥም።

የመርማሪው ኮሚሽን ቡድን ሪፖርት ተጠናቅቆ ለተባበሩት መንግሥታት ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ፤ የኤርትራ ጉዳይ በመጨረሻ ውሳኔ የሚያገኘው፣ በርማ እና ደቡብ አፍሪካ በሰጡት የፌዴሬሽን ሀሳብ እንደሚሆን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አክሊሉ አርግጠኛ ነበሩ። የፌዴሬሽን አስተዳደር ለኢትዮጵያም ሆነ ለኤርትራ ሕዝብ፣ ፍጹም እንግዳና የባዕድ ሥርዓት ስለሆነ፤ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እንዲቀበሉት ለማድረግ አቶ አክሊሉ ከባድ ችግር ገጠማቸው። በዚያን ዘመን በንጉሠ ነገሥቱ ዙሪያ ያለው የወልደጊዮርጊስና የመኰንን ሀብተወልድ የሕብረት ሥልጣን ማንም የማይደፍረው ስለሆነ፤ የፌዴሬሽኑን ሀሳብ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ያለ ቅሬታ እንዲቀበሉት የጸሐፊ ትዕዛዙንና የገንዘብ ሚኒስትሩን እርዳታ ጠየቁ።

ለወልደጊዮርጊስና ለመኰንን ሀብተወልድ አቶ አክሊሉ ባጭሩ ያመለከቱት፤ « ..... አሁን በተባበሩት መንግሥታት ኮሚቴ ላይ ንግግር የሚደረግበት የኤርትራ ጉዳይ፤ ውሳኔ የሚያገኘው በፌዴራሲዮን መልክ ካልሆነ በስተቀር፣ ሌላ አማራጭ መንገድ የለም። በእኔ በኩል ብርቱ ጥረት ለማድረግ የምሞክረው፤ በፌዴራሲዮኑ አሠራር የጃንሆይ ሥልጣን በጥና ጥና ጉዳዮች ላይ፣ በተለይ በውጭ ጉዳይ ፖሊሲ፣ በመከላከያ፣ በፊናንስና በመገናኛዎች በኩል በሕግ የተረጋገጠ እንዲሆን ነው። ከዚህ ውጭ ማድረግ የሚቻል አይመስለኝም። ...... ፌዴራሲዮኑን አንቀበልም ብለን ብንሟገት፤ ለጣልያን የታሰበውን የሞግዚት አስተዳደር ሀሳብ ለማስፈጸም መንገድ እንከፍታለን። ስለዚህ፣ ጃንሆይ በሰፊው አስተያየታቸው ጉዳዩን እንዲረዱትና፣ የፌዴራሲዮኑን ሀሳብ እንዲቀበሉት እርዳታ አለምናለሁ። ይህን ሁሉ የማስቸግረው፣ የኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ መመለስ፣ ፍጹም በሆነ የአንድነት አስተዳደር እንዲሆን፤ ጃንሆይ የጣሉብኝ አደራ እጅግ ስለከበደኝ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ እስከዛሬ ድረስ ጠላቶቻችንን ተቋቁመን ከዚህ ደረጃ መድረሳችን ትልቅ ነገር ሆኖ መታየት አለበት። በእኔ የግል አስተያየት፤ በታላላቅ ጉዳዮች ላይ፣ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ሥልጣን በሕግ ታውቆ፣ ለኤርትራ የፌዴሬሽን አስተዳደር መመሥረቱ፣ ኢትዮጵያን የሚጐዳት አይመስለኝም ...... » የሚል ነበር። ከጥቂት ቀናቶች በኋላ፤ ከጽሕፈት ሚኒስትሩና ከገንዘብ ሚኒስትሩ ላቶ አክሊሉ የተላኩት መልሶች ደረሱ።

## ሀ/ ከጸሐፊ ትዕዛዝ ወልደጊዮርጊስ ወልደዮሐንስ

*« ...... ስለ ኤርትራ ጉዳይ በተባበሩት መንግሥታት ኮሚሲዮን ላይ የሚደረገው ንግግር፤ የመጨረሻው ውሳኔ በፌዴራሲዮን አስተዳደር መሆኑ እንደማይቀር፣ ዘርዝረህ የላክልኝ ደርሶኛል። መቼም ይኸ ሀሳብ ዛሬ የተፈጠረ አይደለም። ባለፈው ዓመት አሜሪካኖች አቅርበውት፤ አንተም ታግለህ፤ እነዚያ ተንኮለኞች እንግሊዞችም ረድተውህ፣ ሳይሳካ መቅረቱን ሁላችንም እናስታውሳለን። ዛሬ ደግሞ የተባበሩት መንግሥታት በመረጣቸው ሁለት ዳኞች፣ የፌዴራሲዮኑ ሀሳብ ተደግፎ ሲቀርብ፤ በእነዚሁ በአሜሪካኖች ኃይልና እርዳታ፤ በዋናው ጉባኤ ላይ መወሰኑ የማይቀር ነው ያልከው፤ እኔም እዚህ ሩቅ ሆኜ ይታየኛል። መቸም አንድ ነገር ማመን ያለብህ፣ በአንተ በኩል ይኸ ቀረ፣ ይኸ ጐደለ የሚባል ነገር አለመኖሩን ነው። እዚህ ላይ በቁም ነገር መታየት ያለበት፣ በፌዴራሲዮንም ሆነ ወይም በሌላ የአስተዳደር መንገድ፣ ኤርትራ ለኢትዮጵያ ትመለሳለች እንጂ፤*

ከእንግዲህ ወዲህ ለጠላታችን ለጣልያን አትጸረግም። የድካምህ ውጤቱ ይኸ ነው። የፌዴሬሲዮኑ ውሳኔ እየገፋ ስለመጣ መቀበል ያስፈልጋል ብለህ ባመለከትከው መሠረት፣ ከጌቶቹ ጋር በሰፊው ተነጋግሬበታለሁ። አንተ ያለብህን ችግር ከማናችንም በበለጠ የሚያውቁት እሳቸው ናቸው። እርግጥ፣ የፌዴሬሲዮኑን ሀሳብ በቶሎ ከመቀበላችን በፊት፣ አንዳንድ ነገር ማድረግ ትችል እንደሆነ ? ብለው ተስፋ ያደርጉብሃል። ይኸውም፣ የኖርዌዩ ዳኛ እንደሰጠው አስተያየት፣ የአቆርዳቱ ጉዳይ ለጊዜው ቆይቶ፣ ሌላው ግዛት በሙሉ ያለ አንዳች ሁተታ ወደ እኛ እንዲመጣ፣ ከእንግሊዞችና ከአሜሪካኖች እርዳታ ለማግኘት ትሞክር እንደሆነ ? ብለው ያሰባሉ። መቸም የሚሆነውንና የማይሆነውን የምታውቀው አንተ ነህ። ..... በእኔ በኩል የምመክርህ ሁለት ነገር ነው። 1. የጌቶቹ ሀሳብ ምን እንደሆነ ስለምታውቀው፣ ከኖርዌዩ የቀረበው ሀሳብ እንዲወሰን የተቻለህን አድርግ። 2. በዚህ አኳኋን የማይቻል ሆኖ የፌዴሬሲዮኑ ጉዳይ ገፍቶ ከመጣ በቶሎ መቀበል ነው። በተረፈ ጤናህን ጠብቅ። ...... »

ለ/ ካቶ መኰንን ሀብተወልድ፣

« ..... ትናንት ጌቶቹን ሳነጋግራቸው፣ በዚህ ፌዴሬሲዮ በተባለው ነገር አክሊሉ እንደምንም ታግሎ ያስቀረው ይሆናል ብለው ተስፋ ያደርጋሉ። እንደምታውቀው የጃንሆይ ሀሳብ ትክክል ነው። ይኸ ፌዴሬሲዮ የሚባል ሕግ፣ በአንድ አካል ላይ ሁለት ዓይነት ቀለም መለጠፍ ከመሆኑ በቀር፣ አንድነታችንን የሚገፋ ሊሆን አይችልም። አንተ እስካሁን የምትደክምበትን ጌቶቹ ደህና አድርገው ስለሚያውቁ፣ ከአቅምህ በላይ የሆነ ነገር ለምን አልሠራህም ? አትባልም። እኔ የማስጨንቀህ አንድ ነገር እንድትሞክር ነው። በመጀመሪያ እንግሊዞችን፣ ከዚያም አሜሪካኖችን በወዳጅነት ይዘህ፣ ይኸን ለጃንሆይ አመራርና ለኢትዮጵያ አንድነት ማጠናከሪያ ምቹ ያልሆነ ነገር ለማስቀረት፣ የተለየ ድካም ብታደርግ የሚሳካልህ ይመስለኛል። ኤርትራ በሙሉ በፌዴሬሲዮ ወደ ኢትዮጵያ ይግባ ከሚባል፣ ይኸ ቀድሞውንም ኢትዮጵያ አይደለሁም የሚለው የአቆርዳት አውራጃ ሕዝብ ቀርቶብን፣ ሌላው ኤርትራ፣ ሙሉ ኢትዮጵያ ሆኖ ቢመጣልን ይሻለናል። በአንተ በኩል ይህ ሀሳብ እንዲሳካ ፊት ለፊት መሟገት፣ ወደፊት በታሪክ ያስወቅሰናል የሚል ግምት እንዳለህ ትዝ ይለኛል። ኢትዮጵያን አልፈልጋትም፣ በታሪክም በዘርም አልወክላትም ብሎ፣ በአደባባይ የቆመውን ሕዝብ፣ እኛም አንፈልግህም ብንለው፣ ታሪክ ለምን እንደሚወቅሰን ለእኔ አይታየኝም። የሆነ ሆኖ ለፖለቲካው ዘዴ ኃላፊው አንተ ስለሆንክ፣ በዚህ በኩል አልሞግትህም። እኔ የምናገረው የመሰለኝን ነው። ጃንሆይ እንደሚፈልጉት ቢፈጸም፣ ከብዙ ጣጣ ለለምንድን በብርቱ ድከምበት። ካልሆነ ደግሞ ፌዴሬሲዮ መቀበሉ አስፈላጊ ስለሆነ፣ ጸሐፊ ትዕዛዝም ደህና አድርጉ አስረድቷልና በዚህ በኩል ሥጋት አይደርብህ ...... »

ከዚህ በላይ እንደታየው ከጸሐፊ ትዕዛዝ ወልደጊዮርጊስም ሆነ ካቶ መኰንን ሀብተወልድ የተሰጠው ምክርና አስተያየት፣ አቀራረቡ ይለይ እንጂ፣ መሠረቱ አንድ ዓይነት ነው። ሁለቱም ከፍተኛቹ ባለሥልጣኖች፣ የፌዴሬሽኑን መፍትሔ ከመቀበል በፊት፣ ቢቻል ከኖርዌይ የቀረበው ሀሳብ ደጋፊዎች አግኝቶ እንዲፈጸም ይደከምበት የሚል ነው። አቶ አክሊሉም ይህንኑ በዣተ ልዑል ቤተመንግሥት ያለውን መንፈስ በመከተል ልዩ ጥረት ማድረጋቸውን አላቋረጡም ነበር። የኤርትራን እና የኢትዮጵያን ጉዳይ፣ በፌዴሬሽን መፍትሔ ብቻ መመልከት በቂ አለመሆኑን፣ የተባበሩት መንግሥታት ኮሚቴ እንዲገነዘበው፣ አቶ አክሊሉ ሙከራ ያደረጉት የሚከተለውን አስተያየት በማቅረብ ነበር።

« ...... ከአምስቱ የመርማሪ ኮሚሲዮን አባሎች መካከል ሶስቱ፣ አብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ጋር አንድ መሆንን እንደሚፈልግና፣ በኢኮኖሚም ረገድ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ካልሆነች በስተቀር፣ ራሷን ችላ ስመኖር እንደማትበቃ አረጋግጠዋል።

...... ኤርትራ ለአሥር ዓመታት በሞግዚት አስተዳደር ከቆየች በኋላ፤ ነፃነቷን ማግኘት ይገባታል ያሉትም፣ የጓቴማላና የፓኪስታን ጳኞች፤ የእገሪቱ የኤኮኖሚ ሕይወት ከኢትዮጵያ ተለይቶ ብቻውን መቆም እንደማይችል መስክረዋል:: እነዚሁ ዳኞች ከዚህም አልፈው፣ ኤርትራ ነፃ መንግሥት በምትሆንበት ጊዜ፣ በኤኮኖሚ ረገድ ሁለቱ አገሮች (ኢትዮጵያና ኤርትራ) በቅርብ የሚተሳሰሩበት ስምምነቶች እንዲደረጉ አስፈላጊነቱን አጠንክረዋል:: በዚህ አቀራረባቸው የጓቴማላና የፓኪስታን መልዕክተኞች አስተያየት፣ ትክክለኛውን የዳኝነት መስመር አለመከተሉን ለመረዳት አያስቸግርም:: ..... በአንድ በኩል ኢትዮጵያ ለኤርትራ እናቷ አይደለችም ብለው አየካዱ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ልጂ እይደለችም የሚሏት፤ ይህች ባዕድ ኤርትራ ነፃ መንግሥት እንድትሆን ሲጠይቁ፤ በኤኮኖሚ ረገድ ኢትዮጵያ መመገብ አለባት ይላሉ:: የእነዚህ የሁለት አገሮች መልዕክተኞች የፍርድ ሚዛን፣ ምን ያህል መዛባቱን ለመገንዘብ ከዚህ የበለጠ ግልጽ ማስረጃ የለም:: ኢትዮጵያ፤ እናትነቷ ለታወቀላት ልጆቿ ያላትን ማካፈልና መመገብ ሰብዓዊ ግዴታዋ ቢሆንም፤ እናትነቷ ለተካዱባት ልጆቿ ማሳደጊያ ወተት መለገስ አለባት ብለው፤ ፍርዳቸውን የሰጡትን የጓቴማላንና የፓኪስታንን ዳኝነት፤ በቁም ነገር ለመመልከት አይቻልም::

...... የበርማና የደቡብ አፍሪካ ኮሚሽነሮች፣ በኤርትራ ውስጥ ምንም እንኳ አብዛኛው ሕዝብ ለኢትዮጵያዊነቱ የቆረጠ መሆኑን ቢያረጋግጡም፤ በምዕራቡ ቆላ ነዋሪ ከሆነው ሕዝብ ውስጥ፤ የሚበልጠው ክፍል ኢትዮጵያን እንፈልግም ስላለ፣ ለሁሉም ወገን አስታራቂ እንዲሆን፣ የፌዴሬሽን አስተዳደር ቢመሠረት ይሻላል ብለዋል:: የበርማና የደቡብ አፍሪካ ኮሚሽነሮች ያቀረቡትን ይህንን የፌዴሬሽን መፍትሔ ለመቃወም ወይም ውድቅ እንዲሆን ለመጠየቅ ሳይሆን፣ ለኤርትራ ሕዝብ ዕድልና ሕይወት፣ ኢትዮጵያ በበኩሏ ጠቃሚ ይሆናል ብላ የምታምንበትን አስተያየት መግለጽ ትፈልጋለች::

...... የፌዴሬሽን አስተዳደር ትክክለኛ ትርጉሙና የአሠራሩ ዘዴ፣ በኤርትራ ሕዝብ ዘንድ ከዚህ ቀደም ተሰምቶ የማይታወቅና፣ ፍጹም አንግዳ ነገር ስለሆነ፣ ኮሚቴው ወደ ውሳኔ ከማምራቱ በፊት፣ የሕዝቡ የትምህርት ደረጃና የሥራ ኤክስፒሪያንስ፣ የውስጡን አስተዳደር ኃላፊነት ለመቀበል በቂ መሆን አለመሆኑን ጠለቅ ብሎ ማተኮር ያስፈልገዋል:: የተባበሩት መንግሥታት አባል አገሮች እንደሚያውቁት፣ ኤርትራ በጣልያን ቅኝ አስተዳደር ታሥራ በተሰቃየችበት በሃምሣ ዓመታት ውስጥ፤ ሕዝቡ በትምህርት ከአራተኛ ክፍል እንዳያልፍ በሕግ ተወስኖበት የኖረ ስለሆነ፤ የፌዴሬሽን ሕግ የሚሰጠውን የውስጥ አስተዳደር ሥልጣን ለመቀበል የሚችሉ፣ እንኳንስ የዩኒቨርሲቲ ቀርቶ የሁለተኛ ደረጃን እንኳ የፈጸሙ ኤርትራውያኖች፣ አለመኖራቸው መታየት አለበት::

...... የዲሞክራሲ ትርጉሙ የአብዛኛውን ሕዝብ ፍላጐት መፈጸም ከሆነ፤ አብዛኛው ሕዝብ የጠየቀው ኢትዮጵያዊነትን መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው:: እንግዲህ ይኸ ሕዝብ ወደ ጥንት አገሩ መመለስን እንደሚፈልግ፤ በወዳጅም በጠላትም ከተመሰከረ በኋላ፤ በማያውቀውና ባልተረዳው ሥርዓት፣ የተለየ አስተዳደር ያስፈልግሀል ብሎ መወሰን ወይም ማስገደድ፤ ጠቃሚ አለመሆኑን ኢትዮጵያ ታሳስባለች:: ...... እኔ ይህን ሁሉ ስናገር፤ የበርማ እና የደቡብ አፍሪካ ኮሚሽነሮች፣ ለኤርትራ ትክክለኛ መፍትሔ ፍለጋ ያደረጉትን ጥረት ሳልገነዘብ ቀርቼ አይደለም:: በርማና ደቡብ አፍሪካ የፌዴሬሽን መፍትሔ ይበጃል ያሉት፤ ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት የምዕራቡ ቆላ ነዋሪዎች፣ ከኢትዮጵያ ጋር መዋሀድን

ስለሚቃወሙ፣ አስታራቂ መንገድ በመፈለግ መሆኑን ሁላችንም እናውቃለን:: ይሁን እንጂ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር የምትቀላቀለው በፌዴሬሽን ነው ሲባል፣ ይህች በቅኝ ገዥዎች ስትሰቃይ የኖረች አገር፣ አቶኖሚው በሚሰጣት መብት የውስጥ አስተዳደሯን ስለማምራት፣ የሰው ኃይልና ያገር ውስጥ የገቢ ምንጭ ስለሚያጥራት፣ ከባድ ችግር ላይ እንደምትወድቅ መታወቅ አለበት::

ከዚህ ሁሉ ጣጣ ለመዳን፣ የኖርዌዩ መልዕክተኛ እንዳሳሰበው፣ በጣልያን ፕሮፓጋንዳ የተወናበዱት የምዕራቡ ቆላ ነዋሪዎች፣ ትክክለኛ ፍላጎታቸውን አጥንተው ለመወሰን ጊዜ እንዲሰጣቸውና፣ ሌላው፣ ሳያመነታ በቀጥታ ኢትዮጵያዊነትን የመረጠው ሕዝብ፣ አሁኑኑ በቀጥታእንዲቀላቀል ቢደረግ፣ የተሻለ መሆኑን ኢትዮጵያ ታሳስባለች ...... »

የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ይህን አስተያየት ለኮሚቴው ባቅረቡ ጊዜ፣ የታላቋ ብሪታንያ መልዕክተኛ ድጋፍ ይሰጥ ይሆናል የሚል ተስፋ ተደርጐ ነበር:: በመሠረቱ፣ የኖርዌዩ ኮሚሽነር ባቀረበው ራፖር፣ የኤርትራ የምዕራባዊው ቆላ አውራጃ ጉዳይ፣ ለጊዜው አሁን ባለበት ሁኔታ ቆይቶ፣ ወደፊት በሕዝቡ ፍላጐት እንዲወሰን አሳሰበ እንጂ፣ እንግሊዞች እንደሚፈልጉት ከሱዳን ጋር ይቀላቀል የሚል ፍርድ አልሰጠም:: ከዚህም ሌላ፣ አምስቱም የመርማሪው ኮሚሽን አባሎች በአንድ ቃል የተስማሙበት አንድ ነገር ቢኖር፣ የምዕራቡ ቆላ አውራጃ ወደ ሱዳን እንዲቀላቀል በእንግሊዞች የቀረበውን ሀሳብ፣ መላው የኤርትራ ሕዝብ መቃወሙን በየራፖራቸው መግለጻቸው ነው:: ስለዚህ፣ እንግሊዞች ከሚያዝያ ወር 1949 ዓ.ም ጀምሮ ሲደክሙበት የቆየው ጉዳይ፣ በአሁኑ ጊዜ እንደማይፈጸም ስለተገነዘቡ፣ ከኢትዮጵያ መልዕክተኛ የተሰነዘረውን አስተያየት መደገፍ አልፈለጉም::

የአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ በተካሄደበት ጊዜ፣ በጥቅምት 1949 ዓ.ም፣ ለኤርትራ ጉዳይ መፍትሔው በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር ማቀላቀል ነው ብለው፣ አሜሪካኖች ያቀረቡትን ረቂቅ ውሳኔ፣ አጅግ አድርገው የተቃወሙት እንግሊዞች እንደነበሩ ይታወሳል:: በዚያን ጊዜ፣ የታላቋ ብሪታንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኧርኔስት ቤቭን፣ የአሜሪካኖችን የፌዴሬሽን ሀሳብ አልቀበልም ያለበት ዋናው ምክንያት፣ ከኤርትራ ግዛት የምዕራቡ ቆላ አውራጃ ወደ ሱዳን እንዲቀላቀል የታሰበውን የሚያፈርስ በመሆኑ ነበር:: አሁንም የበርማና የደቡብ አፍሪካ መፍትሔ፣ እንግሊዞች የሚፈልጉትን የአቆርዳትን አውራጃ፣ ወደ ሱዳን የማቀላቀሉን ጉዳይ የሰረዘው መሆኑን አሜሪካኖች እያወቁ፣ የቀረበው የፌዴሬሽን ፎርሙላ ድጋፍ እንዲያገኝ ብርቱ ጥረት አደረጉ::

የተባበሩት መንግሥታት ጊዜያዊ ኮሚቴ፣ በአሜሪካኖች እርዳታ የፌዴሬሽኑን መፍትሔ ለመቀበል ሲዘጋጅ፣ የጣልያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ካርሎ ስፎርዛ፣ በድንገት አንድ ችግር ፈጥሮ ለማስናከል ተነሳ:: የኤርትራን ሕዝብ ፍላጐት እንዲመረምር አደራ የተሰጠው የመርማሪው ኮሚሽን ቡድን፣ በአንድ ዓይነት ሀሳብ ለመስማማት አለመቻሉ እጅግ የሚያሳዝን መሆኑን ከገለጸ በኋላ፣ ካርሎ ስፎርሳ ባቀረበው አዲስ ሀሳብ፡ « ..... ወደፊት የጠለቀ ጥናት ተደርጐ ለሁሉም ተስማሚ የሆነ መፍትሔ እስኪገኝ ድረስ፣ ላልተወሰነ ጊዜ መላው የኤርትራ ግዛት፣ በታላቋ ብሪታንያ ወታደራዊ አስተዳደር እንዲቆይ ያስፈልጋል..... » አለ::

እንግሊዞችም ከዚህ ቀደም ታላቋ ሱማሌ ብለው በነደፉት ፕላን፣ የኦጋዴንን አውራጃ ሳያገኙ በመቅረታቸው፣ ቀጥሎም የኤርትራን የምዕራብ ቆላ አውራጃ ከሱዳን ጋር አቀላቅለው ለመያዝ የተመኙት ስላልተሳካላቸው፤ በብስጭት መንፈስ ይኸንን ከካርሎ ስፎርሳ የተነገረውን የጣልያንን ሀሳብ ለመደገፍ ፈለጉ። ወዲያውም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዘንድ የተመልካችነት (OBSERVER) ቦታ ያለው፣ የጣልያን አምባሳደር አልቤርቶ ታርኪያኒ፣ ስፎርሳ የሰጠውን መግለጫ፣ የድርጅቱ አባል አገሮችና በተለይም የላቲን አሜሪካ ግሩፖች እንዲደግፉት ከፍ ያለ ጥረቱን ቀጠለ።

አሜሪካኖች ደግሞ በበኩላቸው፣ የጣልያንን የተንኮል ዕቅድ ለመስበር ቆርጠው ስለተነሱ፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ዲን አቸሰን (DEAN ACHESON) ራሱ፣ በኮሚቴው ስብሰባ ላይ ተገኝቶ፣ በፌዴሬሽኑ መፍትሔ አባሎቹን ካስማማ በኋላ፤ በደንቡ መሠረት ጉዳዩ ለዋናው የፖለቲካ ኮሚሲዮን እንዲተላለፍ አስደረገ። የንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣን በውጭ ጉዳይና በመከላከያ ብቻ ሳይወሰን፣ በፋናንስና በውጭ ንግድ፣ በመገናኛዎችና በወደብ አስተዳደር ጭምር እንዲሆን የቀረበው ሀሳብ፣ ብዙ ድጋፍ እያገኘ በመሄዱ፣ ጣልያኖች የበለጠ ተናደዱ። ይህንን የፌዴሬሽን እቋም ኮሚቴው ተቀብሎ፣ ለውሳኔ ወደ ፖለቲካው ኮሚሲዮን ከማስተላለፉ በፊት አስናክሎ ለማስቀረት፣ ጣልያኖች ላቲኖቹን ይዘው ያደረጉትን ሙከራ፣ የዩናይትድ ስቴትስ መልዕክተኞች ፈጥነው ባይደርሱበት ኖሮ፤ በቀላሉ አይከሽፍም ነበር። ዕድሜ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዲን አቸሰን የፌዴሬሽኑ ፎርሙላ በኮሚቴው ተደግፎ ለፖለቲካው ኮሚሲዮን ተላለፈ።

የኤርትራ ጉዳይ የሚወሰነው በፌዴሬሽን መልክ መሆኑ እየተረጋገጠ ሲመጣ፤ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ ለጃንሆይ በላኩት ቴሌግራም፣ « ...... ያለን ምርጫ ኤርትራን በፌዴራሲዮን አስተዳደር መቀበል ብቻ ስለሆነ፣ የግርማዊነትዎ ውሳኔ በአስቸኳይ እንዲደርሰኝ እጠብቃለሁ ...... » አለ። ወዲያው፣ ንጉሠ ነገሥቱ በገነተ ልዑል ቤተመንግሥት ትልቁን ስብሰባ አድርገው፣ ልዑል አልጋወራሽ፣ ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ፣ ጸሐፊ ትዕዛዝ ወልደጊዮርጊስ፣ አቶ ዘውዴ ገብረሕይወት (በዚያን ጊዜ የውጭ ጉዳይ ም/ሚኒስትር) በተገኙበት «... ኤርትራን በፌዴራሲዮን አስተዳደር እንድንቀበል ከተባበሩት መንግሥታት ስለተጠየቅን፣ እኛም መስማማታችንን ዛሬ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትራችን መልዕክት ስለምንልክለት፣ እንድታውቁት ነው ...... » ብለው መግለጫ ሰጡ።

ራስ ካሣ የፈሩት ደረሰ። በአንድ ኢትዮጵያ ላይ ሁለት መንግሥት ተቋቁሞ ሊካሄድ ነው። ኤርትራውያኖች የራሳቸውን መንግሥት አቋቁመው የሚተዳደሩ ከሆነ፣ ከኢትዮጵያ ጋር አንድ ሆኑ የሚባለው በምኑ ነው ? እንደዚህስ የመሰለውን ፍርድ መቀበሉ ጥቅሙ ምንድን ነው ? በማለት እጅግ ማዘናቸውን ገለጡ። ጃንሆይ ራስ ካሣ በተናገሩት አልተደሰቱም። « ...... አንተ እኮ ያልተረዳኸው ብዙ ነገር አለ። ጥና መላክተኞችንና ከእሱም ጋር አብረውት እንዲሠሩ የመደብናቸው ሰዎች፣ የሰጠናቸውን ትዕዛዝ ተከትለው በሚቻላ አኳኋን በዓለም ጉባኤ ፊት በብዙ ተሟግተውበታል። አሁን ለብዙ ዘመን ደክመን ጉዳዩ እዚህ ደረጃ ከደረሰ በኋላ አንቀበልም ብንል፣ ጣልያን ተመልሶ እንዲመጣ በሩን ከመክፈት በስተቀር የምናገኘው ጥቅም የለም። ይኸንን የኤርትራን ጉዳይ ስንዘምረው፣ በፌዴራሲዮን ይሰጠን ብለን እኛ አላመለከትንም። የኤርትራም ሕዝብ አልጠየቀም። በተለይም የኤርትራ ሕዝብ ለኢትዮጵያ አንድነቱን፣ ለኛም ታማኝነቱን የገለጠው በስፊው ነበር። ምን ይሆናል ? የተባበሩት መንግሥታት

ዳኞች ለአንዳንድ ጥቅም በጠላቶቻችን እየተገፋ፣ ይኸን ፌዴራሲዮን የሚባል ነገር ደነቀሩብን። ሆኖም የፌዴራሲዮን ነገር ሲታይ፣ ራስ ካሣ በተናገርከው ዓይነት አደለም። በኢትዮጵያና በኤርትራ ሁለት መንግሥት የለም። መንግሥቱ አኛው ነን። ፌዴራሲዮን የተባለው፣ ለኤርትራ የምንሰጠው የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ነው። ይኸውም፤ ኤርትራውያኖቹ በመሬታቸው ላይ የሚያገኙትን ማናቸውንም ነቢ ለራሳቸው መተዳደሪያ አድርገው፤ በጤናም፣ በትምህርትም፣ በርሻም ነገር ለመሥራት እንዲችሉ የታሰበ ነው። ከዚህ በቀር በፖለቲካም፣ በጦር መከላከያም፣ በኢንተርናሲዮናልም፣ በገንዘብም፣ በመገናኛዎችም፣ በንግዱም፣ ትልቁ ኃላፊነት የሚወድቀው እኛው ላይ ነው። ስለዚህ ሌት ተቀን ደክመን ብዙ ፈተናዎች ደርሰውብን የተገኘውን ዕድል ማቃለሉ የተገባ አደለም። በኛ ምኞትና በኛ ፍላጐት ቢሆን ኖሮ፣ ከአንድ ዘርና ከአንድ ታሪክ በመጡ ሕዝቦቻችን መካከል ፌዴራሲዮን የሚባል ነገር መታሰብ አልነበረበትም ነበር ...... » በማለት፤ በራስ ካሣ ላይ ያደረውን ሥጋት ለማስወገድ በሰፊው ተናገሩ።

ልዑል ራስ ካሣም የጃንሆይን ሁኔታ ሲያዩ አስተያየታቸውን ረገብ አደረጉ። « .... እንግዲያውማ የኛን ሀሳብ ተረድቶ በሀቅ የሚፈርድልን ዳኛ ነዋ! ያጣነው ? ... » አሉ። ጃንሆይም « ..... እምን ! በውነት የሚፈርድልን ዳኛ በማጣት ነው ...... » ብለው መለሱ።

የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ፤ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንድትቀላቀል በሚወስን ጊዜ፣ ኢትዮጵያ ውሳኔውን አክብራ እንደምትፈጽም የንጉሠ ነገሥቱ መልክም ፈቃድ መሆኑን፣ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ እንዲያውቁት ትዕዛዝ ተሰጥቶ፣ የዘውተ ልዑል ቤተመንግሥት ስብሰባ ተፈጸመ።

# የአምስተኛው ጉባኤ ሂደት

ሀ/ <u>የኢትዮጵያ አስተያየት</u>

መስከረም 28 ቀን 1950 ዓ.ም የአምስተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ በተከፈተ ጊዜ፣ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለመላው የአባል መንግሥታት እንደራሴዎች ያደረጉት ንግግር፤ በዘመኑ በነበረው ዓለምን በሚያሠጋው ፕሮብሌም ላይ ያተከረና፤ ለመሠረታዊው የኤርትራ ጉዳይ ለመጨረሻ ጊዜ ትክክለኛን ፍርድ የሚጠይቅ ነበር።

« ..... የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከተፈጸመ፤ ይኸው ዛሬ አምስት ዓመት ሆነ። በነዚህ ጊዜያቶች ውስጥ በዓለም ሕዝብ ላይ ለደረሰው አስቃቂ ዕልቂት፣ ተጠያቂዎቹ ከሆኑት ከጀርመንና ከጃፓን ጋር፣ አስፈላጊው የሠላም ስምምነት እስከዛሬ አልተፈረመም። ይህም ባለመሆኑ መላው ዓለም ቋሚ በሆነ በጦርነት ሕይወት ላይ እንደሚገኝ ተደርጐ ተቆጥሯል።

..... በአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያዎቹ ዓመታት ላይ፣ ዓለምን ለብዙ ጊዜ ያስቃዩት የናፖሊዮን ጦርነቶች ሲፈጸሙ፤ የፓሪስና የቪየና ስምምነቶች ሠላምን ባጭር ጊዜ ውስጥ እንደመሠረቱ ለናስታውስ፤ እንዲሁም ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት በኋላ በጥቂት ወራቶች ውስጥ የተከናወነውን የቬርሳይን የሠላም

ሁሉ ስናስብ፡ በዘመናችን የደረሰው የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ ስምምነት፣ ከአምስት ዓመታት በኋላም አለመፈረሙ ሊያስገርመንና ሊያሳስበንም ይገባል።

...... በዛሬው ዕንት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅታችን ላይ፣ የተደቀኑት አብዛኛዎቹ የዓለም ዋና ዋና ፕሮብሌሞች፡ ከነዚህ ከሠላም ስምምነቶች መጓደል የተነሣ መሆኑን መገንዘብ አለብን። ይህን መሠረታዊ ምክንያት በጥልቅ አውቀነው ይሁን ሳናውቅ፡ ከጦርነቱ ፍጻሜ በኋላ የአጭር ጊዜም ቢሆን አስተማማኝ ሠላም ሳናገኝ፡ በቀጥታ ወደ ቀዝቃዛው ጦርነት ተሻገረናል።

...... እኛ ታናናሽ አገሮች፡ የዚህ የቀዝቃዛው ጦርነት የተካፋይነት ደረጃ ባይሰጠንና፡ ድምፃችንም የመስማት ዕድል ባይኖረው፡ የተመልካችነትና የሩቅ ታዛቢነት መብት የተነፈገን አይመስለኝም። የኛ የታናናሾች ትግልና ጥረት፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለዓለም ሠላም ዋስትና እንዲሰጥልንና፣ በሕዝቦች መካከል ለሚፈጠረው ማናቸውም ችግር፣ ትክክለኛ ፍትሕ እንድናገኝበት ስለሆነ፡ ይህን አቋማችንን ኃያላን መንግሥታቶች እንዲያውቁልን እንጠይቃለን።

...... በዓለም ላይ ተደጋግመው የደረሱት አሰቃቂ ጦርነቶች ሁሉ፣ መነሻዎቻቸው በአምባገነኖችና በዲክታተሮች አብሬት መሆኑ እየታወቀ፣ ካለፈው ስህተት በመማር ለግፈኞችና ለአጥፊዎች ቦታ እንዳይኖር ለማድረግ፣ ችግሩ ምን ላይ እንደሆነ ለመከረኛው ሕዝብ ግልጽ ሆኖ እልታየውም። በአገሮችና በሕዝቦች መካከል በከፍለ ዘመናችን ለሚፈጠረው ችግር፡ ዳኛችንና ፍትሕ ሰጪያችን ይሆናል ብለን የመሠረትነው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅታችን፣ ኃላፊነቱን በትክክል እንዲወጣ ለማድረግ፡ የኃያላን መንግሥታቶች ሙሉ እምነትና በጐ ፈቃድ ብቻ ሳይሆን፣ የኛም የታናናሽ አገሮች ሕብረትና ጥንካሬ መታየት ነበረበት። በዚህ ረገድ በኛም በኩል የታየብንን ጉድለት ለማረም፣ ባለፉት ጊዜያቶች የተደረጉት ስህተቶች ትምህርት እንዲሆኑን ያስፈልጋል።

...... ባለፈው ዓመት በዚሁ በኒውዮርክ በተካሄደው በአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ፣ የሱማሌ ሕዝብ፣ ግፈኛው ጣልያን አስተዳዳሪው ሆኖ እንዳይመለስበት፣ ያቀረበውን ያን ሁሉ አሳዛኝ አቤቱታ አልሰማም ብሎ፤ ለቀድሞው ኮሎኒያሊስት መልሶ እንዳስረከበው ሁላችንም እናስታውሳለን። እንደዚሁም አብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ፣ ኢትዮጵያዊነትን መጠየቁ በአራቱ ኃያሳኖች ተመርምሮ ከታወቀ በኋላ፡ የጣልያን ወዳጆች ዳኞች ሆነው በተመረጡበት፣ በተባበሩት መንግሥታት ልዩ ኮሚሲዮን በድጋሚ እንዲመረመር መወሰኑን ሁላችንም እናውቃለን።

...... ወደ ኋላ ተመልሰን ይህን ሁሉ ሁኔታ በምናስተውልበት ጊዜ፣ ባለፈው ዓመት አቤቱታቸው ያልተደመጠውና ተገቢ ያልሆነ ውሳኔ የተጫነባቸው የሱማሌ ሕዝቦች፡ ዛሬ ምን እንደሚያስቡ ብናተኩር፤ ያለ ጥርጥር ሀዘናቸውና ምሬታቸው ለሕሊናችን ሠላም የማይሰጡ ሆነው እናገኛቸዋለን። እንደዚሁም፤ ለወደፊት ዕድላቸው ምን እንደሚፈልጉ ሀሳባቸውን በሚገባ ከገለጹ በኋላ፤ በድጋሚ እንዲመረመሩ አለአግባብ የተበየነባቸው ኤርትራውያኖች፣ ዛሬ በምን መንፈስና በምን አኳኋን ፊታቸውን ወደ ኒውዮርክ መልሰው፣ የሚሰጣቸውን ፍርድ እንደሚጠባበቁ እናያቸዋለን።

...... የተባበሩት መንግሥታት ከላኳቸው ከአምስቱ መርማሪ ዳኞች ውስጥ ሶስቱ፣ ኖርዌይ፣ በርማና ደቡብ አፍሪካ፤ የኤርትራን ሕዝብ ስሜትና አቋም በትክክል አዳምጠው፣ አስተያየታቸውን አቅርበዋል። ሁለቱ ዳኞች ጓቲማላና ፓኪስታን ደግሞ፣ ገና ከጠዋቱ ለጣልያን መንግሥት ጥብቅና የቆሙ በመሆናቸው፣ የኤርትራን ሕዝብ ስሜትና አስተያየት እነሱ በሚፈልጉት መልክ ተርጉመው፣ ኢትዮጵያን ለመጉዳትና ጠላቷን ለመጥቀም፣ ታሪካዊ የሆነ የተዛባ ፍርዳቸውን ሰጥተዋል። እንግዲህ የአምስተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ የትኛውን ይከተላል ? የአብዛኛዎቹን ዳኞች ? ወይስ የጥቂቶቹን ? ..... ይህን የዓለም ሕዝብ አተኩሮ የሚመለከተውን የተባበሩት መንግሥታት የመጨረሻ ውሳኔ ለመስማት፣ ሀገሬ የምትጠባበቀው ከፍ ባለ ናፍቆት ነው ...... »

አቶ አክሊሉ ይህን አስተያየት ለጠቅላላው ጉባኤ ከገለጹ በኋላ፣ ከእንግዲህ ወዲህ የመጨረሻው ፍርድ እስከሚሰጥበት ጊዜ ድረስ፣ በትዕግሥትና ዝምታ ከማዳመጥ በስተቀር፣ ምንም ዓይነት ንግግር ወይም መግለጫ ላለማድረግ ቆርጠው ነበር። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ እስከዚህ ለመወሰን የደረሱት፣ የኤርትራ ጉዳይ ከተጀመረ አንስቶ፣ በየምክንያቱ ለሚቀርቡት ጥያቄዎች ማብራሪያ ለመስጠት ሆነ ወይም በኢትዮጵያ ላይ ለሚሰነዘሩ የተዛቡ አስተያየቶች መልስ ለማቅረብ፣ ያደረጓቸው ንግግሮች በሙቶ የሚቆጠሩ በመሆናቸው፣ እንደ አንዳንዶቹ የላቲን አሜሪካ ተናጋሪዎች « እሰልቺ » እንዳይባሉ ነበር። ነገር ግን በዚያኑ ሳምንት ውስጥ፣ በተባበሩት መንግሥታት ጉባኤዎች ላይ በተመልካችነት (OBSERVER) የሚካፈለው የጣልያን ወኪል አልቤርቶ ታርኪያኒ፣ ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት ጉዳይ ጠቅሶ የተናገረው ስለአናደዳቸው፣ እንደገና ተመልሰው መድረክ ላይ መታየት ግድ ሆነባቸው። የጣልያን ወኪል የተናገረው፣ የአንድ አገር ሕዝብ አንድነት ሊከበርና ሊታወቅ የሚችለው፣ በሕዝቦች ሙሉ ፈቃድ መፈጸሙ ማስረጃ ሲገኝለት እንጂ፣ በግዴታ የተደረገ፣ ወይም በፈጠራ ታሪክ የተገነባ ሲሆን፣ ተቀባይነት እንደሌለው የኢትዮጵያ መንግሥት መገንዘብ ያስፈልገዋል የሚል ነው። በመሠረቱ የአምባሳደር ታርኪያኒ ንግግር፣ ከሚሲዮኑ ከሚያጠናው ከፌዴሬሽኑ መፍትሔ ጉዳይ ጋር የሚገናኝ አልነበረም። « ...... ኤርትራና ኢትዮጵያ አንድ ዓይነት ሕዝቦች ናቸው የሚባለው፣ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት የፈጠራ ታሪክ ውስጥ ብቻ ሲሆን፣ የሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ አንድነቱ የተመሠረተው በቅርቡ ዘመን ዳግማዊ ምኒልክ ከጣልያን መንግሥት የጦር መሣሪያ እርዳታ አያገኙ፣ ባደረጉት ዘመቻ ነው። ..... » በማለት፣ ከ1945 ዓ.ም ጀምሮ የሮማ መንግሥት የሚያሰራጨውን የተለመደ ፕሮፓጋንዳ፣ አምባሳደር ታርኪያኒ በድጋሚ ከመግለጹ በስተቀር፣ ለጉባኤው አዲስ ነገር አላቀረበም። ሆኖም፣ ይህን የተደረገውን የአፃፋ ንግግር ሰምቶ በዝምታ ማለፍ ስለማይቻል፣ በማያዳግም ሁኔታ መልሱን መስጠት ከኢትዮጵያ የሚጠበቅ ስለሆነ፣ የጉባኤው ሊቀመንበር የሆነው የኢራኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሚስተር ናስሮላህ ኢንተዛም፤ (NASROLLAH – ENTEZAM) ለአቶ አክሊሉ የመልስ መስጠት መብታቸውን ጠበቃቸው።

የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ንግግራቸውን የጀመሩት፡ « .... አገሬ ለብዙ ሺህ ዓመታት ነፃ ሆና በቆየው የሕይወት ዘመኗ፡ የፈጠራ ታሪክን የማዘጋጀትና፣ እውነተኛ ታሪክን በቅጥፈት የመሸፈን ችሎታም ልምድም እንደሌላት፡ ለታወቀው የኢትዮጵያ ወዳጅ ለጣልያን መልዕክተኛ ማረጋገጥ እወዳለሁ ..... » * በሚል ቃል ነበር።

« ..... በዚህ በተሰበሰብንበት የተባበሩት መንግሥታት እንደራሴዎች ገበታ ላይ፣ ስለ ኤርትራ አዳዲስ ታሪክ እየፈጠረ፣ በቅጥፈት አባል አገሮችን ለማሳሳት ሲጥር የከረመው ማን እንደሆነ፡ ባለቤቱ ራሱ እዚሁ ስለአለ፡ ( በጣታቸው ታርኪያኒን እየጠቆሙ ) የተለየ ማስረጃ ማቅረብ የሚያስፈልግ አይመስለኝም። ...... ስለ ኢትዮጵያ አንድነት የሚነገረው፣ የጣልያን መንግሥት በኤርትራ ጉዳይ ላይ እንደሚያሠራጨው የፈጠራ ታሪክ ዓይነት አለመሆኑን፣ የተከበረው የጣልያን መልዕክተኛ እንዲረዳው ተፈላጊውን መረጃ ልንሰጠው እንችላለን። ..... የኢትዮጵያ አንድነት የተመሠረተው፣ በኢትዮጵያውያኖች ብቻ ሲሆን፡ የመቶ ዓመት ዕድሜ ያልሞላው የጣልያን አንድነት ግን የተፈጠረው፣ ከውጭ በመጡ ወታደሮችና፣ የግዛት ጉቦ ተሰጥቶ ከፈረንሣዩ ናፖሊዮን ሶስተኛ፡ በተገኘው የጦር ኃይል ዘመቻ መሆኑን፣ ለአምባሳደር ታርኪያኒ ማስታወስ የሚያስፈልግ ይመስለኛል። .....

...... የዛሬ ዓመት በዚሁ አዳራሽ አምባሳደር ታርኪያኒ ስለእኔ ሲናገር፣ ..... የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የአንድን አገር አስተያየት፡ በሌላ አነጋገር ትክክለኛውን ስሜት ለመተርጎም ችሎታው በቂ አይደለም ...... ብሎኝ ነበር። የእኔ የችሎታ አጥረት የተተቸው በትርጉም ሥራ ስለሆነ፡ እኔም የዚህ ሞያ አለኝ ብዬ አልተከራከርኩም። ዛሬ ደግሞ እኔም በተራዬ እንዳደረግሁት አመለካከት፣ ክቡር የጣልያን ወኪል፡ ስለ ዘመናዊው የመቶ ዓመት ታሪክ ያለው እውቀትና አስተያየት፣ እጅግ የጠበበ መሆኑን መግለጽ እወዳለሁ ...... » ብለው ንግግራቸውን ፈጸሙ።

ከአንድ ዓመት በፊት በመስከረም 1949 ዓ.ም የኤርትራ ጉዳይ በዋናው ኮሚሲዮን ቀርቦ በሚታይበት ጊዜ፣ « ኤርትራ ነፃ መንግሥት መሆን አለባት » ብሎ የጣልያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ካርሎ ስፎርሳ ሀሳቡን ሲያቀርብ፣ በጀርባ የተጠመጠመው ተንኮል ትክክለኛው ትርጉም ምን እንደሆነ አቶ አክሊሉ ለጉባኤው በሰፊው አስረድተው ነበር። በዚሁ ጊዜ የጣልያን መልዕክተኛ አልቤርቶ ታርኪያኒ መልሱን ሲሰጥ፡ « ..... የትርጉም ሥራ የተለየ ሞያን የሚጠይቅ ስለሆነ፡ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ የክቡር ስፎርሳን ዲስኩር ሲተረጉም በጣም መሳሳቱን ለጉባኤው ከማረጋገጥ በስተቀር ሌላ የምጨምረው የለም ...... » ብሎ ሲናገር፡ በጣልያን ደጋፊዎች ዘንድ ከፍ ያለ የማውካካት ድምፅ ተሰምቶ እንደነበረ ይታወሳል። አሁን ደግሞ ከአንድ ዓመት በኋላ፡ አቶ አክሊሉ አጋጣሚ አግኝተው፣ የእሳቸው የትርጉም ችሎታ እንደተተቸባቸው ሁሉ፣ የታርኪያኒም የታሪክ ዕውቀት በጣም ውስን መሆኑን ሲናገሩ፡ በጉባኤው አዳራሽ አንድ ዓይነት የሳቅ ድምፅ ተሰምቶ ነበር።

* « የታወቀው የኢትዮጵያ ወዳጅ የሚለው ቃል የጉባኤው ተካፋዮችን እጅግ አስቋቸው ነበር »